# ፍኖተ ጽድቅ

ከብርሃኑ ጎበና

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
SSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

አዲስ አበባ 1986 ዓ.ም

አከፋፋይ:- ማኅበረ ቅዱሳን
አድራሻ :- ከቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
ከሸዋ ዳቦ ቤት አጠገብ
ፖስታ:- 80078 ስልክ 113191

© ብርሃኑ ገበና 1986

ሁለተኛ እትም መስከረም 1991

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

All Rights Reserved

አፍሪካ ማተሚያ ቤት

## መታሰቢያነትዋ

ለአባቴ ለአቶ እምውይ ካሣ ፤ለእናቴ ለወይዘሮ ስመኝሽ ጓንጉል፤ እንዲሁም ለመላው ቤተሰቤ ትሁንልኝ።

## ምስጋና

ረቂቁን ታይፕ በማድረግ ለተባበረችኝ ለወ/ት መድህን ገ/ማርያምና እንዲሁም የተዘጋጀውን መጽሐፍ ረቂቅ በኮምፒዩተር ለቅም ለአፍሴት ሕትመት ለካሜራ ዝግጁ በሆነ መልክ አቀናብረው ለሕትመት እንዲበቃ ላደረጉልኝ ለኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት ሠራተኞች በአንባብያን ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# ማውጫ


መግቢያ ........................................ 6

ምዕራፍ አንድ – ትውፊታዊ መረጃ

1.1 ትውፊት ማለት ምን ማለት ነው .................. 7

1.2 ከመጽሐፍ ቅዱስ በፊት ትውፊት ነበረ.......... 7

1.3 ትውፊታዊ መረጃ በሐዲስ ኪዳን ................. 12

1.4 ጌታ ያስተማረውና ያደረገው ሙሉ በሙሉ በሐዲስ ኪዳን አልተጻፈም ........................ 13

1.5 ሐዋርያትና ትውፊታዊ መረጃ .................... 17

1.6 የሙት ባሕር ጥቅሎች ........................ 23

1.7 የዮሐንስ ራዕይ ግዝት.......................... 25

ምዕራፍ ሁለት – ምሥጢረ ሥላሴ

2.1 አንድነት በሦስትነት፣ ሦስትነት በአንድነት ...... 32

2.2 ልዩ ሦስትነት........................................ 33

2.3 የሥላሴ ምሳሌ........................................ 37

2.4 የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥክርነት..................... 44

2.5 የሥላሴ ትምህርት በሐዲስ ኪዳን................. 54

2.6 የቅዱሳን አበው ምሥክርነት...................... 64

ምዕራፍ ሦስት – ምሥጢረ ሥጋዌ

3.1 ቀዳማዊ ቃል........................................ 68

3.2 ያ ቃል እግዚአብሔር ነው ....................... 72

3.3 ያ ቃል ሥጋ ሆነ...................................... 79

3.4 የተሳሳቱ አመለካከቶች ........................... 80

3.5 ተዋሕዶ .............................................. 82

3.6 ተዋሕዶ እንዴት? .................................. 85

3.7 የተዋሕዶ ምሳሌዎች.............................. 87

3.8 ሥጋ በተዋሕዶት መለኮት የባሕርይ አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል ............. 90

3.9 የጌታ ሰው መሆን በብሉይ ኪዳን ተጽፏል ...... 105

3.10 በክርስቶስ ሰው መሆን ላይ ኑፋቄን ያስተማሩ.. 121

3.11 እግዚአብሔር ሰው በመሆኑ ከባሕርይው አልተለወጠም ....................................... 125

3.12 ሰው የሆነው ምሉ መለኮት ነውን? ............ 125

3.13 ቅዱሱ ሰው በመሆኑ አልረከሰም .............. 130

3.14 ኃያሉ ስለ እኛ ደካማ ሥጋን መዋሐዱ ኃያልነቱን አይሽረውም ........................ 130

3.15 እግዚአብሔር ወልድ ሰው የሆነበት ዓላማ...... 131

3.16 ሥጋው በመቃብር አልቀረም..................... 142

3.17 ያረገው ማን ነው? ................................ 145

3.18 ዳግም ይመጣል ..................................... 148

3.19 የክርስቶስ ተቃዋሚዎች የሚያቀርቡአቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........................ 149



From the Library of

ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ

FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ለባለሟሎቹ ያስተላልፋል። ዳሩ ግን የንጉሡ አማካሪዎች ልጅ በመሆኑ ያደረገው ነው እንጂ አውቆ አይደለም ሕፃን ልጅ እሳትና ፍትፍት ቢያቀርቡለት ከፍትፍቱ ይልቅ እሳቱን በአይኑ አይቶ ደስ ስላለው ብቻ የሚመርጥ አይደለምን ይሉታል።

ፈርኦን ግን እናንተ እንደምትሉት አይደለም «ከፉውንና ደጉን ለይቶ የሚያውቅ ነው በማለት ሙሴ መገደል እንዳለበት ይናገራል ባለሟሎቹ ግን ከፉውና ደጉን ለይቶ የማያውቅ ነው በማለታቸው በፈተናው መሠረት እሳትና ፍትፍት በፈርኦን ፊት ቀረበ። ሙሴ ክፉውንና ደጉን የሚያውቅበት እድሜ ላይ በመሆኑ እጁን ወደ ፍትፍቱ ሊሰድ ሲል የእግዚአብሔር መልአክ እጁን ወደ ፍሙ እሳት እንዲዘረጋና ፍሙን አንስቶ እንዲጉርስ አደረገው። በዚህን ጊዜ ምላሱ ኩምትር አለ። ፈርኦንም ሙሴ ይህን ሲያደርግ በማየቱ ከቁጣው በረድ አለ የሞት ቅጣቱም ከሙሴ ተነሣ ዳሩ ግን ሙሴ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አፈኮልታፋ ሆነ። ይላል ትውፊታዊ መረጃ።

## ትውፊታዊ መረጃ በሐዲስ ኪዳን

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ቢያንስ ቢያንስ ለ20 ዓመታት ያህል ስለ ጌታ ከሰማየ ሰማያት መውረድ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድ፣ ማስተማር፣ መሞት፣ መነሣት፣ ማረግና ለፍርድ ዳግመኛ መምጣቱን ይማሩ የነበሩት በቃል ነበር ምክንያቱም ሐዲስ ኪዳን ገና በጽሑፍ አልተቀረጸም ነበርና በቅብብል ወይም በስሚ ያገኙትንም እነርሱ ራሳቸው ከጌታ እንደተቀበሉት አድርገው ያስተ ምሩ ነበር ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ጳውሎስ ነው። ጳውሎስ ጌታ ካረገ ከ8 ዓመት በኋላ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመነና ቃሉን መስበክ እንደጀመረ የታወቀ ሆኖ ሳለ ዳሩ ግን ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው ክታቡ «ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው» 1ቆር.11፥23–24። በማለት ጽፏል።

ጳውሎስ ከሐዋርያት በቃል የተማረውን ለሌሎች ደግሞ አስተላለፈ ወንጌልን ወንጌል የሚያሰኘው በጽሑፍ መስፈሩ ሳይሆን የሕያው የእግዚአብሔር ቃልና የሕይወት መንገድ መሆኑ ነው።



በጌታ ጊዜ ወንጌል ገና አልተጻፈም ነበር። ግን ጌታ ራሱ ሲያስተምር፣ «የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌል እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ» ማር.1፥5። በዚያን ጊዜ የተጻፈ ወንጌል ሳይኖር «በወንጌል እመኑ» ማለቱ ከእርሱ የሚወጣውን ቃል ማለቱ ነው። ለሐዋርያቱም «ወደ ዓለም ሒዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» ማር.16፥15።

ከእርሱ የሰሙትን የተማሩትን እንጂ በጽሑፍ ቀርጾ የሰጣቸው ወንጌል አልነበረም።

## ጌታ ያስተማረውና ያደረገው ተአምር ሙሉ በሙሉ በሐዲስ ኪዳን አልተጻፈም

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሃያ ሰባት ብቻ ናቸው። ከእነርሱ ውጭ ሌላ መጻሕፍት የሉም። ለእምነታችን የሚሆነው ሁሉ ተመጥኖ ተጽፎልናልና ከነኝህ መጻሕፍት ውጭ የተጠቀሰ ሕግ ሆነ ሥርዓት አያሻንም አንቀበልምም የሚሉ ክፍሎች መኖራቸው ግልጽ ነው።

ዳሩ ግን እነዚህ ክፍሎች ከሃያ ሰባቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውጭ ሌሎች ትውፊታዊ መረጃዎችንና ቅዱሳት መጻሕፍትን አንቀበልም ሲሉ ለሚጠየቁት ጥያቄ ሁሉ ከሃያ ሰባቱ መጻሕፍት ሳይወጡ መልስ ሊሰጡ ይችሉ ይሆን? ለመሆኑ አንድ ሰው የሚከተሉትን ጥያቄዎች ቢጠይቃቸው የሚሰጡት መልስ ይኖራቸው ይሆን?

1. በሃያ ሰባቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ እናት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ልደት የሚናገረው ነገር የለም ከየት መጣች ከሰማይ ወይስ ከምድር? ምድራዊት ከሆነች እናትና አባትዋ እነማን ናቸው?

2. በአራቱ ወንጌላውያን ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጻፈው ላይ ክርስቶስ እስከ 30 ዓመቱ የት እንደነበር ምን ሲሠራ እንደነበር የሚገልጸው ነገር የለም። ሰላሳ አመት እስኪሆነው የሠራው የለም?

3. «ወደ ቅፍርናሆም ገቡ ወዲያውም በሰንበት ወደ ምኩራብ ገብቶ አስተማረ እንደ ባለሥልጣን ያስተምራቸው ነበር እንጂ እንደ ጻፎች አይደለምና በትምህርቱ ተገረሙ» ማር.1፥21–22።

«ወደ ገዛ አገሩም መጥቶ እስኪገረሙ ድረስ በምኲራባቸው ያስተምራቸው ነበር» ማቴ.13፥54።

ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚዎችን ሳይቀር ያስገረመ ያስደነቀ የጌታ ትምህርት ምን ዓይነት ነበር? ይህን ያህል የጌታን ጠላቶች ሳይቀር ያስገረመ ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን ለአሁንዋ ቤተ ክርስቲያን መድረስ አለበት ከደረሰ በየትኛው መጽሐፍ ላይ እናገኘዋለን?

4. አንተ ጕልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ» ዮሐ.21፥18።

የጴጥሮስ አሟሟት እንዴት ነበር? ከሃያ ሰባቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በየትኛው ክፍል ተጽፎ ይገኛል?

5. «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ማር.16፥15።

ወንጌልን በመላው ዓለም እንዲያስተምሩ የተላኩት የጌታ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉም ሲሆኑ በሃያ ሰባቱ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ግን የምናገኘው የአምስቱን ሐዋርያት ብቻ ነው። የእነርሱም ቢሆን ሙሉ ትምህርታቸው በጽሑፍ አልተጻፈም። የቀሩት ሐዋርያትስ? ቃሉን አልሰበኩ ይሆን? ጌታ ባዘዛቸው መሠረት መስበካቸው (ማስተማራቸው) የታወቀ ነው ስብከታቸው ለአሁኑዋ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም ታዲያ የት ገባ?

በጽሑፍ የሠፈሩና ያልሰፈሩ ብዙ መሠረታዊ ትምህርቶች መኖራቸውን ሃያ ሰባቱ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ያረጋግጣል። የሚከተሉትን መረጃዎች ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል።

«እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ በወረቀትና በቀለም ልጽፈው አልወድም ዳሩ ግን ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ወደ እናንተም ልመጣ አፍ ለአፍም ልናገራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።» 2ዮሐ.1፥12።



«ልጽፍልህ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበረኝ ዳሩ ግን በቀለምና በብዕር ልጽፍልህ አልወድም። ነገር ግን ወዲያው ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ አፍ ለአፍም እንነጋገራለን» 3ኛ ዮሐ. ቁ.13።

ሐዋርያው በሁለቱም መልዕክቱ እንደገለጸው በጽሑፍ ያላሰፈረው ዳሩ ግን በቃሉ ያስተማረው እንዳለ ይገልጻል። ይህ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን በትውፊት ደርሷታል።

ጳውሎስ «የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ»1ቆሮ.11፥34። ይህ ጠቃሚ ድንጋጌ ለቤተክርስቲያን የሚያስፈልጋት በመሆኑ በትውፊት ደርሷታል ማለት ነው።

ዮሐ.20፥30፤ «ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ»

በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ በሌላ መጽሐፍ የተጻፈ እንዲሁም ሳይጻፍ የቀረ ብዙ ድንቅ ሥራ መሥራቱን እንዲሁም ማስተማሩን መግለጡን ማስተዋል ይገባል።

ዮሐ.21፥25፤ «ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል?

የወንጌላዊው አባባል ግልጽ ነው። እርሱ በመጠኑ ጌታ ያስተማረውንና የሰራውን ተአምር ከገለጠ በኋላ ጌታ በመዋዕለ ትምህርቱ ያስተማረው ይህ ብቻ ነው እንዳንልና የሰራው ተአምርም በወንጌሉ ላይ ብቻ የሠፈረውን ነው ብለን እንዳንወስን የማይወሰን ተጽፎም የማያልቅ መሆኑን ገልጦልናል።

በዚሁ መሠረት በቤተ ክርስቲያናችን ጌታ ያደረገውን ተአምር የሚገልጡ እንደ ተአምረ ኢየሱስ ያሉ መጽሐፍት አሉ።

ሉቃ.24፥27፤ «ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጓመላቸው»

ከትንሳኤው በኋላ ለሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ የተረጐመላቸው የመጻሕፍት ትርጓሜ በየትኛው ሐዲስ ኪዳን ክፍል ይገኛል? በሃያ ሰባቱ የሐዲስ ኪዳን ውስጥ እንደሌለ የታወቀ ነው።

ሐዋ.ሥራ 1፥3፤ «አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው»

አርባ ቀን ሙሉ ያስተማራቸው ትምህርት ምን ነበር? መቼም በወንጌል የተጻፈውን ከእንደገና ደግሞ ነው ያስተማራቸው እንደማይሉ የታወቀ ነው። ይሕ ጌታ ከተነሣ በኋላ ያስተማረው ትምህርት በሃያ ሰባቱ የሐዲስ ኪዳን ክፍል አልተጻፈም። ቤተ ክርስቲያን ግን ጥንታዊት እንደመሆንዋ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ከተ ነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረው ትምህርት አላት እርሱም መጽሐፈ ኪዳን በመባል ይታወቃል።

ከአሥርቱ ህግጋት አንዱ የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ የሚል ነው። በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ደግሞ ሰንበትነትዋ በገሃድ የተመሠከረላት ሰባተኛይቱ ቀን ቀዳሚት ነች ዳሩ ግን የክርስቲያኖች ሰንበት (ሰንበተ ክርስቲያን) ብለን የምናከብራት እሑድን ነው። እሑድን ሰንበት አድርጋችሁ አክብሩ የሚል በየትኛው የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ ይገኛል?

በዮሐ.ራእይ 1፥10፤ «የጌታ ቀን» የተባለችውን ሰንበተ ክርስ ቲያን እሑድ ለመሆንዋ ምን ማስረጃ ያገኛሉ? ታሪክንና ትውፊታዊ መረጃን መሠረት ካላደረጉ።

ዳሩ ግን የቤተክርስቲያንን ታሪክና ትውፊት መረጃ የምታደርገው ቤተ ክርስቲያናችን ያለምንም ማመንታትና ችግር መልስ መስጠት ትችላለች።

እንግዲህ በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያልሠፈረን በትውፊት የተገኘን በዓል እያከበሩ ትውፊትንና የቤተክርስቲያን ታሪክን መናቅን አንቀበልም ማለት ያስተዛዝባል።



## ሐዋርያትና ትውፊታዊ መረጃ

ሐዋርያት ወንጌልን ሲሰብኩ በጽሑፍ ያልሰፈሩ ዳሩ ግን በቃል ይተረኩ የነበሩ ትውፊታዊ መረጃዎችን ይጠቅሱ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ የሚያረጋግጠው ሐቅ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከቀደሙት አባቶች በቅብብል በርክክብ ያገኘውን (መንፈስ ቅዱስ የገለጸለትን) በወንጌል ስብከቱ ላይ ተጠቅምበት እናገኛለን።

«ኢያኔስና ኢያንበሬስም ሙሴን እንደተቃወሙት እንዲሁ እነዚህ ደግሞ አእምሮአቸው የጠፋባቸው ስለ እምነትም የተጣሉ ሰዎች ሆነው እውነትን ይቃወማሉ» 2ጢሞ.3፥8።

በጳውሎስና በሙሴ ዘንድ ያለው የዘመን ርቀት እጅግ በጣም ብዙ ሆኖ ሳለ፤ ጳውሎስ ሙሴ በፈርኦን ፊት ተአምር ሲያደርግ እነርሱም ምትሐታዊ ተአምርን በማድረግ ሙሴን ይቃወሙት የነበሩትን የፈርኦን ጠንቋዮችና አስማተኞች ዘጸ.7፥11–13። ስማቸው ሙሴ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ሳይኖር እርሱ ግን ስማቸውን ጠቅሶ መናገሩ በትውፊት ያገኘው መሆኑን የሚያሳይ ነው።

አሁንም ይኸው ጳውሎስ የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሕግ ሙሴ ከተራራው ይዞ በሦስተኛው ቀን ወደ እነርሱ በመጣ ጊዜ ነጐድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና እጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምጽ በተራራው ላይ ሲሆን የነበረውን መንቀጥቀጥና መሸበር ሲገልጥ «ሙሴም እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጥማለሁ እስኪል» ዕብ.12፥21። በማለት ገልጦታል ዳሩ ግን ይህን አባባል ጳውሎስ ከሙሴ መጽሐፍ ተጽፎ አግኝቶት ሳይሆን በትውፊት ያገኘው ነው።

ዮሐንስ ወንጌላዊም በራእዩ ላይ ትውፊትን ተጠቅምበት እናገኛለን «ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንዲሴስኑ በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን ሊያኖርባቸው ባለቅን ያስተማረ የበለዓምን ትምህርት የሚጠብቁ» ራእይ 2፥14።

በማለት ስለ በለዓም በሚተርከው በኦሪት ዘኁልቅ ላይ ያልሰፈረን ታሪክ ጠቅሷል። እስራኤል በሰጢም ተቀምጠው በነበረበት ጊዜ ከሞዓብ ልጆች ጋር ማመንዘራቸውንና ለአሕዛብ ጣኦት መስገዳቸውን በዚህም የተነሣ ሃያ አራት ሺህ የእስራኤል ልጆች እንዳለቁ በኦሪት ዘኁልቅ ም 25 ላይ ተጽፏል። ዳሩ ግን ዮሐንስ የጠቀሰው ታሪክ አልተጠቀሰም ዮሐንስ ያልተጻፈውን ታሪክ መናገሩ በትውፊት የሚተረከውን ይዞ መሆኑ ግልጥ ነው።

በለዓም ሐብተ መርገም የተሰጠው ሰው ነበር የረገመው የተረገመ የመረቀው የተመረቀ ይሆን ነበር። የሴፎር ልጅ ባለቅ እስራኤል በአሞራውያን ላይ ያደረገውን በማየቱና ከብዛታቸውም የተነሣ እስራኤልን በእርግማን እንዲያጠፋለት በለዓምን በብር በወርቅ አባበለው ዳሩ ግን እስራኤል እንዲረገም ያልፈለገ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ በለዓምን አስጠነቀቀው በእርግማኑም ፋንታ እንዲመርቃቸው አዘዘው።

በዚህ ጊዜ ባላቅ በበለዓም ተቆጥቶ እኔ ልትረግምልኝ ጠራኁህ እንጂ ልትመርቅልኝ ኖሯልን እነሆ ስትመርቃቸውም ሦስተኛህ ነው እኔ አንተን ላከብርህ አስቤ ነበር እግዚአብሔር ከከለከለህ ሒድ አለው። በዚህ ጊዜ ፍቅረ ንዋይ እንደ እሳት አቃጥሎት ባልራገም ምን ቸገረህ እነሱን ላጥፋልህ እንጂ ገንዘቡን ስጠኝ አለው።

ባለቅምእነሱ ከጠፉ ባትራገም እኔ ምን ቸገረኝ አለው። እንግዲያስ ያገርህን ሴቶች በአዋጅ አሰባስበህ ቆንጆ ቆንጆዎቹን ጠርተህ ሸልመህ አስጊጠህ ለጣዖቱ ከተሰዋው ተረፈ መሥዋዕት አስይዘህ ወደ እስራኤል መንደር ስደዳቸው እስራኤል ሲያዩዋቸው በዝሙት ፍላጻ ልባቸው ይወጋና ፈቃዳችንን ፈጽሙልን ከእኛ ጋር ተኙ ይሉአቸዋል። በዚህን ጊዜ ሴቶቹ እንዲህ ይበሉአቸው ምነውሳ ፍቅር የጋራ አይደለምን ከወደዳችሁን ለአምላካችን (ለጣዖታቸው ማለት ነው) የተሰዋውን ብሉልን ይበሉአቸው ያን ጊዜ ሴቶቹ ያቀረቡላቸውን መሥዋዕት በሚበሉበት ጊዜ (ለጣዖቱ የተሰዋውን) አምላካቸው (የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር) ቀናዒ (ቀናተኛ) ነው በዚህ ተቀጥቶ ተበቅሎ ያጠፋቸዋል። ብሎ ጥልቅ ምክር መክሮ ገንዘቡን ተቀብሎ ሒዷል።



ባለቅም በለዓም እንደመከረው አደረገ። እስራኤልም በለዓም የደገሰላቸውን ድግስ ሳያጤኑ ባለቅ በላካቸው ሴቶች ፍቅር ልባቸው ተረቶ ከእነርሱ ጋር በዝሙት ለመውደቅ ለጣዖት የተሰዋውን መስዋዕት በሉና አመነዘሩ በዚህ የተነሣ እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆች ላይ ተቆጥቶ መቅሰፍት አዘዘባቸው።

ይህ ከላይ ያለው በትውፊት የሚተረክ ነው በኦሪት ዘኁልቅም ሆነ በሌላው የኦሪት መጽሐፍ ግን ሰፍሮ አይገኝም ዮሐንስ በጽሑፍ ያልሰፈረውን በትውፊት ያገኘውን በሐዲስ ኪዳን ላለነው ክርስቲያኖች መማሪያ ይሆን ዘንድ ጠቅሶታል።

ይሁዳም በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድም ቦታ ሰፍሮ የማይገኝን በመጽሐፉ ጠቅሶ እናገኘዋለን «የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም» ይሁዳ ቁ.9።

ይሁዳ የጠቀሰው የቅዱስ ሚካኤልና የዲያብሎስ ክርክር በየትኛውም የ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሰፍሮ አይገኝም። ታዲያ ከወዴት አመጣው? ያለምንም ክርክር በትውፊት ያገኘውን ነው የጻፈው ነው መልሱ።

እንደዚሁም በቁጥር 14ና 15 ላይ ይኸው ይሁዳ ሄኖክ በዘመኑ የተናገረውን ትንቢት ጽፏል ሄኖክ ተናገረው ብሎ የጠቀሰው ትንቢት በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም። የሚገኘው በመጽሐፈ ሄኖክ በም 1 በቁ.9 ላይ ነው።

ስለዚህ ከ66ቱ ውጭ ሌሎች መጻሕፍት መኖራቸው በዚህ ይታወቃል።

ማቴ.2፥23፤ «በነቢያት ናዝሬዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ...ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ»

ይህን ትንቢት የተናገረው ነብይ ማነው? በየትኛው የትንቢት መጽሐፍስ ተጽፏል? በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ ትንቢታዊ ቃል ተጽፎ ይገኛል? ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ ድረስ

ብናነብ ይህን ትንቢታዊ ቃል አናገኘውም። ስለዚህ ሌሎች መጻሕፍትም ከ66ቱ ሌላ መኖራቸው በዚህ ይታወቃል።

ማቴ 27፥9፤ «በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርሚያስ የተባለው ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት የሚል ተፈጸመ» ይላል።

ይህ ትንቢታዊ ቃል በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉት የኤርሚያስ መጻሕፍት በፍጹም አናገኘውም ታዲያ ወንጌላዊው ነብዩ ያልተናገረውን በሐሰት እንደተናገረ አቀረበ ሊባል ነው? ካልሆነስ ቃሉን ከምን አገኘው?

በመሠረቱ ወንጌላዊው ያልተጻፈውን ወይም ያልተነገረውን እንደተነገረ አድርጐ አልጻፈም። የጌታን መሢህነት ለማስተባበል በጌታ ላይ የተነሱት ጌታን የሰቀሉት አይሁድ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መሢህነት ያስተባበሉ መስሎአቸው ገንጥለው በጣሉት በተረፈ ኤርሚያስ ላይ ይገኛል። ተረፈ ኤርሚያስ ም.7 ቁ.3 ይመልከቱ ቃሉን ያገኙታል።

ሉቃ.2፥25–32፤ «ስምዖን...የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር...በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር። ጌታ ሆይ አሁን እንደቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ...»

ወንጌላዊው ሉቃስ ስለ ስምዖን በተናገረው ላይ ብዙ አጠያያቂና ግልጽ ያልሆኑ ነገሮች አሉ የከዚህ በፊቱን ታሪክ ለማያውቅ ሰው ብዙ እንቆቅልሽ የሚሆኑበት ነገሮች አሉ። «በጌታ የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር» በየትኛው የ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሠፈረው? «ጌታ ሆይ እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ» የጌታ ቃል ምን ነበር? ትውፊታዊ መረጃ ከላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ይሰጠናል።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ284 ዘመን በጥሊሞስ የሚባል ገናና የግብጽ ንጉሥ ነበር። በዘመኑ እርሱን የሚያህል ኃያል ንጉሥ



አልነበረም ከገናንነቱ የተነሣ ይህን ዓለም እንደ ሰም አቅልጦ እንደ ገል ቀጥቅጦ ገዝቶታል ያገሩን ሁሉ ቋንቋ ያውቅ ነበር። ያልሠራሁት የቀረኝ ምን አለ ብሎ ባለሚሎቹን ጠየቀ እነርሱም ብዙ ጥበብ ብዙ ምሳሌ ያለባቸው አርባ ስድስቱ መጽሐፍተ ብሉያት (የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት) ቀርተውሃል እነርሱን ከዕብራይስጥ ቋንቋ ወደ ጽርዕ ቋንቋ ብታስተረጉም ስምህን ይበልጥ ገናና ያደርገዋል ስላሉት በዚያን ወራት በእስራኤል ላይ ሠልጥኖባቸዋልና ጸሐፍቱንም (ጸሐፊዎቹን) መጽሐፍቱንም ስደዱልኝ ብሎ ወደ እስራኤል ላከ አርባ ስድስቱን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከሰባ (70) ሊቃውንት ጋር አድርገው ልከዋል።

ንጉሡም ለእያንዳንዱ ሊቃውንት አንዳንድ ብላቴና ረዳት ሰጥቶአቸው ለሁለት ለሁለት አንዳንድ ድንኳን ሰጣቸው ሊቃውንቱም መጻሕፍቱን ተከፋፈሉት ትንቢተ ኢሳይያስ የተባለው መጽሐፍ ለስምዖን ደረሰው እየተረጎመ እያለ ምዕራፍ 7 ቁ 14 ላይ፥ «እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» የሚለው ጋ ሲደርስ ጥርጣሬ ገባው። ድንግል ሴት በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ትወልዳለች ብዬ ብጽፍ ስንኳን የአሕዛብ ንጉሥ የእስራኤል ንጉሥ ቢሆን ይቀበለኛል ብሎ። ድንግል የሚለውን የእስራኤል ሴት (ቆንጆ) በሚለው ብቻ ለውጦ ጻፈ። እንቅልፍ መጥቶበት ተኝቶ ቢነቃ ሴት ያለው ድንግል በሚለው ተተክቶ አየ። ረስቶት ሳያስተካክለው የተኛ መስሎት ድጋሚ ድንግል የሚለውን ወለቶሙ ለእስራኤል/የእስራኤል ሴት (ቆንጆ) በሚለው ለወጠ። ሁለተኛ እንቅልፍ መጥቶበት ተኛ ቢነቃ ሴትን ፍቆ ድንግልን ጽፎ አገኘው። አሁንም ለሦስተኛ ጊዜ ድንግልን ፍቆ ሴትን ጽፎ እንቅልፍ መጥቶበት ተኛ እንደገና ሲነቃ ሴት የሚለው ድንግል በሚለው ተተክቶ አገኘው ለአራተኛ ጊዜ እፍቃለሁ ሲል «ተው ይህን የተጠራጠርከበትን ሳታይ አትሞትም» ማለት ድንግል በድንግልና ጸንሳ በድንግልና የወለደችውን መሢህ ሳታይ አትሞትም የሚል ድምፅ ሰማ።

እግዚአብሔር አምላክ የተናገረውን የማያስቀር በመሆኑ ስምዖን በመንፈስ ቅዱስ ሳታይ አትሞትም የተባለውን መሢህ በአይኑ ያይ ዘንድ እንደ ትጓን ከአልጋ ተጣብቆ ጊዜውን ይጠባበቅ ነበርና። ይህን

በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ከዋሻው ውስጥ የተገኙት ጥቅሎች ምንነት ለጊዜው ግልጽ አልሆነም ነበር። ምክንያቱም የብራናው ጥቅል የተጻፈው በእብራይስጥ በመሆኑ ነው። ያ ወጣት ከዋሻው ይዞት የመጣው የብራና ጥቅል ግን የኢሳይያስ መጽሐፍ ነበር ይህም የኢሳይያስ የብራና ጥቅል (መጽሐፍ) በአሁን ጊዜ በብዙ ዓይነት ቋንቋ ተተርጉሞ በዓለም ላይ ተሠራጭቶ ከሚገኘው የኢሳይያስ መጽሐፍ የአንድ ሺ (1,000) ዘመን ቀደምትነት እንዳለው በኋላ ሊረጋገጥ ችሎአል።

ከዋሻው ውስጥ ያገኙዋቸውን ጥንታውያን በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉትን ጥቅሎች ይዘው ካሉበት በረሃ ተነስተው ወደ ጥንታዊቱ ከተማ ወደ ቤተልሄም ጉዞ አደረጉ። ከተማዋም እንደ ደረሱ ካንዶ (Kando) ለተባለ ነጋዴ በመጠነኛ ዋጋ ሸጡለት።

እነዚህ የአረብ ወጣቶች በዋሻው ውስጥ የተገኙት ጥቅሎች ይህን ያህል ገንዘብ የሚያወጡ የከበሩ ዕቃዎች መሆናቸውን ባወቁ ጊዜ ወደ ዋሻው እየተጓዙ ዋሻውን መመዝበር ሥራዬ ብለው ተያያዙት ዋናም የገንዘብ ማግኛ መንገድ አድርገው ቆጠሩት።

በከተማው በየወቅቱ የሚታዩት ጥንታውያን የብራና ጥቅል ቀስ በቀስ የመንግሥትን ትኩረት ሊሳቡ ቻሉ። ቀስ በቀስም ምንጫቸው በጥናት ተደረሰበት። አርኪዮሎጂስቶችም ወደ ዋሻው ተላኩ። ብዙ ታሪካዊ ቅርሶችን የብራና ጥቅሎችን የያዘው ዋሻ የብዙ ቲኦሎጂያን አይን ማረፊያ ሆነ ወሬው በአንድ ጊዜ ተናፈሰ።

ከ15,000 በላይ የሚሆኑ ሙሉ ያልሆኑ ጽሑፎችና ከ500 በላይ የሚሆኑ ያልታተሙ መጻሕፍት (manuscripts) ከዋሻው ውስጥ ተገኝተዋል። ሁሉም ግን የእብራውያን ሀብት መሆኑ በብዙዎች ታምኖበታል። እነዚህ የረዥም ዘመን እድሜ ባለቤት የሆኑ የብራና ጥቅሎች በነገረ መለኮት ተመራማሪዎች መካከል አወዛጋቢ ሆነዋል። ከተገኙት የብራና ጽሑፎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንደኞቹ ናቸው።

መጻሕፍቱ በዋሻው ውስጥ ለረዥም ጊዜ የተቀመጡ እንደሆነ በአንዳንዶቹ ተመራማሪዎቹ ዘንድ ታምኗል። ሐብትነቱ የይሁዲ እምነት ተከታዮች ብቻ ነው የሚለው አመለካከትን የነቀፉና



የክርስቲያኖችም ሃብት ነው ያሉም አልጠፉም። ጥቅሎቹ ብዙ እያከራከሩ ናቸው። ከውስጣቸው ጥቂቱ ተተርጉመዋል። የትርጉም ሥራው እንዲቀጥል የሚሹ የመኖራቸውን ያህል እንዳይተረጐሙ የሚከላከሉም ተገኝተዋል።

ጥቅሎቹ ቲዎሎጂያንን ትልቅ ውዝግብ ውስጥ የከተቱ ይመስላሉ። በእርግጥ ይህን ያህል ዘመን በዋሻው ውስጥ ኖሩ? በውስጣቸው የሰፈረውስ ቃል በአሁን ዘመን በብዙ ቋንቋ ከተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ምን ያህል አንድነት ወይም ተመሳሳይነት አላቸው?[1]

በሙት ባሕር አካባቢ ባለው ዋሻ ውስጥ የተገኙት ጥቅሎች ጥንታዊት ቤተክርስቲያን አሉ ብላ ለምትቀበላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት አይነተኛ መረጃ ሆኑዋል። ለምሳሌ እንደ መጽሐፈ ሄኖክ ላሉት መጻሕፍት።

## የዮሐንስ ራእይ ግዝት

አንዳንዶቹ ከስልሳ ስድስቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ሌላ የእግዚአብሔር ቃል የሠፈረባቸው መጻሕፍት የሉም ቢኖሩም እንዳንቀበል ማስጠንቀቂያ ተጽፎልናል በማለት በዮሐንስ ራእይ መጨረሻ ላይ የተጻፈውን ማስጠንቀቂያ ለማስረጃነት ይጠቅሳሉ። «በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሰፍቶች ይጨምርበታል ማንም ከዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጐድል በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጐድልበታል።» የዮሐንስ ራእይ 22፥18–19።

በመሠረቱ ግዝቱ ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራዕይ ላሉት ቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረ አለመሆኑን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጠለቅ ያለ እውቀት መኖርን አይጠይቅም መጠነኛ ግንዛቤ ያለው ሁሉ የሚረዳው እውነታ ነው። ምክንያቱም በአሁን ጊዜ በአንድ ጥራዝ እንደ አንድ ወጥ መጽሐፍ ሆኖ በእያንዳንዳችን እጅ የሚገኘው

[1] Resurrecting the Dead Sea Scrolls

መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ዘመንና በአንድ ፀሐፊ የተጻፈ አለመሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ሁሉ ይረዳዋል።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነው። ሌላው ቀርቶ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንኳን በአንድ ወቅት በአንድ ጸሐፊ አልተጻፉም። እንግዲህ እውነቱ ይሄ ከሆነ የዮሐንስ ራእይን ማጠቃለያ ለሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አድርጐ መናገር አላዋቂነትን መናገር ነው።

ማስጠንቀቂያው ለዮሐንስ ራእይ ብቻ የተነገረ መሆኑን ለመገንዘብ ካስፈለገ ቃሉን ደግሞ ደጋግሞ ማንበቡ ብቻ በቂ ነው፡ «በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን <u>የትንቢት ቃል</u>» «...ማንም በዚህ <u>በትንቢት መጽሐፍ</u>» መጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት መጽሐፍ ብቻ አይደለም የዛሬ ሁለት ሺ ዓመት በክርስቶስ የተገኘውን የቤዛነት ሥራ እንደዚሁም የጥንታውያን የእስራኤልን ታሪክ እንዲሁም የሐዋርያትን ሥራ የሚገልጽም ነው። እንግዲህ በዚህ የትንቢት መጽሐፍ ማለቱ ለዮሐንስ ራእይ ብቻ የተነገረ መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው። ምክንያቱም ዮሐንስ ያየው ራእይ ሙሉ ለሙሉ ማለት ይቻላል መጭውን ጊዜ የሚገልጽ ነው።

## የግዝቱ ምክንያት

በዮሐንስ ራእይ መደምደሚያ ላይ የሠፈረው ግዝታዊ ቃል የተጻፈበት የራሱ የሆነ ምክንያት አለው።

ዮሐንስ በኤፌሶን የምሥራቹን ቃል (ወንጌልን) በማስተማሩ የተነሣ ወደ ደሴተ ፍጥሞ ይጋዛል። በዚያም ብቻውን ሳለ ወንድሞቹ ሁሉ በየሀገረ ስብከታቸው ጸንተው ያስተምራሉ የእኔ ማስተማር ፈቃድህ ባይሆን ነው ብሎ ወደ ፈጣሪው ቢያመለክት የበለጠ ጸጋ ተሰጥቶት የጥጦስ፣ የሐሳዊ መሢሕ፣ የምጽአት ነገር ተገልጾለት ጽፏል። ጌታ ጥቂት ሲሹ ብዙ መግለጥ ልማዱ ነውና። «ሐዲስ ሰማይና ሐዲስ ምድርም አየሁ» በማለት የመንግሥተ ሰማይ ነገር ተገልጾለት ጽፏል። ይህንንም መጭውን ጊዜ የሚያመለክታቸውን ትንቢታዊ ቃል የሠፈረበትን ጽሑፍ ለሰባቱ መንፈሳውያን ከዋክብት



(ኤጲስ ቆጶሳት) ሰዶላቸው እንደዚሁም የዚሁን ራእይ ሌላ ግልባጭ (ኮፒ) ለሐዋርያት ሰዶላቸዋል። ሐዋርያትም ከሰማንያ አሐዱ (81) መጽሐፍ አንዱ ራእየ ዮሐንስ ነው ብለው ለቀሌምንጦስ (የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር ነው) ሰደውለታል (ሰጥተውታል) ይህም ሲነበብ ሲተረጐም ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ዘመን ኑሯል።

በሁለት መቶ ሰባ ስድስት ዘመን ዲዮቅልጥያኖስ መክስምያኖስ የሚባሉ ሁለት አላውያን (ከሀዲያን) ነገሥታት ተነሥተው «አብያተ ክርስቲያናት ይዘጉ ይጥፉ የጣዖት ቤቶች ይከፈቱ ይሠሩ» ብለው አዋጅ አወጁ በአዋጁ መሠረት ብዙ ቤተክርስቲያናት በእሳት ተተኮሱ ፈረሱ። ክርስቲያኖችም እንደ በግ ታረዱ ሰውነታቸው እንደ ሸንኩርት ተቀረደደ ደማቸው እንደ ውኃ ፈሰሰ ቅዱሳት መጻሕፍትም ፈለሱ። ክርስቲያኖች እኛ ብናልፍ ሌላ ይተካል መጻሕፍቶቻችን ግን መተኪያ የላቸውም በማለት ቅዱሳት መጻሕፍትን ይዘው በየዋሻው በየፍርክታው ተንከዋረሩ። የቤተክርስቲያንን መፈተንዋን እንጂ መጥፋትዋን የማይሻ ጌታ ዘመነ ድዮቅልጥያኖስን አሳልፎ ደገኛ ዘመን አመጣ መፍቀሬ ሃይማኖት ቈስጠንጢኖስ በሮም ነገሠ እርሱም የዲዮቅልጥያኖስን አዋጅ በአዲስ አዋጅ ሻረው «አብያተ ክርስቲያናት ይከፈቱ ይታነጹ የጣዖታት ቤት ይዘጉ ይፍረሱ መጻሕፍት ከፈለሱበት ቦታ ይፈለጉ» አለ በዚህን ጊዜ በየዋሻው ሲንከራተቱ የነበሩ ክርስቲያኖች መጻሕፍቶቻቸውን ይዘው ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ።

በ325 ዓ.ም አርዮስ የተባለ መናፍቅ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የክህደት ትምህርት በማስተማሩ ኒቂያ በተባለችው ቦታ ጉባኤ ተካሄደ ከየዓለማቱ የተሰበሰቡት የሃይማኖት አባቶች 318 ሊቃውንት (ሠለስቱ ምዕት) የአርዮስን ክህደት አውግዘው ሃይማኖት መልሰው/አቅንተው በሚለያዩበት ጊዜ ለመጻሕፍቱ ሁሉ አርእስት ሰጥተዋል በዚህ ጊዜ ራእየ ዮሐንስን አጥተውታል። ከሰማንያ አሐዱ መጻሕፍት አንዱ ራእየ ዮሐንስ ነበር ጠፋ ብለው በአርእስት ጽፈውታል በምን አውቀው ቢሉ ሐዋርያት በአርእስት ጽፈውት አግኝተው። በሌላ በኩል ከሐዋርያት ሲያያዙ የመጡ እነ አቡሊዲስ እነ ዲዮናስዮስ ነግረዋቸው።

ይህ በሆነ በመቶ አምሳ ዘመን ዮሐንስ አፈወርቅ በቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስነት ተሾመ። ንጉሡ አርቃድዮስ ይባላል ንግሥቲቱም አውዶክስያ ትባላለች። ይህቺ ንግሥት በገንዘብ ፍቅር ልቡናዋ የነደደ የድሆችን ኃብት የምትነጥቅ የስስት ጾር ልብዋን ቀስፎ የያዛት ሴት ነበረች።

አንድ ቀን የአንዲትን ደኃ ሴት ርስትዋን ቀማቻት። ይህችም ድሃ ወደ ዮሐንስ አፈወርቅ (ሊቀ ጳጳስ ነውና) ሄዳ ንግሥቲቱ ርስቴን ቀማችኝ ብላ ትነግረዋለች። እርሱም ለወንጌል ያደረ ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሊቀ ጳጳስ ነበርና ወዲያው ተነስቶ ወደ ቤተመንግሥት ያመራል። ንግሥቲቱንም ባገኛት ጊዜ «የድሀዋን ርስት ለምን ቀማሻት መልሽላት» ይላታል ንግሥቲቱም «እንዲሁ አልቀማሁአትም ምትኩን ሰጥቻት ነው» አለች ዮሐንስ አፈወርቅም ወደ ድኃዋ ፊቱን መልሶ እውነት ነው ወይ? ብሎ ይጠይቃታል። የእኔ ርስት ለከተማ አቅራቢያ ነው በዚያውም ላይ ከዓመት ሦስት ጊዜ ያፈራል ልጆቼን ርስት ነቅያቸው አልሞትም» አለችው እርሱም ወደ ንግሥቲቱ ፊቱን መልሶ ፈቃደኛ አይደለችም ያለውዴታዋ በግድ በኃይልሽ (በሥልጣንሽ) ተጠቅመሽ ይህን ልታደርጊ አትችይምና መልሽላት አላት።

በዚህን ጊዜ አውዶክስያ ፊትዋ ተለዋወጠ አራስ ነብርም ሆነች ሃገሩን የምንገዛውኮ እኛ ነን የወደድነውን የፈቀድነውን ልናደርግ መብት አለን አንተን እዚህ ውስጥ የሚያገባህ የለም ብላ በቁጣ ቃል ተናገረች እርሱም «እንግዲያውስ ቤተ ክርስቲያን እንዳትገቢ ከምእመናን አትገናኝ ሥጋውን ደሙን አትቀበይ» ብሎ አወገዛት።

ቆጵሮስ ወዳለው ወደ ኤጲፋንዮስ ዘንድ መልእክት ልካ ኤጲፋንዮስን ታስመጣና «ተመልከት ዮሐንስ አፈወርቅ የሚያደርገውን እያውቅ ለአንዲት ድሀ ብሎ በማይገባ ነገር አወገዘኝ እንግዲህ ያለፈውን የዲዮቅልጥያኖስን ዘመን እንዲመለስ ላደርግ ነው» አለችው ይህ አባት ወደ ዮሐንስ አፈወርቅ በመሄድ «ወንድሜ ለምን አወገዝሃት ሰውኮ በአንድ ጊዜ በምግባር ፍጹም ሊሆን አይችልም እያደረ ነው የሚስተካከለው። በዚህም ላይ ደግሞ ጣዖት አቆማለሁ ያን የቀደመ የመከራ ዘመን መልሼ አመጣዋለሁ በማለት እየዛተች ነውና በምክር ብናደርገው ከግዝትዋ ብትፈታት ጥሩ



ይመስለኛል አለው። ክርስቲያኖች እሮይ ብለው ሳለ ተመልሶ መከራ ሊመጣባቸው ትወዳለህ?» ብሎ ሊያግባባው ሞከረ። ዮሐንስ አፈወርቅም ንግሥቲቱ ራስዋን ከእግዚአብሔር በላይ አድርጋ ሰሪ አድራጊ ፈጣሪ ሆና መታየትዋ ስላናደደው «ጣዖት ብታቆም ለራስዋ ይባስት እሷ በገሃነም ስትቃጠል ትኖራለች ጌታም ሁሉም በየርስቱ ይኑር ብሏል ስለዚህ የድኃይቱን ርስት ካልመለሰችላት በፍጹም ከግዝትዋ አልፈታትም ይላል።

በዚህ ጊዜ አውዶክስያ በዮሐንስ አፈወርቅ ላይ የነገር መረብዋን መተብተብ ጀመረች ዮሐንስ አፈወርቅ በጥፋታቸው ከስልጣናቸው የሻራቸው ስምንት ኤጲስ ቆጶሳት ነበሩና እነርሱን ሰብስባ ፍረዱኝ አለቻቸው እነርሱም አድርባዮችና በዮሐንስ አፈወርቅ ላይም ጥላቻ ስለነበራቸው «ንጉሠ ነግሥት ሲዘልፍ የማያፍር እንደበት ይጋዝ በቃ» ብለው ፈረዱበት። እርሷዋም አሳስራ ደሴተ አጥራክያ ወደምትባል ደሴት አግዛዋለች።

ዮሐንስ አፈወርቅ መጻሕፍት መመልከትን የሚያዘወትር ነበርና በደሴቱ ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት ሲያገላብጥ ሲያነብ የዮሐንስ ራእይን አግኝቶታል ወደዚህ ደሴት እንዴት ሊገባ ቻለ? ለሚለው ጥያቄ የተሰጠው መልስ በዲዮቅልጥያኖስ ጊዜ መጻሕፍት በፈለሱ ጊዜ ክርስቲያኖች ወደዚህ ደሴት አግብተውታል የሚል አመለካከት አለ። በሀገራችን በግራኝ አህመድ ወረራ ጊዜ መጸሕፍት ዳጋ በተባለው በጣና በሚገኘው ደሴት እንዲሁም ዝዋይ ባለው ደሴት ገብተው እንደ ነበር ማለት ነው።

አንዳንዶቹ አባቶች ደግሞ ይህ ዮሐንስ አፈወርቅ በደሴት ሳለ ከሰማንያ አሐዱ አንዱ የዮሐንስ ራእይ ሆኖ ሳለ መጥፋቱ ከልብ ያሳዝነው ስለነበር ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ቢያመለክት ንባቡ ከነትርጓሜው ተገልጾለት ጽፏል በዚህም ሐዲስ ዳንኤል ተብሏል። ዳንኤል የናቡከደነጾር ሕልም ከነትርጓሜው ተገልጾለት እንደ ተናገረ።

ያም ሆነ ይህ የጠፋው የዮሐንስ ራእይ በዮሐንስ አፈወርቅ በመገኘቱ ይህ ሊቀ ጳጳስ በፍጻሜው ላይ አንድ ማስጠንቀቂያ ማስፈር እንዳለበት ስለተረዳ። በራእይ መጽሐፍ መደምደሚያ ላይ እንዲህ የሚለውን የግዝት ቃል አስተላለፈ።

ዮሐንስ ወንጌላዊ ያየው ጥቂት ነበር አሁን ዮሐንስ አፈወርቅ ጨምሮበታል ብሎ ከዚህ መጽሐፍ አንዲት ቃል የሚያጐድል ቢኖር እግዚአብሔር በልጅነት ከሚገኝ ክብር ዕድል ፈንታውን ጽዋ ተራውን ያጐድልበታል። እንዲከፍልበትም እኔ ምስክሩ ነኝ ምክንያቱም ዮሐንስ ወንጌላዊ ካየው ውጭ የጨመርኩበት የለምና። እንዲሁም ዮሐንስ አፈወርቅ ያየው ብዙ ነበረ የኋላ ሰዎች ከፍለውታል ብሎ የሚጨምር ቢኖር የቀረ አለ ብሎ የሚጨምር የተጨመረ አለ ብሎ የሚቀንስ ወዮለት።

የሚለውን ግዝታዊ ቃል አስፍሯል ይህን ያደረገበትም ምክንያት በአጉል መራቀቅ በኋላ የሚነሱ አንዳንድ ሰዎች ዮሐንስ ወንጌላዊው ባየው ራእይ ላይ እንዲህ የሚል ነበር። ዮሐንስ አፈወርቅ አገኘው በተባለው መጽሐፍ ላይ ግን ይህ የለም። ስለዚህ መጨመር አለበት ብለው እንዳይጨምሩ የተጨመረም አለ ብለው እንዳይቀንሱበት ትክክለኛው የዮሐንስ ወንጌላዊ ራእይ መሆኑን ያልተጨመረበት ያልተቀነሰበት መሆኑን ሊያረጋግጥ ብሎ ነው።

«እጅግ የተወደድህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ መድኃኒታችን አለኝታችን፤ ኃይላችን መሆንህን የሚያስተምሩንን የሚያሳውቁንን በድቅድቅ ጨለማም እንዳንጓዝ የዚህ ዓለም ብርሃን ሆነው መንገድህን የሚያሳዩን ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብ ምሥጢራቸው እንዲረዳንና ከስህተት ዳጥ እንዳንወድቅ ትጠብቀን ዘንድ አንተን በወለደች በቅድስተ ቅዱሳን በንጽህት ቅድስት ድንግል ማርያም ስም እንለምንሃለን። የጸጋ ሁሉ ምንጭ+ አንተ ብቻ ነህና ጸጋህን አጐናጽፈን በምሕረትህ አድነን አሜን»



## ምዕራፍ ሁለት

# ምሥጢረ ሥላሴ

ሥላሴ ማለት ሦስትነት ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክ አንድ ሲሆን ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ ነው። የእግዚአብሔር ነገር ከፍጡራን ህሊና በላይ በመሆኑ ስለ እርሱ ባሕርይ (Essence) ስንናገር ከስነፍጥረት ህግ ጋር አንድ አድርገን ወይም ከእኛ እውቀት ጋር አነጻጽረን ልንናገር አንችልም። አንዳንድ ሰዎች በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በሌላው አማኝ ህሊና ላይ ለመቅረጽና ከዚህ የድኅነት መንገድ ለማስወጣት የሰው አእምሮ በሂደት ካገኘው የቁጥር ስልት (Mathematical Logic) ጋር ለማነጻጸር ሲሞክሩ ይታያሉ። በሒሳብ ሕግ የእግዚአብሔርን ህልውና ልንረዳም ሆነ ልንገነዘብ ያስቸግራል ምክንያቱም የሒሳብን ሕግ የፈጠረው የሰው አእምሮ ነው የሰውን አእምሮ የፈጠረው ደግሞ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ከሰው አእምሮ በላይ ነው። ዳሩ ግን ይህ ገናና አምላክ ኢምንት የሆነው የሰው ፍጥረት ማንነቱን እንዲያውቅ እንዲረዳ ከመሻቱ የተነሣ ማንነቱን በተለያየ ሁኔታ ሲገልጥለት መኖሩ በቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኝ እውነት ነው።

እንግዲህ እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው፤ ይህ የእግዚአ ብሔር ሦስትነት ልዩ ሦስትነት ነው። ሦስት ብቻ ተብሎ አይቆምምና ሦስት ሲሆን አንድም ነው። ስለዚህ የፍጥረታት ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ የአንድነትና የሦስትነት ባለቤት በመሆኑ ሥላሴ ይባላል። የአንጾኪያ ሊቀጳጳስ ቅዱስ ባስልዮስ ሲያስተምር «እኔስ እግዚአብሔር ባልኩ ጊዜ የምናገረው ስለ አብ ስለ ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ ነው» ብሎ መስክሯል።

እኛም እንግዲህ በእግዚአብሔር መንፈስ ተቃኝተ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርገ ቅዱስ ባስልዮስ የተናገረውን ቃል በመያዝ እግዚአብሔር ስንል ሥላሴ ሥላሴ ስንል እግዚአብሔር ማለታችን እንደሆነ ልንገልጽ እንወዳለን። ይህም ትምህርት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋትና በምልዓት ተጽፎ የምናገኘው መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ነው።

## አንድነት በሦስትነት፣ ሦስትነት በአንድነት እንዴት?

እግዚአብሔርን አንድ ነው ስንል በመለኮት በባሕርይ በአገዛዝ በሥልጣን ይህን ዓለም በማፍጠርና በማሳለፍ በመሣሠሉት ነው።

መጻሕፍት እግዚአብሔር በመለኮቱ አንድ መሆኑን ሲመሰክሩ «እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍፁም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ» ዘዳ.6፥4።

በማለት የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ አንድ መሆን ይገልጻሉ። እግዚአብሔር አምላክህ አንድ እግዚአብሔር ነው ሲል ሦስትነት የለውም ማለቱ አለመሆኑን መጻሕፍት በየቦታው የሚመሰክሩት በመሆኑ በሚቀጥሉት አንቀጾች የሚገለጽ ነው።

ፍጥረታትን የፈጠረ በመለኮት አንድ የሆነ እግዚአብሔር መሆኑን መጻሕፍት ይናገራሉ «እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ...» ዘፍ.1፥1–26። «አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትኽ ሰማያትም የእጅህ ሥራዎች ናቸው» መዝ.101፥25። «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድር ነው እነዚህን ሁሉ እጇ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው» ኢሳ.66፥1።

ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ባህርይ አንድ መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው። ለፍጥረት ሁሉ ፈጣሪው አንድ ነው እንጂ ሁለት ወይም ሦስት አይደለም። ሦስት ፈጣሪዎች ቢኖሩማ ኖሮ ሥነ ፍጥረቱ ሁሉ ያማረ የተዋበ ባልሆነ ነበር እንደዚሁም እርስ በርሱ ተጠፋፍቶ ባለቀ ነበር። ዳሩ ግን የሁሉ ፈጣሪ አንድ መለኮት በመሆኑ ሁሉም ሥርዓትንና ሕግን ጠብቀው ሲኖሩ እናያለን።

ከመነሻችን እግዚአብሔር የአንድነትና የሦስትነት ባለቤት መሆኑን ገልጸናል። አንድ ነው ስንል እንግዲህ በቅዱስ መጽሐፍ



እንደተገለጸው ሁሉ በመለኮት፥ በሕልውና «እኔና አብ አንድ ነን» ዮሐ.ወን.14፥10። ባለው መሠረት ነው በአገዛዝ በሥልጣን ይህን በመሳሰለው ሁሉ እግዚአብሔር አንድ ነው።

የእግዚአብሔር አንድነቱን በዚህ ዓይነት መልኩ ከተረዳንና ከተገነዘብን የሦስትነትን ነገር ወደ መመልከት እንገባለን። የብዙዎቹ ችግር የእግዚአብሔርን ልዩ ሦስትነት ያለመረዳት ነውና።

## ልዩ ሦስትነት

እግዚአብሔር በመለኮት በህልውና አንድ ሲሆን ዳሩ ግን በአካል፥ በስም፥ በግብር ሦስት ነው።

አካል:- ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ ያለውን ያመለክታል። ገጽን መልክዕን አቋምን ያሳያል።

ሀ. ገጽ ሲል ልብስ የማይሸፍነውን ከንገት በላይ ያለውን መገለጫ መታወቂያን ግንባርን ያመለክታል።

ስለዚህ የሰው መታወቂያው መገለጫው ከንገቱ በላይ ያለ ፊቱና ግንባሩ ስለኾነ አንድ ሰው ፊቱን ቢሸፍን ወይም ከንገቱ ላይ ተቆርጦ ከንገት በላይ ያለው አካል ቢጠፋና ከንገቱ በታች ያለው አካል በሙሉ ቢታይ ማን እንደኾነ ሊታወቅ አይችልም። የገጽ ትርጓሜ መገለጫ መታወቂያ ማለት ነው።

ለ. መልክዕ በምንልበት ጊዜ ቀይ ጥቁር የሚለው ይከተለዋል። ኀብርን መልካም ክፉ ማለት ሲከተለው ደግሞ ቅርፅን ደም ግባትን ያመለክታል። ይኸውም ቀይ መልክ ጥቁር መልክ ወይም መልከ መልካም፥ መልከ ክፉ እንደማለት ነው።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ኹሉ የአካልን ስልት ስልቱን የሚያሳዩ አነጋገሮች ናቸው እንጂ ሌላ አይደሉም አካል በመባል ይጠቃለላሉ።

ስም:- ስም የሚለው ግን ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር ያለው ያንድ ሰው አካል ከሌላው ሰው አካል ተለይቶ ማን እንደኾነ ታውቆ የሚጠራበት ነገር ነው እንጂ ራሱ አካል አይደለም።

ለምሳሌ አዳም፥ ሴት፥ ኖኅ፥ አብርሃም እንደማለት ነው ይህ የተጸውዖ ስም ይባላል። ደግሞ ከዚህ ሌላ የአካል የግብር ስም አለ።

የአካል ስም :- ሲባል ሰው፥ ላም፥ ፈረስ፥ በግ፥ አንበሳ እንደ ማለት ነው ሰውም ላምም በግም ፈረስም አንበሳም ቢኾኑ ይህን ስም የሚያገኙት አካል ሲገኝ ነው እንጂ ኖረው ኖረው የሚያገኙት አይደለምና። ስለዚህ ይህን የመሳሰለው የአካል ስም ይባላል።

የግብር ስም :- ሲባል የሥራቸውን ጠባይ የሚገልጽ ነው። ሥዕል የሚሥለው ሠአሊ የሚጽፈው ጸሐፊ የሚነግደው ነጋዴ የሚያርሰው ገበሬ የሚያስተምረው አስተማሪ ሥራውን ቢተው ግን ነበረ ከመባል በቀር በዚህ ስም ሊጠራበት አይችልም። ለምሳሌ ቀድሞ ገበሬ የነበረ አሁን ግን ግብርናውን ፈጽሞ የተወን ሰው ገበሬ ነበር ይባላል እንጂ ገበሬ ነው አይባልም። ስለዚህ ይህን የመሳሰለው ስም የግብር ስም ይባላል።

ከላይ እንደተዘረዘረው ኹሉ ለአብ ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ አለው ለወልድም ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ አለው ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ ፍጹም አካል አለው።

በዚህ ሥላሴ ፍጹም ሦስት ናቸው። አንድ ሰው የራሱ የሆነ አካል እንዳለው ሁሉ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስም የራሳቸው የሆነ ፍጹም አካል አላቸው።

ለሥላሴ የአካል ስም፣ የአካል ግብር ስም፤ አካላት በህልውና የሚገናዘቡበት የባሕርይ ከዊን ስም አላቸው።

የአካል ስም :- የአካል ስም ማለት አብ፣ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ነው። ሰው ሰው መባልን የሚያገኘው አካሉ ሲገኝ እንደኾነ ሁሉ እንደዚሁም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚባለው ስም ምንም እንኳን ሥላሴ በዚህ ጊዜ ተገኙ የሚባልበት ጊዜ ባይኖር፥ ጥንት መሠረት ሳይኖረው ቅድመ ዓለም ሲኖር የኖረ ነው እንጂ እንደ ተጸውዖ ስም ኖሮ ኖሮ የወጣ ስም አይደለም።



ወይም ሰው ኖሮ ኖሮ ልጅ ሲወልድ አባት እንዲባል አብም ከወልድ ቀድሞ ኖሮ ኖሮ ወልድን ወልዶ አብ የተባለ አይደለም። ወልድም ልጅ ካባቱ በዘመን ወደ ኋላ ኾኖ ኖሮ ኖሮ በእናቱ ማኅፀን ተጥሎ ፅንስ ሽል ሲባል ኖሮ ከ9 ወር በኋላ ሲወለድ ልጅ እንዲባል ከአብ በዘመን ወደኋላ ኾኖ ኖሮ ኖሮ ተወልዶ ወልድ የተባለ አይደለም። የመንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ።

የአካል ግብር ስም :- ወላዲ፥ ተወላዲ፥ ሠራጺ ማለት የአካል ግብር ስም ነው። የአካል ግብር ስም ማለትም አብ ወልድን ቢወልድ መንፈስ ቅዱስን ቢያሠርፅ (ቢያወጣ) ወላዲ አሥራጺ ተባለ። ወልድም ከአብ ቢወለድ ተወላዲ ተባለ። መንፈስ ቅዱስም ከአብ ቢሠርፅ ሠራጺ ተባለ ማለት ነው። አብ ተለውጦ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንዳይኾን እንዳይባል ወልድም ተለውጦ አብ መንፈስ ቅዱስ እንዳይኾን እንዳይባል መንፈስ ቅዱስም ተለውጦ አብ ወልድ እንዳይኾን እንዳይባል ወላዲነት፥ አሥራጺነትም ከአብ ወጥቶ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ተወላዲነትም ከወልድ ወጥቶ በአብ በመንፈስ ቅዱስ ሠራጺነትም ከመንፈስ ቅዱስ ወጥቶ በአብ በወልድ የሚሠራ ግብር አይደለም ስለዚህ ይህ ስም ሦስቱ የሚለያዩበት ነው እንጂ የሚገናዘቡበት ወይም አንድ የሚኾኑበት ስም አይደለም።

የባሕርይ ከዊን ስም :- አካላት በህልውና የሚገናዘቡበት የባሕርይ ከዊን ስም አላቸው። የባሕርይ ከዊን ስም የምንለው ልብ፥ ቃል እስትንፋስ፥ መባል ነው። ይኸውም ተከፍሎ (መከፈል) ተፈልጦ (መለያየት) በሌለበት ባንዲት ባሕርይ ያለ የከዊን (የሁኔታ) ስም ነው። እርሱም ልዩነት ሳለበት አንድነት፥ አንድነት ሳለበት ልዩነት አለበት። ልዩነቱ በከዊን (ሁኔታ) ሲሆን፥ አንድነቱ በህልውና መገናዘብ ነው። ይህንንም በነፍስ ሁኔታ (አኳኋን) ልንረዳውና ልንገነዘበው እንችላለን።

ነፍስ በአካሏ አንድ ስትኾን ሦስት ከዊን አላት ይኸውም ልብ ቃል እስትንፋስ መሆን ነው። የልብነቷ ከዊን (ሁኔታ) ቃልን እስትንፋስን አስገኝቶ እውቀት ይኾናል የቃልነቷ ከዊን ከልብነቷ ከዊን ተገኝቶ ከሥጋ ምላስ ጋር ተዋሕዶ ንባብን ይሰጣል፥ የእስትንፋስነቷ ከዊን ከልብ መንጭቶ ዐየርን በማውጣት በማግባት ሕይወት ይኾናል።

የሥላሴም ከዊን እንደዚሁ ነው አንዲት የምትኾን ባሕርየ መለኮት ሦስት ከዊን ስላሏት የልብነቷ ከዊን አብ ነው:- አብ በልብነቱ ቃል የተባለ ወልድን እስትንፋስ የተባለ መንፈስ ቅዱስን አስገኝቶ ለራሱና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ እውቀት ይኾናል። የቃልነቷ ከዊንም ወልድ ነው። ወልድ በቃልነቱ ከዊን ልብ ከተባለ ከአብ ተወልዶ ለራሱና ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ ይኾናል።

የእስትንፋስነቷ ከዊንም መንፈስ ቅዱስ ነው መንፈስ ቅዱስ በእስትንፋስነቱ ከዊን ልብ ከተባለ ከአብ ሠርፆ (ወጥቶ) ለራሱና ለአብ ለወልድ ሕይወት መኾን ነው። የነፍስ የልብነቷ ከዊን በልብነቱ የቃልነቷም ከዊን በቃልነቱ የእስትንፋስነቷ ከዊን በእስትንፋስነቱ ጸንቶ ከመኖር በቀር የልብነቷ ከዊን ወደ እስትንፋስነት ወደ ቃልነት፥ የቃልነቷም ከዊን ወደ ልብነት ወደ እስትንፋስነት የእስትንፋስነቷም ከዊን ወደ ልብነት ወደ ቃልነት እንደማይለወጥ እንደማይቀላቀል ያንዲት ባሕርየ መለኮት ከዊንም እንደዚሁ የልብነቷ ከዊን በአብ የቃልነቷ ከዊን በወልድ የእስትንፋስነቷ ከዊን በመንፈስ ቅዱስ ጸንቶ ይኖራል እንጂ አይለወጥም አይቀላቀልም።

የከዊን ሦስትነት አንድነት ሳለበት ልዩነት አለበት መባሉ ለዚህ ነው ሁለተኛም ቃል፥ እስትንፋስ ከልብ ቢገኙም ተከፍሎ ተፈልጦ ሳይኖርባቸው ከልብ ሳይለዩ ህልዋን ኾነው እንዲኖሩ ወልድና መንፈስ ቅዱስም በቃልነትና በእስትንፋስነት ከዊን በልብነት ከዊን ካለ ከአብ ቢገኙ ተከፍሎ ተፈልጦ ሳይኖርባቸው በአብ ህልዋን ኾነው ይኖራሉ እንጂ ተከፍሎ ተፈልጦ (መለያየት) የለባቸውም ሥላሴ በህልውና አንድ ናቸው የሚያሰኘው ምሥጢር ይህ ነው።

ከላይ የተዘረዘረውን አጠር መጠን ባለ ሁኔታ ለመግለጽ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ባሕርይ በህልውና በመፍጠር በስልጣን አንድ ነው።

በስ፡ም በግብር በአካል ሦስት ነው:—

በስም — አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ይባላል ማቴ 28፥19።

በአካል — ለአብ የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ፍጹም አካል አለው ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስም እንዲሁ።



በግብር:- አብ ወላዲ (አባት)፣ ወልድ ተወላዲ (ልጅ) መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ (የወጣ)

አብ ወልድን ቢወልድ መንፈስ ቅዱስን ቢያሠርጽ እንጂ አይወለድም አይሠርጽም (አይወጣም) ወልድም ቢወለድ እንጂ አይወልድም አያሠርጽም አይሠርጽም መንፈስ ቅዱስም ቢሠርጽ እንጂ አይወልድም አይወለድም አያሠርጽም።

## የሥላሴ ምሳሌ

በመሠረቱ ምሳሌ ከሚመስልለት ነገር እንደሚያንስ በሁሉም ዘንድ የታወቀ በመሆኑ ለሥላሴ ምሳሌ አድርገን ከስነ ፍጥረት የምናቀርባቸው ሁሉ ፍጹም የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት ይገልጣሉ ለማለት ሳይሆን መጠነኛ ግንዛቤ ይሰጣሉ በማለት ነው አስቀድመን ይህን ካስገነዘብን አበው ለምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ አድርገው ያቀረቡአቸውን ለመግለጽ እንወዳለን።

### 1ኛ. ሥላሴ በነፍስ ይመስላሉ

ለሥላሴ ምሳሌነት ከሰው ነፍስ የበለጠ ምሳሌ አይገኝም ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ ሰውን በመልኩና በአርአያው መፍጠሩን ገልጾአልና ሰው እግዚአብሔርን የሚመስለው በነፍሱ ነው። ዘፍ.1፥26።

ነፍስ በአካልዋ አንድ ስትኾን በኪዊን (በሁኔታ) ሦስት ናት። ይኸውም ልብ መኾን፣ ቃል መኾን እስትንፋስ መኾን ነው። ልብ ቃል እሳት ንፋስ የነፍስ ባሕርያት ናቸው። ነፍስ በአካልዋ አንድ ስትሆን ሦስት ባሕርያት አሉአት። የነፍስ አካልዋ አንድ እንደሆነ ሁሉ ሥላሴም በመለኮት ብባሕርይ በሕልውና አንድ ናቸው። አካልዋ አንድ የሆነ ነፍስ ሦስት ከዊን እንዳላት ሁሉ ሥላሴም በመለኮት አንድ ሲሆኑ በአካላት ሦስት ናቸው።

ነፍስ በአካሏ ከሦስት የማትከፈል አንዲት ስትኾን በባሕርይዋ እንደ ሥላሴ ሦስት ከዊን አላት። በባሕርይዋ ያለ ሦስት ከዊን አካሏን

ከሦስት እንደማይከፈለው ሁሉ በሥላሴ ባሕርይ ያለ ሦስት ከዊንም ባሕርየ ሥላሴን፥ መለኮተ ሥላሴን ከሦስት አይከፍለውም።

በባሕርይዋ ሦስት ኪዊን (ሁኔታ) ያላት ነፍስ (ሦስት የነፍስ ከዊን ከላይ የተጠቀሱት ልብነት፣ ቃልነት፣ ሕይወትነት ናቸው)። አንዲት ብትባል እንጂ ሦስት እንደማትባል ሁሉ ሦስት ከዊን ያላት መለኮተ ሥላሴ ባሕርየ ሥላሴም አንዲት ብትባል እንጂ ሦስት አትባልም።

በልብነቷ አብ በቃልነቷ ወልድ በእስትንፋስነቷ መንፈስ ቅዱስ ይመስላል ልብነቷ ቃልነትን እስትንፋስነትን ያስገኛል እንጂ ቃልነቷ ወይም እስትንፋስነቷ ልብነቷን አያስገኝም።

እንደዚኸውም ቃልነቷ እስትንፋስነትዋን እስትንፋስነትዋ ቃልነትዋን ሊያስገኝ አይችልም። እንዲሁም ማለት ቃል እስትንፋስ ከልብ ይመነጫል እንጂ ልብ ከቃል ከእስትንፋስ አይገኝም ቃልም እስትንፋስን እስትንፋስ ቃልን ሊያስገኝ አይችልም ማለት ነው።

እንደዚኸውም በቃል የተመሰለ ወልድ በእስትንፋስ የተመሰለ መንፈስ ቅዱስ በልብ ከተመሰለ ከአብ ይገኛሉ እንጂ አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ አይገኝም። በቃል የተመሰለ ወልድም በእስትንፋስ የተመሰለ መንፈስ ቅዱስን አያስገኝም። በእስትንፋስ የተመሰለ መንፈስ ቅዱስም በቃል የተመሰለ ወልድን አያስገኝም። መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ይሠርፃል ማለት እስትንፋስ ከቃል ይመነጫል እንደ ማለት ነውና። መንፈስ ቅዱስን ከወልድም ይሠርፃል (ይወጣል) የሚሉ እጅግ በጣም መሳሳታቸውን ሊያውቁ ይገባል ጌታም መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሚሠርጽ መሆኑን ተናግሯል። ዮሐ.15፥26።

## ሥላሴ በቅድምና እኩል ናቸው

አንዳንድ ሰዎች አብን ቀዳሚ ወልድን ተከታይ መንፈስ ቅዱስን ሠላሽ አድርገው የሚያቀርቡ አሉ። ይህ ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው። ሥላሴ በቅድምና አንድ ናቸው። ይህንንም ከላይ በመሰልነው በነፍስ ምሳሌነት ማየት ይቻላል።

ልብ ከቃል ከእስትንፋስ ጋር ባንድነት አንድ ጊዜ ይገኛል እንጂ ከቃል ከእስትንፋስ ቀድሞ መገኘት የለበትም ቃልም ከእስትንፋስ



ከልብ፥ እስትንፋስም ከልብ ከቃል ቀድሞ መገኘት የለባቸውም እንደዚኸውም አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ቀድሞ የተገኘበት ጊዜ የለም ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ አይቀድምም ቀድሞ የተገኘበት ጊዜ የለም ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ አይቀድምም መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ወደኋላ አይኾንም።

## 2ኛ. ሥላሴ በፀሐይ ይመስላሉ

ለፀሐይ ክበብ፣ ብርሃን፣ ሙቀት አለው። በክበቡ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ። ክበቡ ሙቀትን ብርሃንን ያስገኛል እንጂ ብርሃን ሙቀትን ክበብን አያስገኝም ሙቀትም ክበብን ብርሃንን አያስገኝም።

እንደዚኸውም በክበብ የተመሰለ አብ በብርሃን የተመሰለ ወልድን በሙቀት የተመሰለ መንፈስ ቅዱስን ያስገኛል እንጂ በብርሃን በሙቀት የተመሰሉ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በክበቡ የተመሰለ አብን አያስገኙትም።

ብርሃን ሙቀትን፣ ሙቀት ብርሃንን ሊያስገኝ እንደማይችል መን ፈስ ቅዱስ ወልድን ወልድም መንፈስ ቅዱስን ሊያስገኝ አይችልም።

ክበብ ሲገኝ ብርሃን ሙቀት አብረው ይገኛሉ እንጂ ክበብ ቀድሞ ብርሃን ሙቀት ኋላ የሚገኙ አይደሉም።

እንደዚኸውም ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንደ አብ ቅድመ ዓለም ህልዋን ናቸው እንጂ አብ በዘመን ቀድሟቸው ኋላ የተገኙ አይደሉም። ክበበ ፀሐይ ብርሃንን ሙቀትን እየላከ መኖሩን ያስታውቃል እንጂ እንደ ብርሃን እንደ ሙቀት የሚላክ አይደለም።

እንደዚኸውም አብ ወልድን መንፈስ ቅዱስን እየላከ ህልውናውን ይገልጻል እንጂ ለማንም የታየና የተገለጸ አይደለም። ዮሐ.1፥18።

ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት አብን ላኪ ወልድን ተላኪ መንፈስ ቅዱስንም ተላኪ እያሉ ይነግሩናል እንጂ በክበብ በብርሃን በሙቀት መቅደም መቀዳደም መከተል መከታተል እንደሌለባቸው በሥላሴም መቅደም መቀዳደም መከተል መከታተል የለባቸውም።

እንግዲህ ፀሐይ አንድ ስትሆን ሦስት ነገሮች ስላሏት ሦስት ፀሐይ እንደ ማትባል ሁሉ ሥላሴም በመለኮት አንድ ሲሆኑ በአካላት ሦስት ናቸው ዳሩ ግን በአካላት ሦስት በመሆናቸው ሦስት አምልክ አይባሉም አንድ አምላክ እንጂ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ እንደተናገረ «አብ አምላክ ነው ወልድም አምላክ ነው መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው አንድ አምላክ እንላለን እንጂ ሦስት አማልክት አንልም።»

## 3ኛ. ሥላሴ በእሳት ይመሰላሉ

እሳት ሦስትነት አለው። ነበልባል፣ ዋዕይ (ሙቀት) ብርሃን። በነበልባሉ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ፣ በዋዕዩ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ። ነበልባል ብርሃንን ዋዕይን (ሙቀትን) ያስገኛል እንጂ ብርሃንና ዋዕይ ነበልባልን አያስገኙትም ወይም ብርሃን ዋዕይን ዋዕይ ብርሃንን አያስገኝም እንደዚኸውም በነበልባል የተመሰለ አብ በብርሃን የተመሰለ ወልድን በዋዕይ የተመሰለ መንፈስ ቅዱስን ያስገኛል እንጂ በብርሃን በዋዕይ የተመሰሉ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በነበልባል የተመሰለ አብን አያስገኙትም።

እንደዚኸውም ብርሃን ዋዕይን ዋዕይ ብርሃንን ሊያስገኝ እንደማይችል። በብርሃን የተመሰለ ወልድም በዋዕይ የተመሰለ መንፈስ ቅዱስን ወይም በዋዕይ የተመሰለ መንፈስ ቅድስ በብርሃን የተመሰለ ወልድን አያስገኝም።

ነበልባል ከብርሃን ከዋዕይ መቅደም መብለጥ እንደሌለበት ለብርሃንና ለዋዕይም ከነበልባል ማነስ ወይም ወደኋላ መኾን እንደሌለባቸው አብም ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ አይቀድምም አይበልጥም ወልድ መንፈስ ቅዱስም ከአብ አያንሱም በዘመን ወደኋላ አይሉም ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም መንፈስ ቅዱስም ከወልድ አያንስም በዘመን ወደኋላ አይልም።

አብ ላኪ ወልድ ተላኪ መንፈስ ቅዱስ ተላኪ በመባላቸውም ከላይ በፀሐይ ምሳሌነት እንደገለጥነው ነበልባል ብርሃኑን ፈንጥቆ ጨለማን በማራቁ፣ ዋዕዩን (መቀቱን) ልኮ በማሞቁ ህልውናውን (መኖሩን) እንዲያሳውቅ፣ የአብም ህልውናው በወልድ በመንፈስ



ቅዱስ ስለተገለጸ ነው እንጂ በሥላሴ መቅደም መቀዳደም መብለጥ መበላለጥ ኖሮባቸው አይደለም።

## 4ኛ. ሥላሴ በቀላይ (በባሕር) ይመሰላሉ

ባሕር ሦስት ነገሮች አሉት። እነዚህም ስፍሐት፣ ርጥበት፣ ሑከት (ማዕበል) ይባላሉ። ስፍሐቱ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ያለው ነው። ርጥበቱ ከውኃው ጋር ያለው ነው። ሑከት የተባለው የባሕሩ እንቅስቃሴ ነው።

በባሕሩ ስፍሐት አብ ይመሰላል፣ በባሕሩ ርጥበት ወልድ ይመሰላል፣ በባሕሩ ሁከት መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። ይህ ሦስት ከዊን (ሁኔታ) ያለው ባሕር አንድ ባሕር ይባላል እንጂ ሦስት ባሕር እንደማይባል ሁሉ ሦስት ከዊን ያላት ባሕርየ ሥላሴ መለኮተ ሥላሴም አንዲት ብትባል እንጂ ሦስት አትባልም። እንደዚሁም ሥላሴ በስም በአካል በግብር ሦስት ቢባል በመለኮታዊ ባሕርይ ግን አንድ ነው።

## 5ኛ. ሥላሴ በሦስት ማዕዘን ቅርጽ ይመሰላሉ

አስቀድመን እንደገለጽነው ሁሉ የምንመስላቸው ምሳሌዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በምናየውና በሚገባን አገላለጽ ለመግለጽና መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖረን ለማድረግ እንጂ እግዚአብሔርን ከስነ ፍጥረት ውስጥም ሆነ የሰው ሐሳብ ካመነጨው መካከል ፍጹም የሚመስለው የሚተካከለው ነገር የለም። ምንግዜም ምሳሌ ከሚመስልለት ነገር እንደሚያንስ ሊታወቅ ይገባል።

ሦስቱም ጐኖቹ አንድ አይነትና እኩል የሆኑ ሦስት ማዕዘን ቅርጽ መኖሩን በሒሳብ ትምህርት (ጂኦሜትሪ) ብዙዎቻችን የተማርነው ነው። በምሁራን አሰያየም (Equilateral Triangle) ይባላል። ሦስቱም ጐኖቹና ሦስቱም አንግሎቹ (Angle) እኩል የሆኑ ማለት ነው።

ሦስቱ ጐኖች በየራሳቸው የቆሙ ናቸው። ስያሜ ስጥተናቸው በስያሜአቸው መጠቀም እንችላለን።




ሦስቱ ጐኖች በርዝመት በውፍረት በማናቸውም ሁኔታ አንድ ናቸው ወይም እኩል ናቸው።

ሀ = ለ = ሐ

አንዱ ጐን ከሌሎቹ ጐኖች በማናቸውም አይነት ሁኔታ አይበልጥም አያንስም። ሁሉም ጐኖች በየራሳቸው የቆሙ ናቸው። ጐን ሀ የራሱ ጐን አለው ጐን ለ ና ጐን ሐ እንደዚሁ።

በማናቸውም ሁኔታ አንድ አይነት የሆኑት ሦስት ጐኖች ጫፍና ጫፋቸው ሲገናኙ ሦስቱም ጐኖቹ ሦስቱም አንግሎቹ እኩል የሆነ ሦስት ማዕዘን (Equilateral Triangle) ይገኛል።




ሀ = ለ = ሐ

1 = 2 = 3

የሀ ጐን ከሌሎች ጐኖች በአካል የተለየ መሆኑን አስተውል።

የ‹ለ› ጐንና የ‹ሐ›ን ጐን እንደዚሁ ሁሉም በየራሱ ጐን በመቆም አንድ ሦስት ማዕዘን ሠርተዋል።



## ምሳሌው ከእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ጋር ያለው ተመሳሳይነት

ከላይ በተጠቀሱት ሦስት ጐኖች አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ። ሦስቱ ጐኖች በየራሳቸው ጐን የቆሙ እንደሆን ሁሉ ሥላሴም በሦስት አካላት፣ በሦስት ገጻት ፍጹማን ናቸው። አብ የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ፍጹም አካል አለው። ወልድም የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ፍጹም አካል አለው። መንፈስ ቅዱስም የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ፍጹም አካል አለው። በሦስት ጐኖች መካከል የርዝመት፣ የውፍረት ልዩነት እንደሌለ በማናቸውም ነገር እኩል እንደሆኑ ሁሉ ሦስቱ ገጻት/ሥላሴ በክብር በብርሃን አንድ ናቸው። አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም ወልድም ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም መንፈስ ቅዱስም ከአብ ከወልድ አይበልጥም ሦስቱም በባህርይ አንድ ናቸው በሥልጣን አንድ ናቸው፣ በመመስገን አንድ ናቸው፣ በመለኮታዊ ማዕረግ አንዱ ከአንዱ አይበልጥም።




አብ = ከወልድ = ከመንፈስ ቅዱስ። ሦስቱ ፍጹማን አካላት አንድ እግዚአብሔር ይባላሉ። አንዱ አንዱን እንደ መልክተኛ በሥልጣኑ አያዝዘውም በአንድ መለኮት ክብር አገዛዝ የሁሉ ፈጣሪ ገንዘብ በሚኾን በባሕርይ ዕውቀት አንድ ናቸው።

ከሦስቱ ጐን አንዱ ከሌለ ሦስት ማዕዘን አይባልም እንደዚኹም ሁሉ ከሥላሴ አንዱን ፍጡር የሚል በአምላክ ህልውና ላይ ምን ያህል የክህደት ትምህርት እንዳስተማረ ከምሳሌው መገንዘብ ይቻላል።

የሦስቱ ማዕዘን ግራና ቀኝ የቱ ነው? ግራና ቀኙ እንደማይታወቅ እንደዚኹውም ለሥላሴ ቀኝና ግራ የላቸውም።

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደመሠከሩት «አልብነ ቀዳማዊ ወአልብነ ደኅራዊ አልብነ የማን ወአልብነ ፀጋም፤ አልብነ ጠፈር ወአልብነ መሠረት፤ ንሕነ ጠፈር ወንሕነ መሠረት»[1] ትርጓሜው «ተቀዳሚና ተከታይ ቀኝና ግራ የለብንም፤ ጠፈር የለብንም መሠረትም የለብንም ጠፈርም መሠረትም እኛው ነን»

## የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥክርነት

በዘመኑ ሕልፈት በመንግሥቱ ሽረት የሌለበት ልዑል ባሕርይ አምላካችን እግዚአብሔር የአንድነትና የሦስትነት ባለቤት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። የመጽሐፍ ቅዱስን ምሥጢር በአግባቡ ያልተረዱና ያልተገነዘቡ አንዳንዶች ከዚህ እምነት ውጭ ሆነው ይታያሉ።

እግዚአብሔር በአካል ሦስት በመለኮት አንድ መሆኑን ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የምታምነውና የምትመሠክረው መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድርጋ ነው።

የመጻሕፍትን ምሥክርነት እንደሚከተለው እንጠቅሳለን። ኦሪት ዘፍጥ 1፥26 «እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር» ከዚህ አባባል የምንረዳው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር በአካል አንድ ብቻ አለመሆኑን ነው። የአካልን ትርጉም ቀደም ብለን የገለጽን በመሆኑ እዚህ ላይ ማብራራቱ አስፈላጊ አይደለም።

እግዚአብሔርም አለ:- የሚለውን እንመልከት። እግዚአብሔር የሚለው ስም የገናናው አምላካችን መጠሪያ ስም ነው። ቃሉም የግዕዝ ቃል ነው ትርጉሙም በሁለት ወገን ይተረጐማል።

1ኛ. የአምላክን አንድነት ያመለክታል። እግዚአብሔር የሚለውን ቃል ለሁለት ስንከፍለው እግዚአ – ብሔር የሚሉትን ቃላት እናገኛለን። እግዚአ የሚለው ግዕዛዊ ቃል የአማርኛ ትርጉሙ ጌታ ማለት ነው። ሁለተኛው ቃል ብሔር የሚለው ሀገር ወይም ዓለም

[1] ግሩም ቅዳሴ ቁ.43



ማለት ነው። ዓለም ሲል ባጠቃላይ የሚታየውን የማይታየውን ፍጥረት ያመለክታል። ሁለቱ ቃላት በተገናኘ ሲነበቡ «የፍጥረታት ጌታ» የሚል ትርጉምን ይፈጥራል። ስለዚህ እግዚአብሔር በመፍጠር በጌትነት አንድ መሆኑን ያሳያል።

2ኛ. ሦስትነትን ያሳያል። እግዚአብሔር ከሚለውም ቃል ሌሎች ሦስት ቃላት ይወጣሉ እነዚህም እግዚ–አብ–ሔር እግዚ–ጌታ። አብ–አባት። ሔር–ቸር ማለት ነው። ምሥጢራዊ ትርጉሙ ጌታ የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል ሐዋርያት ጌታ ኢየሱስ እያሉ እንደሚጠሩት ሐዋ.ሥራ 16፥31።

አብ :- አባት ማለት ነው አባት የተባለው አብ ሲሆን ወልድን የወለደ መንፈስ ቅዱስን ያሠረጸ ነው። 2ጴጥ. 1፥17።

ሔር :- ቸር ማለት ነው። ቸር የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ቸር የተባለው ለሰው በሚሰጠው ጸጋው ብዛት ነው 1ቆሮ.12፥4።

ባጭሩ እግዚአብሔር የሚለው ስም የአንድነት ስም ሲሆን በምሥጢራዊ ትርጓሜው ሦስትነትን ይገልጣል።

«እግዚአብሔርም አለ» ብሎ በመለከታዊ ባሕርይ አንድ መሆኑን ይገልጻል። ምክንያቱም አለ አንድነትን የሚገልጽ ነውና።

«ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር» የሚለው አባባል ደግሞ ብዛትን ያመለክታል። በዚህ አነጋገር እግዚአብሔር በገጽ፥ በመልክዕ ወይም ሁለቱንም በሚጠቀልለው አጠራር በአካል አንድ ብቻ እንዳልሆነ እንረዳለን። ከአንድ በላይ ስንል ሦስትነትን ማለታችን ነው። ምንም እንኳን በዚህ ቦታ ላይ ሦስትነትን ባይገልጽም በሌላው ምዕራፍ ተገልጦአል።

የእግዚአብሔርን ሦስትነት ለመቀበል የማይሹ ወገኖች በዚህ ቦታ የተጠቀሰውን አነጋገር ለማስተባበል ሲጣጣሩ ይታያሉ። እግዚአብሔር ሦስትነቱን ለመግለጽ ሳይሆን ራሱን እንደ ነገሥታት ልማድ በአክብሮት ለመጥራት ብሎ የተጠቀመው ዘዴ ነው እንጂ ሌላ ምሥጢር ኖሮት አይደለም ይላሉ።

በመሠረቱ ነገሥታት ራሳቸውን ለማክበር «እኛ» እያሉ መናገራቸው በአንዳንዶቹ ነገሥታት የሚዘወተር የአነጋገር ዘይቤ ቢሆንም ዳሩ ግን ይህ አባባል በጥንታውያኑ ነገሥታት ይልቁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጠቀሱት ኃያላን ነገሥታት ዘንድ ያልተለመደ አባባል ነው አንዱም ንጉሥ ተጠቅሞበት አናገኝም። ለዚሁም የሚከተሉትን ምሳሌዎች መጥቀስ እንችላለን።

ፈርኦን:- የታወቀ የግብፅ ንጉሥ ነበር። ዳሩ ግን ይህ ንጉሥ ዮሴፍን «በግብፅ ምድር ሾምኩህ» አለው እንጂ ሾምንህ አላለውም ዘፍ.41+41።

ዳርዮስ:- ትዕዛዝ በሚያስተላልፍበት ወቅት «እኔ ዳርዮስ ይህንን አዝ ዣለሁ» ይል ነበር እንጂ አዘናል አላለም። መጽ.ዕዝ.6+12።

ናቡከደነጾርም «የሕልሙን ፍቺ እንዲያስታውቁኝ የባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ወደ እኔ ይገቡ ዘንድ አዘዝሁ» አለ እንጂ አዘዝን አላለም ትን.ዳን.4+6።

እ'/ግዲህ ነገሥታቱ ከእግዚአብሔር በተማሩትና እሱን ምሳሌ ባደረ'ጉት መሠረት ራሳቸውን ለማክበር እኛ ማለት ከጀመሩ ከላይ የጠ' ስናቸው ታላላቅ ነገሥታት ዘይቤውን በተጠቀሙበት ነበር።

ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱን ለማክበር ብሎ ሳይሆን፤ ሦስትነቱን ለማስረዳት ሽቶ ነው። «በመልካችን እንደምሳሌአችን» ሲል ሁለትና ወይም ከዚያ በላይ መሆኑን ይገልጻል።

በሌላ አንጻር አርዮሳውያን ይህ አባባል ሦስትነትን ሳይሆን ሁለትነትን የሚያሳይ ነው። ተናጋሪው እግዚአብሔር ሲሆን ረዳቱ መልአኩ ሚካኤልን ጨምሮ መናገሩን የሚያሳይ ነው ይላሉ፤ ይህ አባባል እግዚአብሔር ራሱን ከመልአኩ ከሚካኤል ጋር አንድ አድርጐ የተናገረው ነው የሚለውን አመለካከት ምን ያህል ሐሰትና የተሳሳተ መኾኑን መግለጽ ያስፈልጋል።

«በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» በዚህ አነጋገር ላይ በመልክ አንድ የሆኑ መፍጠር የሚችሉ ከአንድ በላይ የሆኑ አካላት መኖራቸውን ነው የሚገልጸው።



ለመሆኑ እግዚአብሔርን በመልክ የሚመስለው በባሕርይ የሚተካከለው ፍጥረታትን በፈጠረ ጊዜ አብሮት የፈጠረ ከመላእክት ወገን አለ? ወይም እግዚአብሔር ሰውን ብቻውን እስከ መፍጠር ደካማ ሆኖ በፍጥረቱ ረዳት አማካሪ የሆነው ከፍጥረታት ወገን ነበረ?

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል። «የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? ወይስ ማን መከረው? እውቀትን ማን አስተማረው? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?...ኢሳ.40+13።

የዚህ መልሱ ያዘዘውም አማካሪ የሆነውም በፍጥረት ሥራውም ተባባሪ ወይም ረዳት የሆነው ማንም እንደሌለ ብቻውን ሰማይን ያለ ባላ ምድርን ያለካስማ እንዳቆመ እንደዘረጋ የሚገለጥ ነው።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም የአርዮሳውያንን አመለካከት ሐሰት መሆኑን ሲገልጥ «የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና» ብሏል። ሮሜ.11+34–36።

ከሐዋርያው አነጋገር የምንረዳው እውነት ቢኖር እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር ያማከረው ፍጥረት አለመኖሩንና ያገዘውም ሆነ ረዳት የሆነው ማንም እንዳልነበር ነው።

ስለዚህ በአንድነት በሦስትነት ያለ የነበረ ጌታ አምላክ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር በሥልጣን በመሳሰለው አንድ ናቸውና «በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር» አሉ።

«እንፍጠር» ሲል አንድ አካል ሌሎቹን አካላት በመፍጠር ከእርሱ ጋር አንድ የሆኑትን መጥራቱ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ዘፍ.3+22፤ «እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ»

«እግዚአብሔርም አለ» ብሎ መለኮታዊ አንድነቱን ያመለክታል። ከእኛ የሚለው አባባል ደግሞ እግዚአብሔር አንድ ገጽ ነው የሚለውን እምነት ፍጹም ስሕተት መሆኑን ያረጋግጣል። አንድ

«እነርሱም ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት? አሉት «ሦስትነትን ያመለክታል።» «እርሱም የዛሬ አመት እንደዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ» ሲል ደግሞ አንድነቱን ያመለክታል።

«ሰዎቹም ከዚያ ተነሥተው ወደ ሰዶም አቀኑ አብርሃምም ሊሸኛቸው አብሮአቸው ሄደ።» ቁ.16 ተመልከት (ወደ ሰዶም ያቀኑት በሦስት ሰው አምሣል የተገለጡት ሥላሴ ናቸው። ምንም እንኳን በአካል ሦስት ቢሆንም በመለኮት አንድ እግዚአብሔር ስለሚባል «እግዚአብሔርም አለ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን?») ቁ 17 ብሎ ተናገረ።

«ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ ወደ ሰዶምም ሄዱ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር።

ይህን አባባል በተሳሳተ መንገድ ለመተርጐም የሚሞክሩ ክፍሎች «ሁለቱም ሰዎች ወደ ሰዶም ሄዱ። አብርሃምና እግዚአብሔር ግን ማውራት ጀመሩ ይላሉ። ዳሩ ግን የመጽሐፍ ቅዱስን አባባል በአንክሮ ብናጤነው «ሰዎቹም ያለው ለአብርሃም በሦስት ሰው አምሳል የተገለጡትን ነው» አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ነበር። የሚለው አነጋገር «እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን በኃጢአታቸው ብዛት የተነሣ በእሳት ሊያጋያቸው እንዳሰበ ለአብርሃም ከባለሟልነቱ የተነሣ በሚነግረው ጊዜ አብርሃም በእግዚአብሔር ዘንድ ባለው ሞገስ (ባለሟልነት) ስለ ሰዶምና ገሞራ ይማልድ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት መቆሙን የሚገልጥ ነው። በእግዚአብሔር ፊት መቆም ማለት ባለሟልነትን የሚያሳይ ነው። በእግዚአብሔር ፊት መቆም ማለትም ማማለድን የሚያመለክት መሆኑን ልበ አምላክ ዳዊት ሲያስረዳ «እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ» ብሏል መዝ.105፥23።

አንዳንድ ሰዎች በምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ ላይ የተጠቀሱትን ሁለቱን መላእክት ከላይ ከምዕራፍ አሥራ ስምንት ጋር አጣምረው ለአብርሃም የተገለጡለት ሦስት ሰዎች ሁለቱ መላእክት አንዱ እግዚአብሔር ነው ይላሉ። ዳሩ ግን እነዚህ ሁለቱ መላእክት እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ስለ ሰዶም ተነጋግሮ ከጨረሰ በኋላ ሰዶምን ያጠፋ ዘንድ እግዚአብሔር የወሰነው እርምጃ አግባባዊ መሆኑን አብርሃም ባመነ ጊዜ ሰዶምን ያጠፋ ዘንድ ከእግዚአብሔር የተላኩ እንጂ ለአብርሃም ከተገለጡት ከሦስቱ ሰዎች መካከል መሆናቸውን የሚያሳይ አንዳችም አይነት ማስረጃ የለም።

ምናልባት «ሁለቱም» የሚለውን አባባል ከምዕራፍ አሥራ ስምንቱ ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚገልጥ ነው ይላሉ «ም» የምትለው ፊደል መላእክቱ ከዚህ ቀደም የሚታወቁ መላእክት መሆናቸውን የሚገልጥ ስለሆነ የግጼታ ከም 18ቱ ጋር የሚቆራኝ ነው ይሉ ይሆናል። ዳሩ ግን «ሁለቱም» የሚለው አባባል ታዋቂነትን ያመለክታል ከተባለ ሰዶምና ጐሞራንም በእሳት ያቃጠሉት ሁለቱ መላእክት በብሉይ ኪዳን ከሌሎቹ መላእክት በብዛት የሚታወቁትን ሚካኤልንና ገብርኤልን ለመጠቆም ነው የሚል አመለካከት አለ።

ያም ሆነ ይህ የምዕራፍ አሥራ ዘጠኙ ሦስት ሰዎች እግዚአብሔር ሦስትነቱን ለመግለጥ ያደረገው መገለጥን ሲያመለክት በምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ ላይ የተጠቀሱት ሁለቱ መላእክት ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰዶምና ጐመራን በእሳት እንዲያቃጥሉ የተላኩ መላእክት መሆናቸውን ነው።

ኦሪት ዘኁልቁ 6፥24-26፤ «እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፤ ይራራልህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ ሰላምንም ይስጥህ»

ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር የሚለው ስም ተጠርቷል «ለምን? መቼም ያለ ምክንያት እግዚአብሔር የሚለውን ስም ሦስት ጊዜ አልጠራም ሦስት ጊዜ መጥራቱ ምክንያታዊና ዓላማ የሌለው ቢሆን ኖሮ እንዲህ ብሎ መግለጽ ይችል ነበረ እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም ፊቱን ያብራልህ ይራራልህ ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ ሰላምንም ይስጥህ» ግን በዚህ ዓይነት አጭር አገላለጥ ማስቀመጡ ቀላል ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል ሦስት ጊዜ መጠቀሙ የሥላሴን ትምህርት ሊያስተምረን ነው።

መዝ.117(118)፥16-17፤ «የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ፥ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች»

በማስከተሉ ሌላም አካል «መንፈስ ቅዱስ» መኖሩን ገልጾልናል። መንፈሱ የሚለው አካል ባይሆን የእግዚአብሔር ኃይሉ (አካል የሌለው) ቢሆን ኖር «የእግዚአብሔር መንፈስ» ልኮኛል ባለ ነበር። ዳሩ ግን ላኪዎች በአካል ሁለት መሆናቸውን ግልጽ ሲያደርግ «እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል» ነው ያለው ልከውኛል የሚለው ብዛትን እንጂ አንድ ብቻ መሆኑን አያሳይም።

ስለዚህ በዚህ ጥቅስ መሠረት ተላኪ ወልድ ላኪ አብና መንፈስ ቅዱስ። አብ በፍጹም ገጽ ያለ በመሆኑ እኔ ባይ ነው ወልድም በፍጹም ገጽ ያለ በመሆኑ እኔ ባይ ነው። መንፈስ ቅዱስም በፍጹም ገጽ ያለ በመሆኑ እኔ ባይ ነው አካል የለሽ ብትን ኃይል አይደለም።

## የሥላሴ ትምህርት በሐዲስ ኪዳን

ቀደም ብለን እንዳየነው የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት በብሉይ ኪዳን የተገለጸ ቢሆንም ዳሩ ግን እንደ ሐዲስ ኪዳን በግልጽ አልተረዳም ወይም ጉልህ አልሆነም ነበር። የዚህንም ምክንያት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሲያብራሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ተብለው የተጠሩት እስራኤላውያን አምላካቸው እግዚአብሔርን ሌሎች ባዕዳን አማልክትን (ጣዖትን) እያመለኩ ያስቆጡት ነበር በተለይ በአሕዛብ አማልክት (ጣዖታት) ብዛት ቅናታዊ ስሜት አድሮባቸው ነበርና እንደ አሕዛብ ብዙ አማልክት እንዲኖርአቸው ፍላጐቱ ነበራቸው «በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ» እንደሚሉ በዚህ ዓይነት ያልጸና ያልተረጋጋ ሕይወት ላይ ሳሉ እግዚአብሔር ሦስትነቱን ገሐድ ቢያደርግላቸው ኖሮ አምላካቸው እግዚአብሔር በመለኮት አንድ መሆኑን ዘንግተው እኔ የአብ ነኝ እኔ የወልድ ነኝ እኔ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ነኝ ወደሚለው ክፍፍል በገቡ ነበር። በአንድነቱ በሦስትነቱ ያለ የነበረ የሚኖረውን ጌታ ሦስት አድርገው ወደ ብዙ አማልክት (ፓሊተይዝም) በገቡ ነበር። ስለዚህ በእነርሱ ውስጥ በእምነታቸው ጽኑአን ለነበሩት ብቻ አንድነቱንና ሦስትነቱን ሲገልጥላቸው የተቀሩት ግን እስራኤል ሆይ ስማ እግዚአብሔር አምላክህ አንድ እግዚአብሔር ነው እርሱን ብቻ አምልክ» ዘጸ.6+41። በሚለው ሕግና ትዕዛዝ እንዲመሩ ተደርጓል።



እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች በገሐድ የሚገልጥበት ጊዜ የደረሰ ጊዜ ቀድሞ ከእስራኤላውያን ዘንድ ሰውሮት የነበረውን አንድነቱንና ሦስትነቱን ገሐድ አደረገው።

እንግዲህ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አባቱ አብን የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስን ገለጠልን። ስለ አንድነቱና ስለ ሦስትነቱ በጎላ በተረዳ ሁኔታ አስረዳን። ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን የሥላሴ ትምህርት በግልጥ ታትቷል። ይህንንም በተጨባጭ ለማስገንዘብ መጽሐፍ ቅዱስን (የሐዲስ ኪዳንን) ወደ መመርመር እንገባለን።

ማቴ.3+16:17፤ «...ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም+ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም+ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ:- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።»

በቤተ ክርስቲያናችን የጌታ ጥምቀትና መታሰቢያ በዓል በጥር 11 ቀን ይከበራል ይህ ወር አስተርእዮ በመባል ይታወቃል። መገለጥ መታየት ማለት ነው በጌታ ጥምቀት የተገለጠው ወይም የታየው ምንድነበር? መልሱ ለዘመናት ተሰውሮ የነበረው የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ነው በዚህ ቀን ሰማያት መከፈታቸውን ወንጌላዊው ገልጦታል። ሰማይ መስኮት ኖሮት የሚከፈት የሚዘጋ አለመሆኑ የታወቀ ነው። ዳሩ ግን ደጅ በተከፈተ ጊዜ በቤት ውስጥ ያለው ሁሉ እንደሚታይ እንዲሁም እስከዛሬ ድረስ ለብዙኃኑ ድብቅ ሆኖ የነበረው የእግዚአብሔር ልዩ ሦስትነት ታወቀ ተረዳ ተገለጠ ለማለት ሲሆን የአምላኩን ገጽታ ማየት ተስኖት ጣዖትን ያመልክ የነበረው የሰው ልጅ የአምላኩን ፊት አየ አምላኩን አወቀ በአንድነትና በሦስትነት የሚቀደስ መሆኑን ተገነዘበ ማለት ነው። በዚህ በጥምቀት ጊዜ የእግዚአብሔር ልዩ ሦስትነት እንዴት ተገለጠ?

1ኛ. ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በተለየ አካሉ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ ታይቷል አንድ አካል፤

2ኛ. የእግዚአብሔር መንፈስ (የአብ የወልድ ሕይወታቸው) እግዚአብሔር የሚለው የሦስቱ የአንድነት ስም ነውና፤ መንፈስ

ማቴ.28፥19፤ «...በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ»

ሥላሴ በስም ሦስት ናቸው። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ። አብ በሚለው ስም የሚጠራው አብ ብቻ ነው። ወልድ በሚለው ስም የሚጠራው ወልድ ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስ በሚለው ስም የሚጠራው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። አንዱ አካል በሌላኛው አካል ስም አይጠራም።

አብ ሲል በተለየ አካሉ ያለውን ወልድን የወለደውን መንፈስ ቅዱስን ያሠረጸውን እኔ ባይ አካልን ነው። ወልድ ሲል ከአብ የተወለደውን እኔ ባይ አካልን ነው። መንፈስ ቅዱስ ሲል ከአብ የሠረጸውን እኔ ባይ አካልን ነው።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ሥልጣን አንድ አገዛዝ ስላላቸው አንድ አምላክ ይባላል። ሰዎች ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታስገባውን ጥምቀት በሦስቱም ስም መጠመቅ እንዳለባቸው ጌታችን ገልጦአል። በአብ ስም ብቻ ተጠመቁ አላለም። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንጂ። ስለዚህ ማንም ክርስቲያን በሥላሴ ስም ሊጠመቅ ይገባዋል።

ሉቃ.1፥35፤ «መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፤ የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።»

ሥላሴ በእመቤታችን አድረዋል። ይህንንም ሉቃስ ጽፎታል። ገብርኤል ስለ እግዚአብሔር ልዩ ሦስትነት ገልጦአል። መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል በማለቱ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት ኃይለ ልዑል ወልድ ሥጋሽን ይዋሃዳል በማለት አካላዊ ቃል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ መዋሃዱን። ከአንቺ የሚወለደው የአብ የባሕርይ ልጅ ነው ብሎም አብን አንስቶአል። እንግዲህ ሥላሴ ማለት ሦስትነት ማለት በመሆኑ ቅ.ገብርኤል የሥላሴን ትምህርት ማስተማሩን ልብ ልንል ይገባል።

ዮሐ.1፥1፤ «በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብ ሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።»



ወንጌላዊው ዮሐንስ በቅድምና ያለውን እግዚአብሔርን በአንድነቱና በሦስትነቱ ገልጦታል። ያ ቃል ቀዳማዊ ነው። ያ ቃል አካላዊ ቃል ነው። ያ ቃል በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበረ። ያ ቃል እግዚአብሔር ነው። እንዲሁም ቀዳማዊ ቃል አስቀድሞ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዘንድ ነበረ በማለት የሦስትነትን (የሥላሴን) ትምህርት በግልጥ አስተምሯል።

ዮሐ.14፥15-17፤ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤»

ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምሥጋና ይግባውና፤ የሦስትነትን ትምህርት ግልጽ አድርጐ አስቀምጦታል። በዚህ ቦታ ላይ ሦስት አካላት መኖራቸው በግልጽ ተቀምጧል። እኔም በማለት ተናጋሪው አንድ አካል መሆኑን ገልጾአል። አብን በማለት በአካል ከእርሱ (ከተናጋሪው) የተለየውን ሌላ አካል ገልጾአል። ሌላ አጽናኝ በማለት ደግሞ ሦስተኛ አካል መኖሩን አስገንዝቦናል።

እንግዲህ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት በመለኮት አንድ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረው ነው። እግዚአብሔር ሦስትነት የሌለው አንድ አካል ብቻ ቢሆን ኖሮ ጌታ ይህን ባልተናገረ ነበር።

ዮሐ.15፥26፤ «ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤»

አሁንም በጌታ አነጋገር የአካል ሦስትነት መኖሩን ነው የምንረዳው። እኔ በማለቱ የራሱን በአካል ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ መለየት ሲያስረዳ ከአብ ዘንድ በማለቱ ደግሞ የአብን በአካል ከእርሱ የተለየ መሆን ገልጾአል። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስም እኔ ባይ አካል (Personal) መሆኑን ሲያረጋግጥልን «እርሱም» ብሎታል። እርሱም የሚባለው እኔ ባይ አካል ነው እንጂ ዝርው ኃይል (Impersonal Power) አይደለም። የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት ሲያስረዳም የእውነት መንፈስ ብሎታል። ይህ መንፈስ ቅዱስ እንደ

አብ እንደ ወልድ ፍጹም ገጽ (አካል) ያለው መሆኑን ጌታ ሲያስርዳ «እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» ብሎአል። ለምስክርነት የሚበቃ እኔ ባይ እንጂ ብትን ኃይል አይደለም።

ዮሐ.16፥7–11፤ እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ። እርሱም...መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤...ወደ አብ ስለምሄድ...»

በተመሳሳይ ሁኔታ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስን በአካል ልዩ መሆን ወይም የአካልን ሦስትነት አስተምሯል። እኔ በማለቱ ስለ ራሱ ማንነት አጽናኙ በማለት የገለጸው መንፈስ ቅዱስን ነው። በመሠረቱ የሚያጽናና እኔ ባይ አካል እንጂ ብትን ኃይል አይደለም። ጌታ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር እርሱ መጥቶ ዓለምን ይወቅሳል ብሏል። እርሱ ሲል አካላዊነቱን መግለጡ ሲሆን ዓለምን ይወቅሳል በሚለው አነጋገሩ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት በገሃድ መስክሯል። መውቀስ የሚችል ያለ የሚኖር እኔ ባይ አካል ነውና። ወደ አብ ስለምሄድ በማለቱም በሕልውና ፈጽሞ ወዳልተለየው በአካል ግን ከእርሱ ልዩ ወደ ሆነው ወደ አባቱ እንደሚሄድ ገልጦአል።

እንግዲህ የሥላሴን ትምህርት የማይቀበሉ ክፍሎች ይህን እንዴት ሊያስተባብሉ ይችላሉ? በመሠረቱ ከዚህ የበለጠ ማረጋገጫ ከወዴትስ ይመጣል። ሦስት አካላት ባይኖሩ ኖሮ ጌታ ከላይ ያለውን ባልተናገረ ነበር። አንድ አካል እንደ ሦስት አካላት ሆኖ ሊናገር አይችልም። ስለዚህ ሰባልዮሳውያንም ሆኑ ሌሎቹ አጽራረ ሥላሴ ራሳቸው ግራ ተጋብተው ሌላውን ግራ ማጋባትን ትተው በአንድነት በሦስትነት ወደ ሚመሰገነው አምላክ ቢቀርቡ ይሻላቸዋል እንላለን።

የሐዋ.7፥55፤ «በእስጢፋኖስም መንፈስ ቅዱስ አደረበት ሰማይ ተከፍቶ ተመለከተ የእግዚአብሔርን ክብር አየ ኢየሱስም በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ»

ቅዱስ እስጢፋኖስ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ሲያድርበት ጌታ ኢየሱስን በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ አይቶአል። ራእዩን የገለጠለት መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ምሥጢር ገላጭ ነውና ሰማይ



ሲከፈት በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ሰማያዊውን ክብር ሲያይ አብና ወልድን አየ። ባጠቃላይ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ላይ ታይተዋል።

አብና ወልድ በአካል ልዩ መሆናቸውን ራሱ እስጢፋኖስ ጌታ ኢየሱስን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ አየዋለሁ ብሎ ገልጾአል። አካላዊ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ አድሮ ምሥጢርን ገልጾለታል።

2ቆሮ.13፥14፤ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችን ጋር ይሁን።»

በብሉይ ኪዳን የነበረው ቡራኬ ወይም ምርቃት «እግዚአብሔር ይባርክህ፥ ይጠብቅህም፥ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፥ ይራራልህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ፥ ሰላምንም ይስጥህ» የሚል ነበር። ዘኍ.6፥24–26።

በተመሳሳይ ሁኔታ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የቆሮንቶስ ሰዎችን ሲባርክ የሥላሴን ስም ጠርቶ ባርኳል። አንዳንድ ሰዎች አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ አይደሉም። እውነተኛ አምላክ አብ ብቻ ነው። ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጡራን ናቸው የሚሉ አሉ። ለዚህም ምክንያት የሚያደርጉት በየቦታው ሲጻፍ የአብ ስም መቅደሙ የወልድ ስም መከተሉ የመንፈስ ቅዱስ ስም ደግሞ መሠለሱን ነው። ይህ የስም ቅደም ተከተል የስልጣንን ተዋረድ ያመለክታል ይላሉ። በእነርሱ አመለካከት አብ በመጀመሪያ ደረጃ በመጠቀሱ የበላይ ወልድ በሁለተኛ ደረጃ በመጠቀሱ የአብ የበታች መንፈስ ቅዱስ በሦስተኛ ደረጃ በመጠቀሱ ከወልድ የሚያንስ ነው ይላሉ። ይህ ግን ስህተት መሆኑን ጳውሎስ የቆሮንቶስ ምእመናንን በባረከበት ጊዜ ገልጾልናል። ጳውሎስ በመጀመሪያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቀጥሎ አብን ከዚያም መንፈስ ቅዱስን ጠርቷል። እንግዲህ እንደ መናፍቃኑ አባባል መጀመሪያ የተጠራው በሁለተኛው ከተጠራው የሚበልጥ ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ይበልጣል ማለታቸው ነው። ነገር ግን በሥላሴ ዘንድ መበላለጥ የለም። አብ ከወልድ አይበልጥም። ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም ሦስቱም በመለኮታዊ ሥልጣን አንድ ናቸውና። ስለዚህ አንዱ ቀድሞ መጠራቱና ሌላው መከተሉ በሥላሴ ሥልጣን ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም።

ከአንዱ አይከተልም። እንደዚሁም ሁሉ የሥላሴም ቅድምናቸው አንዲት ነች። በቅድምና አንድ ናቸው። በልብ የተመሰለ አብ በቃል ከተመሰለ ከወልድ ቀድሞ የኖረበት ዘመን የለምና። ስለዚህ በቅድምና አንድ ከሆኑት ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ሰው ሆነ ለማለት ይመቸው ዘንድ «ቃል» በሚለው ስሙ ጠርቶታል።

ፈጠረበት ለማለት:- አብ በወልድ ዓለምን ፈጠረ ሲባል እንደ አርዮስ አይደለም። አትናቴዎስ ሐዋርያዊ እንደተናገረው የእግዚአብሔር ቃል እኛን ለመፍጠር የተፈጠረ አይደለም። እኛ በእሱ ተፈጠርን እንጂ። «በሱ ኹሉ ተፈጠረ።» ለእኛ ለድኩማን መፈጠሪያ እንዲኾን ልዑሉና ኃያሉ እንደ አገልግሎት መሣሪያ ተፈጠረ ብሎ ማውራት ከደካማ አስተሳሰብ የተገኘ ነው። ዓለምን እንደፈጠረ ባይካድም ቃል ምን ጊዜም ነበረ። ምንጊዜም ባሕርያዊ ነውና። በእርግጥ ያለ ቃል ምንም አልተፈጠረም። ያለ እጅ ምንም መሥራት እንደማይቻል «እጁ ክንዱ» ይባላልና። አብ በወልድ ዓለምን ፈጠረ ሲባል በእጅ ጥልፍ እንደመጥለፍ ሥዕል እንደመሳል ነው። «እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ» ያለውን ቃል ሲተረጉም ቃሉን ሰምቶ ትእዛዙን ሊፈጽም የሚሮጥ ተወራጅ አሽከር ነበር ማለት አይደለም። ይህ በሰዎች ዘንድ በሰዎች ባሕርይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግን ራሱ ፈጣሪ ነው። የአብም ፈቃዱ እሱው ራሱ ነው።

እንግዲህ ወንጌላዊው ሰው የሆነው የፍጥረታት ባለቤት መሆኑን ለመግለጽ «ቃል» በሚለው ስሙ ጠራው።



## አምላክ ወይም ወልድ ብሎ ለምን አልጠራውም?

ቃል በሚለው ምትክ አምላክ ቢለው ኖሮ መናፍቃን የጸጋ አምላክ እንጂ የባሕርይ አምላክ አይደለም ባሉ ነበርና ዘጸ.7፥11። መዝ.31(32)፥6።

ወልድም ቢለው እስራኤል የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው እንደተጠሩ ሁሉ ዛሬም ምእመናን በጸጋ እንደሚወለዱት ሁሉ እርሱም የጸጋ ልጅ እንጂ የባሕርይ ልጅ አይደለም እንዳይሉ እንዲሁም ወልድ ብሎት ቢሆን የሁለቱን (የአብና የወልድን) አንድነት ብቻ እንጂ የሦስቱን አንድነት አያስረዳምና።

ቃል ግን የሦስቱን (የአብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ) አንድነት ያስረዳልና «ቃለ አብ ወቃለ መንፈስ ቅዱስ ወልድኒ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ እንዲል» ወልድ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው።

የሦስቱን አንድነት በሚያስረዳ እዱ መዝራዕቱ (ክንዱ) በሚለው ለምን አልጠራውም ቢሉ ይህም ቢሆን የአፍአ (የውጭ) አንድነታቸውን ነው እንጂ የውስጥ አንድነታቸውን አያስረዳም።

እሺ ውሳጣዊ አንድነታቸውን በሚያስረዳ ጥበቡ ምክሩ ሕሊናው አይለውም ነበር ቢሉ የምክር የሕሊና መዲናቸው መገለጫቸው ቃል ነውና በመዲናቸው በመገለጫቸው በቃል ተናገረው።

እንዲሁም ቃል ከልብ ተገኝቶ በልብ ሕልው ሆኖ ሲኖር ልገለጽ ባለ ጊዜ ባንደበት እንዲገለጽ እርሱም ከአብ ተገኝቶ (ተወልዶ) በአብ ሕልው ሆኖ ሲኖር ልገለጽ ባለ ጊዜ በሥጋ ተገልጧልና።

አንድም ለምሳሌ ያመቸው ዘንድ ነው። ቃል በልቡና ሲወጣ ሲወርድ ይኖራል። ሰዑየው ቀለም በጥብጦ ብዕር ቀርጾ ብራና ዳምጦ በጻፈ ጊዜ ረቂቁ ቃል ከልቡና በቀለም ገዝፎ እንዲታይ ረቂቅ አካላዊ ቃልም ከአብ አንድነት ሳይለይ በሥጋ ገዝፎ ታይቷልና።

በቅድምና ነበረ ብሎ የመሰከረለት አካላዊ ቃል ወልድ በእግዚአ ብሔር አብ ሕልው መሆኑን ሲገልጥ፥ «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ብሎአል። የፀሐይ ብርሃን በፀሐይ ክበብ ነበልባል በእሳት

የባሕር ርጥበት በባሕር ስፍሐት፣ የነፍስ ቃል በልብ ሕልው ሆና እንዲኖር ሁሉ «ያ ቃል በእግዚአብሔር አብ ሕልው ነው» ብሎ የሥላሴን በሕልውና አንድ መሆን አስገንዝቦአል።

## «ያ ቃል እግዚአብሔር ነው» ዮሐ.1፥1።

አርዮስና መሰሎቹ የወንጌላዊውን ምስክርነት «ጀር ዳባ ልበስ» ብለው፣ መንፈስ ቅዱስ ሳስተማረው ትምህርት ጀርባቸውን ሰጥተው ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ለይተው ፍጡር ብለውታል። ለክብር ባለቤት ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምሥጋና ይግባውና! ከጌታ የተማረ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተጥለቀለቀ ሐዋርያው ዮሐንስ፣ «በቅድምና ያለ ነው» ብሎ የመሰከረለት ቃል እግዚአብሔር መሆኑን በማያሻማና በማያከራክር ግልጽ በሆነው አገላለጽ ገልጾታል። በዚህም አካላዊ ቃል ከአብ ጋር በመለኮታዊ ሥልጣን አንድ መሆኑን ገልጾልናል። በተለየ አካሉ ፈጥሮ የሚገዛ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ይህንንም ቅዱሳት መጻሕፍት ተባብረው የሚመሰክሩት እማናዊ ነገር ነው።

የሰውን ሥጋ የተዋሐደው አካላዊ ቃል፤ አንድ አምላክ አንድ እግዚአብሔር ተብለው ከሚጠሩት ከሦስቱ አካላት አንዱ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር ያስረዳል።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ሰው መሆን ሲገልጥ፣ «በሥጋ የተገለጠ የእግዚአብሔርነት ምሥጢር በእርግጥ ያለምንም ጥርጥር ታላቅ ነው።» 1ጢሞ.3፥16። "And without controversy great is the mystery of godliness: God was manifest in the flesh,..." 1Tim. 3 : 16 (ኪንግ ጀምስ ትርጉም)

ሐዋርያው ለደቀ መዝሙሩ እንዳስተማረ፣ በሥጋ የመጣው ወይም ሥጋን የተዋሐደው ያለምንም ጥርጥርና ውዝግብ እግዚአብሔር መሆኑን እንድናምን ያስገድደናል። እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ተወልዷልና ይህን ሃይማኖት ደግሞ ያለጥርጥር መቀበል እንዳለብን ሐዋርያው አሳስቧል።



በአንድ ወቅት ጌታ ስለራሱ ማንነት ፈሪሳውያንን ሲጠይቃቸው «ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?» ብሎአቸው ነበር። እነርሱም «የዳዊት ልጅ ነው» አሉት። ጌታም መልሶ እንግዲያስ ዳዊት ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው ሲል እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል? ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው እንዴት ልጁ ይሆናል? አላቸው ማቴ.22፥41።

በዚህ አነጋገሩ የባሕርይ ጌታ የባሕርይ አምላክ የዳዊት ፈጣሪ የዳዊት ጌታ ባጠቃላይ እግዚአብሔርነቱን ገልጦአል።

ከሐዋርያቱ አንዱ ፊልጶስ መለኮትን ለማየት ከነበረው ጉጉት የተነሣ አጠገቡ ያለውን የጌታን ማንነት ባለመገንዘቡ፣ «ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል» ብሎ ጌታን ለመነ። ጌታም፣ «አንተ ፊልጶስ ይህን ያህል ዘመን ከአንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን?» የሚል አስገራሚ መልስ ነበረ የመለሰለት። እንዲህ ሲል አብ ነኝ ማለቱ አልነበረም። ዳሩ ግን በመለኮታዊ ሥልጣን ከአብ ጋር አንድ መሆኑን ሊገልጥለት በመፈለጉ ነው። ስለዚህ «እኔን ያየ አብን አየ» በማለት የባሕርይ አንድነታቸውን አስረድቷል። ዮሐ.14፥8–10።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ መለኮት፣ አንድ ክብር፣ አንድ ኃይል፣ አንድ ሥልጣን ነው ያላቸው። አንድ ሰው ክርስቶስ ሁሉን ቻይ መለኮት ወይም እግዚአብሔር ከሆነ «እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም» ብሎ ወንጌላዊው ለምን ተናገረ? ዮሐ.1፥18። ምክንያቱም ክርስቶስ ታይቷል ተዳሷል ሊል ይችላል። በመሠረቱ ወንጌላዊው «እግዚአብሔርን በፍጹም መለኮታዊ ክብሩ ያየው ሰው እንደሌለ መግለጡ ነው እንጂ ሥጋን ተዋሕዶ በትህትና ክብሩን ሰውሮ አልታየም አላለም።

መለኮት በዚህች ምድር ሥጋን ተዋሕዶ ሠላሳ ሦስት ዓመት ሙሉ ሲመላለስ በትህትና ክብሩን ሰውሮ ነበር። እንዳውም ባንድ ወቅት ከደቀ መዛሙርቱ ሦስቱን ባለሟሎቹን ጴጥሮስን ያዕቆብንና ወንድሙን ዮሐንስን ይዞ ወደ ረዥም ተራራ ብቻቸውን ባወጣቸው ጊዜ በፊታቸውም ተለወጠ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ» ማቴ.17፥2። ከዚህ የምንረዳው ጌታ ብርሃን

መድኃኒት እንደሌለ፤ በእርግጥም ከእግዚአብሔር በቀር ለአዳም መድኃኒት የሚሆን ባለመኖሩ ነው መድኃኒተ ዓለም ወደ ዓለም የመጣው። እግዚአብሔር የሥጋና የነፍስ መድኃኒት ነው። አዳኝም እርሱ ብቻ ነው። በኃይሉ ማዳን የሚችል ከእርሱ በስተቀር ሌላ ማንም የለም። ቅዱሳን ቢያድኑ በእርሱ ኃይልና ሥልጣን ነው።

ጳውሎስ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር፥ «የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ እየጠበቅን» በማለት የጌታን የባሕርይ አምላክነትና መድኃኒትነት ገልጦአል። ቲቶ.2፥12። እንግዲህ ክርስቶስ አምላክና መድኃኒት ከሆነ በሆሴዕ አድሮ የተናገረው እርሱ መሆኑን እንረዳለን፥ «ከእኔ በቀር አምላክና መድኃኒት የለም።» ይህን በዘመን ብሉይ የተናገረው ጌታ በኋለኛው ዘመን መድኃኒትን በማዕከለ ምድር ያደርግ ዘንድ ተገለጠ።

«እርሱ እናንተ አናጢዎች የናቃችሁት ደንጊያ ነውና ያም የማዕዘን ራስ ሆኖአልና። ሌላ ሕይወት የለም ከሰማይ በታችም ሊድንበት ለሰው ልጅ የሚሰጥ ሌላ ስም የለም» የሐዋ.4፥11:12።

ይህ ስም የገናናውና የልዑለ ባሕርይ፥ የክብር ባለቤት የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። የሰው ልጅ የሚድንበት የመለኮት ስም ነው። አጋንንት የሚፈሩት ታላቅ ስም ነው። «ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም» ፊሊ.2፥9። ይህ ስም የእግዚአብሔር አምላክ ስም ነው። የፍጡር ስም ቢሆን ኖሮ ይህን ያህል ክብርና ኃይል እንዳለው ባልተናገረ ነበር።

ከእኔ በቀር መድኃኒት የለም ያለው ጌታ እኛን ሊያድን መጣ። «ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል።» ሉቃ.2፥11።

ኢሳ.9፥6፤ «ሕፃን ተወልዶልናል፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መከር ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።»

ይህ ትንቢት የተነገረው ከድንግል ማርያም ለተወለደው ለሕፃን ክርስቶስ ነው። ማቴ.2፥1። ሉቃ.2፥7። እንግዲህ ኃያል አምላክ



የሚባል ፍጡር ነውን? ፍጡር ኃያል አምላክ ከተባለ እግዚአብሔርነትን ተጐናጸፈ ማለት ነው።

እኛስ ኃያል አምላክ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን እንናገራለን። ነቢያትና ሐዋርያትን መሠረት አድርገን ጌታችንም ኃያል አምላክ መባሉ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው፤ አምላካችን የዘላለም አባታችን ነው። ርስት መንግሥተ ሰማይን የሚያወርሰን ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር የዘላለም አባት ሌላ የለም። ሚልክያስ እንደተናገረ፥ «ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን?» ሚል.2፥10። እርሱም አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ነው።

ራእይ 1፥8፤ «ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል።»

ሙሴ «የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ ባልሁም ጊዜ:- ስሙስ ማነው? ባሉኝ ጊዜ ምን እላቸዋለሁ? አለው። እግዚአብሔርም ሙሴን:- «ያለና የሚኖር» እኔ ነኝ አለው፤ «እግዚአብሔር ለሙሴ «ያለና የሚኖር» እኔ ነኝ ብሎታል። ዘጸ.3፥14።

ያለውና የነበረው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን እግዚአብሔር አምላክ ራሱ ለሙሴ ገልጾለታል። ዮሐንስም ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር፥ «ያለውና የነበረው የሚመጣውም» ብሏል። ያለውና የነበረው ያለው ለፍርድ የሚመጣውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። እርሱም፥ «ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ» መሆኑን ጌታ ራሱ መናገሩን ዮሐንስ ጽፎታል።

ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ነው። አልፋና ዖሜጋም እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን አረጋግጦልናል። ሁሉን ቻይ (The Almighty) ነው።

ራእይ 22፥12፤ «እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።»

ይህን የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አስቀድሞ ኢሳይያስ ይህን በማስመልከት ትንቢት ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር፦ «እነሆ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይመጣል ክንዱም ስለ እርሱ ይገዛል፤ እነሆ፥ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙም በፊቱ ነው።» ኢሳ.40፥10።

አስቀድሞ ኢሳይያስ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ሀብተ ትንቢት ተሰጥቶት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምፅአትና ፍርድ ሲናገር ክርስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል። አልፋና ዖሜጋም እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ይኸው ኢሳይያስ ሲያስገነዝብ፥ «የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም።» ኢሳ.44፥6።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር በመሆኑ አልፋና ዖሜጋ ተብሏል።

የሐዋ.1፥9፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ መመሪያ ከሰጠ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ ማለቱን (ማረጉን) እናነባለን። ሐዋርያቱ እያዩት በክብር ወደ ሰማይ ያረገው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይደሉም። ከንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋና ነፍስ ነሥቶ በተለየ አካሉ የተወለደው አካላዊ ቃል እንጂ።

ልበ አምላክ ዳዊት የጌታ እርገት ከመሆኑ ሺ ዘመን ቀደም ብሎ መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት እንዲህ ሲል ትንቢት ተናግሮ ነበር፥ «እግዚ አብሔር በእልልታ በመለከት ድምፅ አረገ» መዝ.46(47)፥5።

ሐዋርያት እያዩት በይባቤ (በክብር በምስጋና) ያረገው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን ዳዊት አረጋገጠ።

የሐዋ.1፥11፤ «የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ ያረገው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል»



በፍጻሜ ዘመን በሥጋ ማርያም ግልጥ ሆኖ የሚመጣው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን መላእክት ያረጋገጡ ሲሆን ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ደግሞ፥ «ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል» መዝ.49፥2፤ በማለት ለፍርድ የሚመጣውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል።

ጳውሎስም፥ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ይመጣል» (ተሰ.3፥12፤) በማለት ጌታ ከእልፍ አእላፋት ወትእልፊት አእላፋት (የብዙ ብዙ) ከሚሆኑ መላእክቱ ጋር እንደሚመጣ ተናግሯል። ዘካርያስ ደግሞ፥ «አምላኬ እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ይመጣል» ብሎ ተናግሯል። ዘካ.14፥5።

በመላእክት ታጅቦ የሚመጣው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ዘካርያስ እግዚአብሔር ብሎ መናገሩ የጌታችን እግዚአብሔርነት የተረጋገጠ በመሆኑ ነው።

## ያ ቃል ሥጋ ሆነ

«ምን እላለሁ? ምንስ እናገራለሁ? ከዘመን አስቀድሞ የነበረ እርሱ ትንሽ ሕፃን ሆኖዋልና፤ እኔ ፈጽሜ አደንቃለሁ። ከሰማየ ሰማያት በላይ የሚሆን በዘለዓለማዊ ዙፋን የሚኖር እርሱ በበረት ተጣለ፤ ከሥጋዌ አስቀድሞ አይዳሰስ የነበረ አንዱ እርሱ በምድራውያን እጅ ተዳሰሰ፤ ኃጢአትን የሚያስተሰርይ እርሱን በጨርቅ ጠቀለሉት ይህን ወዶአልና።» ሉቃ.2፥10–13። ዕብ.1፥8፤ 7፥26። ማቴ.9፥1–7።

«ክብሩ ተለይቶት የነበረ ሥጋን ክቡር አምላክ ሊያደርገው የጸጋ ገዥነትን አጥቶ የነበረ ሥጋንም የባሕርይ ገዥ ሊያደርገው ወደደ፤ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ያለውንም ሰው በመሆን ሊገልጠው ወደደ።» ዘፍ.3፥22። መዝ.39/40፥7። ዕብ.10፥5–7። ዮሐንስ አፈወርቅ።[1]

---

[1] ሃይማኖተ አበው ዘዮሐንስ አፈወርቅ ገጽ 220።

ፍጥረት ሁሉ በርሱ ሕልውና በርሱ አንድነት የተፈጠረ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ብርሃን ነውና ጨለማ ለወረሰው ዓለም የጽድቅ ብርሃንን ያበራ ዘንድ ወደ ዓለም መጣ። ወደ ገዛ ወገኖቹ የመጣው አማናዊው ብርሃን እርሱ ነው። «እግዚአብሔር ብርሃን ነው» 1ዮሐ.1፥5።

*«ያ ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ» ዮሐ.1፥14።*

ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጁ አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ መወለዱን ወንጌላዊው ሲያስረዳ፥ «ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ» አለ።

## *ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ ሲል እንዴት ነው?*

## የተሳሳቱ አመለካከቶች

በአምላክ ሰው ሆኖ መገለጥ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች ተሰንዝረዋል። ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል።

ሚጠት:- የቃሉ ትርጉም መመለስ ማለት ሲሆን እንደ ሙሴ በትር ወይም እንደ ግብፅ ውኃ ማለት ነው። በትረ ሙሴ ፊት በትር ነበረች። ኋላ እባብ ሆነች። መልሶ ቢያነሳት ደግሞ በትር ሆነች። ዘጸ.4፥2–5። ማየ ግብጽም ቀድሞ ውኃ ነበር። ኋላ ደም ሆነ። እንደገናም ውኃ ወደ መሆን ተመለሰ። ዘጸ.7፥17–25።

ከላይ በተገለጸው መሠረት የሙሴን በትርና የግብጽን ውኃ ምሳሌ በማድረግ አምላክም መጀመሪያ አምላክ ነበረ። ቀጥሎ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ተለውጦ ሰው ሆነ። የመጣበትን ዓላማ ከፈጸመ በኋላ ተመልሶ አምላክ ሆነ። ይህን አመለካከት በአጭሩ ስንገልጸው በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ሥጋ ሆነ፤ ተመልሶ ቃል ሆነ ይላሉ።

ውላጤ:- የቃሉ ትርጉም መለወጥ ማለት ነው። ቃል ሰው የሆነው በመለወጥ ነው በማለት, የሎጥ ሚስትንና የቃናን ውኃ እንደ ምሳሌነት ይጠቅሳሉ። የሎጥ ሚስት ወደኋላ ዞራችሁ እንዳትመለከቱ የሚለውን ቃል ጥሳ ወደ ኋላዋ ዞራ በእሳት



የምትጋየውን ሰዶምና ገሞራ በመመልከትዋ የጨው ሐውልት ሆና እንደቀረች (ዘፍ.19፥26) ማለትም ሰው የነበረችው ተለውጣ የጨው ሐውልት እንደሆነች እንዲሁም ቃልም ፍጹም ተለውጦ ሰው ሆነ (ሥጋ ሆነ) ይላሉ። በቃና ዘገሊላም ውኃው ወደ ወይን ጠጅ እንደተለወጠ ዮሐ1፥1–11።

ቱሳሔ:- ትርጉሙ ቅልቅል ማለት ነው። እንደ ማርና እንደ ውኃ፥ እንደ ወተትና እንደ ቡና፤ ማርና ውኃ ሲቀላቀሉ ስም ማዕከላዊ፥ መልክዕ ማዕከላዊ፥ ጣዕም ማዕከላዊ ይሆናል።

ስም ማዕከላዊ ማለት የዕለቱ ከሆነ ብርዝ፥ የሰነበተው ከሆነ ደግሞ ጠጅ ይባላል ማለት ነው።

መልክዕ ማዕከላዊ ማለት እንደ ማር ሳይነጣ እንደ ውኃ ሳይጠቁር ሰርጀን ይመስላል።

ጣዕም ማዕከላዊ ማለት እንደ ማር ሳይከብድ እንደ ውኃ ሳይቀል ማዕከላዊ ጣዕም ያለው ሲሆን ነው።

ወተትና ቡናም ሲቀላቀሉ እንደ ወተት ያልነጣ እንደቡና ያልጠቆረ ዳሩ ግን ማዕከላዊ ኅብር ይኖረዋል።

ቃልም ሥጋ ሆነ ሲባል እንደዚህ ነው። ቃልና ሥጋ ተቀላቀሉ ማለት ነው ይላሉ።

ትድምርት:- ትድምርት ሲባል እንዴ ልብስ ወይም እንደ እንጀራ ነው። ልብስ በልብስ ላይ ቢደርቡት ይደረባል። ሲነጥሉትም ይነጠላል።

ቃልም እንደ ልብስ በሥጋ ላይ እንደተደረበ አድርገው የሚመለከቱ ክፍሎች ናቸው።

ኅድረት:- እንደ ዳዊትና ማኅደር፥ ወይም እንደ ሰይፍና ሰገባ ማለት ነው። ማኅደሩ የዳዊቱ ማደሪያ እንደሆነ ሁሉ ሥጋም ለቃል ማኅደሩ ሆነ። ቃልም በሥጋ ውስጥ አደረ እንደ ማለት ነው። ሰይፍም በሰገባ ውስጥ እንደሚያድር እንዲሁም ቃል በሥጋ አደረ እንደ ማለት ነው።

እንግዲህ ባሕርይ ስንል አካል ሥራውን የሚሠራበት የአካል መሣሪያ ነው። በምሳሌ ግልጽ ብናደርገው ውኃን እንውሰድ። ለውኃ አካልም ባሕርይም አለው። አካሉ በብርጭቆ ወይም በእንስራ የሚቀዳው ሲሆን፥ ባሕርዩ ርጥበቱ ነው። ሥራውም የደረቀውን ማራስ የራሰውን ማበስበስ ነው። ውኃ ማናቸውንም የደረቀ ነገር ቢነከሩበት ማራሱ ርጥበት ባሕርዩ ቢኾን ነው። ርጥበት ባይኖረው ሊያርስ አይችልም ነበር ማለት ነው።

ባሕርይ የአካል መገኛ ነው ባልን ጊዜም ውኃን መሬትን፥ ነፋስን፥ እሳትን ባሕርያት ብለን የአዳም ምሉ አካሉ ከነዚህ ከአራቱ ከውኃ፥ ከመሬት፥ ከነፋስ፥ ከእሳት መገኘቱን መናገራችን ነው።

እንዲህም በምንልበት ጊዜ ለአራቱም አካል ባሕርይም እንዳላቸው መዘንጋት የለበትም። የእሳት አካሉ በእንጨት ላይ ወይም ነበልባሉ ቦግ ቦግ ሲል ይታያል። ባሕርዩ ሙቀት፥ ደረቅነት፥ ብሩህነት ነው።

እኒህ ባሕርያት መኖራቸውን ለማወቅ የምንችል እሳቱ በመፋጀቱ በማቃጠሉ ብርሃን በማሳየቱ ነው እንጂ ባሕርያት እንደ አካል ተገልጸው ወይም ከአካል ተለይተው አይተናቸው አይደለም።

ውኃም አካሉ ሲፈስ ይታያል። በዋንጫ፥ በብርጭቆ ይያዛል። ባሕርዩ ግን እርጥብ፥ ብሩህ ወይም ንጹሕ ነው። እነዚህ ባሕርያት መኖራቸው የሚታወቀው ሲፈስ የምናየውን አካሉን የርጥበት የቁረት የጽሩይነት ሥራ ሲያሠሩት በማየታችን ነው እንጂ እንደ አካሉ ገዝፈው ታይተው ተዳሰው ከአካል ተለይተው ሥራ ሠርተው አይደለም።

ነፋስ አካሉ ረቂቅ ነው። ዛፍ ሲያወዛውዝ ባሕር ሲያናውጽ ካልኾነ በቀር ባይን አይታይም። ባሕርዩ ግን ጽሉም ይቡስ (ደረቅነት) ቈሪር ነው። እነዚህ ባሕርያት ነፋስን የጽሉምነት፥ የይቡስነት፥ የቈሪርነት ሥራ ሲያሠሩት አይተን መኖራቸውን ከማወቅ በቀር ከአካሉ ተለይተው ሊታዩ ወይም ሥራ ሊሠሩ አይችሉም።[4]

---

[4] መድሎተ አሚን



ከላይ በተዘረዘረው መሠረት አካልና ባሕርይ አንድ ሲኾኑ ልዩነት እንዳላቸው፥ ልዩነት ሲኖራቸው ደግሞ ተፈልጦ የሌለባቸው አንድ እንደኾኑ፥ አካል ሠሪ ባሕርይ አሠሪ መኾናቸውን ባሕርይም አካላዊ ፍጹመ አካል ቢባል እንጂ አካል አለ መባሉን አካልም ባሕርያዊ ሕያወ ባሕርይ ቢባል እንጂ ባሕርይ አለመባሉን ተረድተናል።

መለኮታዊ አካልና ባሕርይ ከሰብአዊ አካልና ባሕርይ ጋር ሲነፃፀር። መለኮታዊ አካል «አስገኚ የሌለው፥ ረቂቅ፥ የማይጨበጥ፥ የማይዳሰስ፥ እሳታዊ፥ ምሉዕ፥ ሰፋሕ የሆነ (በየትም ቦታ ያለ።)

ሰብአዊ (ሥጋዊ) አካል:- አስገኚ ያለው ግዙፍ የሚታይ የሚጨበጥ የሚዳሰስ ውሱን ነው።

መለኮታዊ ባሕርይ:- ፈጣሪነት፥ ሁሉን ቻይነት፥ ዘለዓለማዊነት፥ የማይለወጥ፥ የማይሻር፥ የማይራብ፥ የማይጠማ፥ የማይ ታመም፥ የማይሞት።

ሰብአዊ (ሥጋዊ) ባሕርይ:- ደካማ፥ ተራቢ፥ ተጠሚ፥ ሞት የሚስማማው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ነው ስንል መለኮታዊ አካል ከሥጋዊ አካል መለኮታዊ ባሕርይ ከሥጋዊ ባሕርይ ተዋሕደው በተዋሕዶ አንድ መሆናቸውን መግለጻችን ነው።

## ተዋሕዶ እንዴት?

ወንጌላዊው ዮሐንስ በመጀመሪያ ቃል ነበር ብሎ በከዊን ስሙ ጠርቶታል። ቃል በሚለው የከዊን ስም የጠራበት ምክንያት አለው። በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን ላይ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት የአካል ስም፥ ልብ ቃል እስትንፋስ ማለት የኩዊን ስም መኾኑን ገልጸናል። የአካል ስም ማለት ደግሞ እያንዳንዱ ሰው ከተወለደ በኋላ ሊጠራበት እንደሚወጣለት አብርሃም፥ ይስሐቅ ያዕቆብ እንደ ማለት ያይደለ ሰው እንደማለት ያለ አካል ሲገኝ የሚገኝ ማለት ነው።

ልብ ቃል እስትንፋስ ማለት ግን ተፈልጦ ተከፍሎ በሌለበት ባንዲት ባሕርይ ያለ የከዊን ስም ነው። ይኸውም ቀደም ተብሎ

እንደተገለጸው አንድነት ሳለበት ልዩነት፥ ልዩነት ሳለበት አንድነት ያለበት ነው። ልዩነቱ በከዊን ነው። አንድነቱ ግን በሕልውና መገናዘብ ነው። ይህን ጠንቅቆ ማወቅ የተዋሕዶን ምሥጢር እንድንረዳ ይጠቅማል።

የተነገረው ትንቢት የተቆጠረው ሱባዔ ሲፈጸም አካላዊ ቃል ከድንግል ማርያም ሰው ሆነ። ይኸውም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ባበሠራት ጊዜ፥ «እንደ ቃልህ ይሁንልኝ ይደረግልኝ» ባለች ጊዜ ቃሏን ምክንያት አድርጐ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ የምትኾን በከዊን (ሁኔታ) የምትለይ ባሕርይ ያለችው አካላዊ ቃል ሰብአዊ ባሕርይ ያለው ሰብአዊ አካልን እንበለ ዘርዕ (ያለ ወንድ ዘር) በሕፃናት መጠን ነሥቶ ተዋሕዶ፥ በተዋሕዶ ምንታዌ (ሁለትነት) ጠፋ። የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ኾነ።

ይህም ተዋሕዶ የአካል ተዋሕዶ ብቻ ሳይኾን የባሕርይም መኾኑን ሲያስረዳ ወንጌላዊው ዮሐንስ አካል ብቻ በሚጠራበት ስም፥ «ወልድ ሥጋ ሆነ» ሳይል አካልን በሕልውና እያገናዘበ ሥላሴን በሕልውና አንድ በሚያሰኝ በባሕርይ ከዊን ስሙ፥ «ቃል ሥጋ ሆነ» ብሎ አረጋግጦልናል።

የቅስብእትንም አካል እንጂ ባሕርይን አልተዋሐደም እንዳይባል፥ «ቃል ሥጋ ሆነ» ካለ በኋላ፥ «በእኛም አደረ» ብሏል። ሥጋ ኾነ ብቻ ብሎ ቢያቆም ኖሮ የእንስሳትም ሥጋ ሥጋ የሚባል በመኾኑ ሰብአዊ ባሕርይ ያለው ሰብአዊ አካልን እንደነሣ (እንደተዋሐደ) ባላስረዳም ነበርና። ሰብአዊ ባሕርይ ያለው ሰብአዊ አካልን እንደተዋሐደ በሚያስረዳ አነጋገር፥ «ቃል ሥጋ ኾነ በእኛም አደረ» ብሎ አረጋገጠ።

በተጨማሪም፥ «ቃል ሥጋ ኾነ» ብሎ ቢያቆም ኖሮ ውላጤን የሚያስተምሩ እነ አውጣኪን መግቢያ ቀዳዳ ባገኙ ነበረ። «በእኛ አደረ» ብቻ ብሎም ቢሆን ኖሮ «ኅድረትን» የሚያስተምሩ እነንስጥሮስ በማድጋ እንደተቀዳ ውኃ በብርሌ እንደ ተቀዳ ጠጅ ቃል በትስብእት (በሰውነት) አድሮ ሔደ ገብቶ ወጣ ብለው ማረጋገጫ



አድርገው ባቀረቡ ነበር። ዳሩ ግን፥ «ቃል ሥጋ ኾነ በእኛም አደረ» በማለት ተዋሕዶን መሠከረ።

በዚህም ቱሳሔ፥ ውላጤ፥ ኅድረት፥ ፍልጠት፥ ቡዐዴ፥ ሚጠት፥ ምንታዌ፥ ሳይኖርበት አካላዊ ቃል ርቀቱን ምልዐቱን ስፋቱን ሳይለቅ በተዐቅቦ ሥጋን ተዋሐደ።

## የተዋሕዶ ምሳሌዎች

### ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘጸ.3፥2፤ «የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው፤ እነሆም ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ። ሙሴም፥ ልሂድና ቁጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ።»

ሙሴ ያየውን ታላቅ ራእይ ስንመረምረው ብዙ የሚያስገርም ነገር እናገኝበታለን። በመሠረቱ እሳትና ቅጠል በምንም የማይገናኙ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች በመሆናቸው አንዱ በአንዱ ላይ ተጽእኖ ማድረጉ አይቀሬ ነው። ወይ እሳቱ ቅጠሉን ማቃጠል፥ ወይ ደግሞ ቅጠሉ እሳቱን ማጥፋት አለበት። ሙሴ ያየው ክስተት ግን ከነባራዊው ሁኔታ የተለየ እንግዳ ክስተት ነበር። ቅጠልና እሳት አንድ ሆነው ተዋሕደው እሳቱ ቅጠሉን ሳያቃጥል ቅጠሉ እሳቱን ሳያጠፋ እሳት እሳትነቱን ቅጠል ቅጠልነቱን እንደያዘ፥ ዳሩ ግን በተዋሕዶ አንድ ሆነው ተመለከተ።

ሙሴም ይህን እጹብ ድንቅ የተዋሕዶ ምሥጢር ያይ ዘንድ ወደ ኮሬብ ተራራ ወጣ። ይህ ግሩም ድንቅ ራእይ የሚያመለክተው የመለኮትና የሥጋን ተዋሕዶ ነበር። አካላዊ ቃል ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ መለኮት ሥጋን አልመጠጠውም ወይም አላጠፋውም። መለኮትም ተለውጦ ሥጋ ሳይሆን ዳሩ ግን መለኮት መለኮትነቱን ሥጋ ሥጋነቱን ሳይለቅ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ የመሆን ድንቅ ምሥጢር፤ ዛሬም እኛ እንደ ሙሴ ወደ አማናዊትዋ የኮሬብ ተራራ ወደ ቤተክርስቲያን ልንወጣ ይገባል። ይህን ድንቅ የተዋሕዶ ምሥጢር አይተንና ተረድተን እንድን ዘንድ።

ሥጋ:- የሚታየውን፥ የሚዳሰሰውን፥ ፈራሽና በሰባሽ የሆነውን እስከ ጊዜ መጽአት በመቃብር የሚቆየውን አካላችንን ማለት ነው።

እንግዲህ ሰው ከእነዚህ ከሁለቱ ተዋሕዶ የተፈጠረ ፍጡር ነው። ዳሩ ግን አንድ ሰው እነዚህ ሁለቱ ነገሮች በሕይወቱ ቢኖሩበትም ሁለት ሰው አይባልም። አንድ ሰው እንጂ በሕይወተ ሥጋው እያለ በሁለቱ መካከል ልዩነት አይኖርም። ይኼ የሥጋ ይኼ የነፍስ ሥራ ተብሎ የሚለይና የሚከፈል ሥራ ሊሠራ አይችልም። የሚሠራው ሁሉ በአንድ ሰው ነው።

መለኮት በነፍስ ሲመሰል ሥጋ ያው ሥጋ ነው። ስለዚህ የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ እንደ ሰው ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ ማለት ነው። አንድ ሰው ሲበላ ሲተኛ ሥጋዬ በላ ተኛ አይልም። እኔ ተኛሁ በላሁ እንጂ። ምክንያቱም ነፍስ የተለየው ሥጋ ሊበላ ሊጠጣ አይችልምና። ስለዚህ የበላው ሰውየው ነው። እንደዚሁም ሁሉ ሥጋ በላ መለኮት አልበላም ተብሎ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይነገርም። «ሥግው ቃል» በላ ይባላል እንጂ።

## ሥጋ በተዋሕዶተ መለኮት የባሕርይ አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል።

ዳን.7፥13፤ «በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ፤ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፤ ወደ ፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።» ሥልጣን ያለው መለኮታዊ ሥልጣን ነው። ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት መሆኑ ተነግሯል። ይህ የተነገረው ለመለኮት ብቻ ነው እንዳንል የሰው ልጅ ብሎ ገልጾልናል። ጌታ ራሱን የሰው ልጅ ብሎ ይጠራ እንደነበር በወንጌል ተጽፏል። ማቴ.16፥13። ማቴ.24፥30።

እንግዲህ ትስብእት (ሰውነት) በተዋሕዶ አምላክ አልሆነም ከተባለ ሕዝብና ነገድ ያመልኩታል ተብሎ ባልተጻፈ ነበር። ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ሲል ለሥጋ መሆኑን እንገነዘባለን።



መለኮትስ ሰጭ ነው እንጂ የሚሰጠው አይሻም። በተመሳሳይ ሁኔታ ጌታ ለሐዋርያቱ፥ «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» ማቴ.28፥18 ሲል ይህንን ሲያመለክት ነው። የሰማይና የምድር ሥልጣን ለመለኮት ሳይሆን ለሥጋ እንደተሰጠ የታወቀ ነው። እንግዲህ የሰማይና የምድር ሥልጣን ለሥጋ ከተሰጠው በእውነት አምላክ ነው። ከመለኮቱም ጋር ትክክል ነው።

መዝ.2፥7፤ «እግዚአብሔር አለኝ፥ አንተ ልጄ ነህ፥ ዛሬ ወለድሁህ» እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ አንድያ ልጁ ከድንግል ማርያም በሥጋ እንደሚወለድ ስለሚያውቅ አንድያ ልጁ የሚዋሐደውን ሥጋ በአካል በባሕርይ በፈቃድ አንድ እንደሆነ ሲያስረዳ ዛሬ ወለድኩህ አለ። በዮርዳኖስ ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ በሚጠመቅበት ጊዜ መለኮቱ ልጄ ነው ሥጋው ግን አይደለም አላለም። መለኮቱን ከሥጋው ጋር አዋሕዶ፥ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» አለ እንጂ። ማቴ.3፥17።

ኢሳ.9፥6፤ «ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል»

ሕፃኑን ጌታ የዘለዓለም አባት ብርቱ አምላክ የሰላም አለቃ ማለቱን ልብ ልንል ይገባል። ሥጋ በተዋሕዶ ከቃል ጋር አንድ ሆኗልና፥ ለመለኮት የሚነገረው ለሥጋ፥ ለሥጋ የሚነገረው ለመለኮት ሊነገር ቻለ። መለኮትና ትስብእት በባሕርይ ተዋሕዶ አንድ ከሆኑ በኋላ እንኳን በግብር በሐሳብ መለየት አይገባም።[5]

መዝ.46(47)፥5፤ «እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ አረገ...»

ሐዋርያት እያዩት ያረገው ከድንግል ማርያም የተወለደውን ጌታ ኢየሱስን ነው። መለኮትን ብቻ ማየት እንደማይቻል ሐዋርያው ተናግሯል። ዮሐ.1፥18። ዳሩ ግን መለኮት ሥጋን ተዋሕዶ ታየ። እንግዲህ መለኮትን የተዋሐደ ሥጋ ወደ ሰማይ ሲያርግ ሐዋርያት አይተዋል። ዳዊትም የሥጋን የባሕርይ አምላክነት ሲገልጥ እግዚአብሔር አረገ አለ።

[5] ምሥጢረ ሥላሴ

ዮሐ.9፥35፤ «...አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? አለው። እርሱም መልሶ፥ ጌታ ሆይ፥ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው? አለ። ኢየሱስም፥ አይተኸዋልም ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው አለው።»

እስቲ ይህን የጌታና የፈወሰውን ሰው ምልልስ በአንክሮ እናጢነው። ጌታ፥ «በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን?» ነው ያለው። ቃል የእግዚአብሔር ልጅ፥ ሥጋ የማርያም ልጅ ብለው ንስጥሮስና መሰሎቹ እንደሚናገሩት አለመሆኑን ጌታ ሊያስረዳን ነው። ሰውየውም መልሶ፥ «በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው?» የሚል ጥያቄ ጠየቀ። መልሱ፥ «አይተኸዋልም ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው» የሚል ነበር። ይህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረው እምነት። አካላዊ ቃል ረቂቅ ነው። ሥጋዊ ዓይን ሊያየው አይችልም። ሥጋን ተዋሕዶ ግን ታየ። እንግዲህ በተዋሕዶ የተገለጸው እርሱ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ነው።

ራእ.1፥17፤ «...አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።

ኢየሱስ ክርስቶስን ሁለት አድርገው የሚያምኑ ይህን እንዴት ይመለከቱታል። ፊተኛውና መጨረሻው ማን ነው? ቃል ነው ካሉ። ሞቼም ነበርሁ ያለው ቃል ነው ማለት ነው። መለኮት በባሕርይው ሟች አለመሆኑን መጻሕፍት ይመሰክራሉ። እኛ ግን ፊተኛውና መጨረሻው እኔ ነኝ ያለው ሥግው ቃል እንደሆነ እንመሰክራለን። እኛን ለማዳን ሲል በሥጋ ሞቷል። ዘላለማዊው እርሱ ሞተ፤ ሞትንም ድል አድርጐ ተነሣ።

ዮሐ.6፥51፤ «ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ» ከሰማይ የወረደ እንጀራ ያለው ከእመቤታችን የነሣውን ሥጋ አይደለምን? ወይስ ከሰማይ ሥጋውን ይዞት ወረደ ሊባል ነው? ከሰማይ የወረደው ቃል ብቻውን ነው። ግን ከሥጋ ጋር በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ በመሆን ይህን ሊናገር ቻለ።[6]

---

[6] ምሥጢረ ሥላሴ



በክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉ። የሥጋ ባሕርይ ለመለኮቱ ባሕርይ ይገዛል። ሥጋ የሥጋን ሥራ ይሠራል መለኮትም የመለኮትነትን ሥራ ይሠራል የሚለው እምነት የሁለት ባሕርይ ባዮች እምነት ነው። በእነርሱ እምነት ሰብአ ሰገል እጅ መንሻ ይዘው የሰገዱለት፤ ውኃውን ወይን ጠጅ ያደረገ፤ የሞቱትን ያስነሣ፤ ባሕርን የገሠጸ፤ ነፋሳትን ያዘዘ፤ በትንሽ እንጀራና ዓሣ ብዙ ሰዎችን ያጠገበ፤ በሽተኞችን ያዳነ፤ ፀሐይን ያጨለመ፤ ምድርን ያንዋወጣት። ይህን ሁሉ የብቻው የመለኮት ሥራ ነው ይላሉ። ሥጋን ከዚህ ሁሉ ውጭ ያደርጉታል።

በጨርቅ የተጠቀለለ፣ ወደ ምድረ ግብጽ የሸሸ፣ ከሣምራዊቷ ውኃ የለመነ፣ የደከመ፣ ለረኀቡ የበለስን ፍሬ የፈለገ፣ ላቡ እንደ ደም የተንጠፈጠፈ፣ የሞት ጽዋ ያልፍለት ዘንድ በፍርሃት የለመነ፤ የሰገደ፣ የጸለየ፤ ተይዞ የታሰረ፣ የተገረፈ፣ የተመታ፤ የተሰቀለ፤ የተቸነከረ፣ የሾህ አክሊል የተቀዳጀ፣ ጐኑን የተወጋ፤ የታመመ፤ የሞተ፤ የተቀበረ ይህ ሁሉ ለብቻው የሥጋ ነው ይላሉ፤ መለኮትን ከዚህ ሁሉ ውጭ ያደርጉታል።

ከዚህ እምነታቸው የተነሣ መለኮት ከትስብእት ያንሳል ይላሉ። ለዚህም ማስረጃ ይሆነናል ብለው የሚያቀርቡት ጥቅስ ራሱ ጌታ በመለኮቱ ከአብ ጋር ትክክል መሆኑን ሲናገር፥ «እኔና አብ አንድ ነን» አለ። ዮሐ.10፥30። ዳሩ ግን በሰውነቱ እንዲያንስ ግን «አብ ይበልጠኛል» አለ። በሥጋም ለአብ ሰገደ ይላሉ። ዮሐ.14፥28።

መንፈስ ቅዱስ ለአባቶቻችን ያመለከተውን የዚህን መልስ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

ክርስቶስ በመለኮትና በሰውነት በኩል በተዋሕዶ መንገድ ሁሉ አንድ ነው። ተአምራትን ያደረገው መለኮት ነው ድካም የተሰማው ሥጋ ነው አንልም። «አብ ይበልጠኛል» ማለቱም ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋን ተዋሕዶ በትሕትና ራሱን ዝቅ አድርጐ ስለ ሰዎች ልጆች ሲል በሥጋ ታመመ መከራን ተቀበለ ብሎ አብ በተለየ አካሉ እንዳልታመመና መከራን እንዳልተቀበለ እንዳልሞተ ለማስረዳት ነው።

መለኮት ከሥጋ የተለየና የወጣ እንዳይሆን ሥጋ ብቻውን ታመመ አንልም። እንደ ጴጥሮስ አነጋገር ሞተ በሥጋ ወሐይወ በመንፈስ

በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ እንላለን እንጂ። 1ጴጥ.3፥18።

ከታመመው በቀር ሕያው የሆነው ማነው? በሥላሴ ላይ አራተኛ አካል እንዳንጨምር አንዱ የሚታመም ሁለተኛው ግን የማይታመም ነው አንልም።

ስለዚህ ክርስቶስ በትህትናው አብ ይበልጠኛል አለ እንጂ በሥጋው ያንሳል በመለኮቱ እኩል ነው ለማለት አይደለም። አንድ ልጁ ሥጋን ተዋሕዶ ታመመ፥ ሞተ እንጂ። አብ ስላልታመመና ስላልሞተ አብ ይበልጠዋል ለማለት አናፍርም ሥጋ ከመለኮት ለብቻው ወዲያና ወዲህ ተለይቶ ሥጋን ብቻውን የፈረደበት አይደለም። ነገር ግን ሥጋ ከነፍስ ጋር እሳት ከብረት ጋር ዓይን ከብርሃን ጋር እንደሚዋሐድ መለኮት ከሥጋ ጋር ተዋሕዶ ነው እንጂ። ስለዚህ ደፍረን እግዚአብሔርን በሥጋ ሞተ እንላለን። አይሁድንም አምላክን የሰቀሉ እንላቸዋለን እንጂ ሥጋን የሰቀሉ አንላቸውም። ማርያምንም አምላክን የወለደች እንላታለን እንጂ ሥጋን ብቻ የወለደች አንላትም። የተሰቀለው ከእሷ የተወለደው ነውና የተሰቀለው እሱም ታሟልና የታመመው እሱም ሞቷልና የሞተው እሱም ተነሥቷልና እሱ ዳግመኛ ይመጣልና ከእሱ ጋርም ሌላ የለም። የታመመው እሱ ነው የተነሣውም እሱ ነው። አብ ይበልጠኛል የማለት ትርጓሜው አባቴ አይታመምም፤ አይሞትም፤ እኔ ግን እታመማለሁ እሞታለሁ ማለት ነው። ክርስቶስ በትሕትና ከአብ ብቻ ያነሰ አልነበረም። ከመላእክትም ጭምር እንጂ! መጽሐፍ «ከመላእክት ጥቂት ዝቅ አደረግኸው» እንዳለ ይህን ይዘን የመላእክትን ጌታ ከመላእክት ያንሳል ልንል እንደፍራለን? ዳሩ ግን የአነጋገሩ ትርጓሜ ሌላ ነው። ይኸውም ክርስቶስ ስለመታመሙና ስለሞቱ ነው። መላእክት አይታመሙም፥ አይሞቱምና። ጌታ ግን ሰውን ከማፍቀሩ የተነሣ ስለ ሰው ልጆች ፍቅር ሲል በትህትና በገዛ ፈቃዱ ከፈጠራቸው ከመላእክቱ አንሶ መጣ። (ዕብ.2፥9)

ከመላእክት ጥቂት አሳንስከው ስለተባለ ክርስቶስ ከመላእክት እንዳላነሰ እንዲሁም አብ ይበልጣል ስላለ በመለኮቱም ሆነ በሥጋው ከአብ አያንስም። ክርስቶስስ በትህትናው ከሐዋርያትም አንሷል። እግራቸውን እንደ አገልጋይ አጥቧልና። አጣቢ ከታጣቢው ያንሳል።



በትሕትና አንጻር ካልተመለከትነው ግን ተማሪዎች ከጌታቸው ይበልጣሉን? (ዮሐ.13፥5።) ዳግመኛም ጌታ በትሕትና ራሱን ዝቅ አድርጐ በዮሐንስ እጅ ተጠምቋል። አሁንም በሰው ሰውኛው አመለካከት አጥማቂ ከተጠማቂው ይበልጣል። ዳሩ ግን አጥማቂው ዮሐንስ ለአጠመቀው ክርስቶስ የመሰከረውን ማስተዋል ይገባል። «ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ ይበረታል።» ማቴ.3፥11።

እንግዲህ ጌታም፥ «ከእኔ አብ ይበልጣል» ማለቱ በትህትና ስለሚቀበለው መከራ መሆኑን ልንረዳ ይገባል። አይደለም በሥጋው ማንሱን የሚገልጥ ነው የሚሉ ከሆነ ግን ክርስቶስን ሁለት ከፍለው አንዱ የተሰቀለ ሌላው ያልተሰቀለ አንዱ የታመመው አንዱ ያልታመመው ወደ ማለት ያመራል። እንዲህ ብለው የሚያምኑ ከሆነ ደግሞ እንጨት ላይ የተሰቀለ ሥጋ ነው። መለኮት ሊሰቀል አይችልም ካሉ እኛም ፀሐይን ያጨለመ ማነው? የማንን ራቁት ለመሸፈን ነው ብርሃንዋን የሠወረችው? ጨረቃስ ደም የሆነ? ፈጣሪያቸውን ደም ተበክሎ ባዩት ጊዜ አይደለምን? ከዋክብትስ ከመንገዳቸው የወደቁ ለማነው? እንላቸዋለን።

ሥጋ ብቻውን ተሰቅሎ ቢሆንስ ፍጡራን ባልደነገጡም ነበር። እንደ ሁለቱ ወንበዴዎች በቆጠሩት ነበር። መላእክትም በመስቀሉ ሥር እንደ ቅጠል ባልረገፉም ነበር። እኛ ግን እንዲህ አናምንም። የሁሉ ፈጣሪ መለኮት የፈጠረውን ሥጋ ተዋሕዶ ለቅጽበተ ዓይን ሳይለይ ዓርብ ቀን በመስቀል ላይ ተሰቀለ እንላለን እንጂ።

አዳም የስህተትን ፍሬ በበላ ጊዜ እንደተራቆተ ጸጋውን እንደተገፈፈ ክርስቶስም ለእርሱ ሊክስ ነውና አመጣጡ ከመለኮቱ ሳይሆን ከልብስ ተራቆተ። በእርሱ መራቆት አዳም የተራቆተውን ጸጋ ተጎናጸፈ።

ስለዚህ ወታደሮች የፈጣሪያቸውን ልብስ በገፈፉት ጊዜ ፀሐይም የሚያበራ ብሩሕ ልብስዋን ገፈፈች። መለኮት በሥጋ እንደተሰቀለ ሥጋም በመለኮት ፀሐይን እንዳጨለመ እናምናለን! እንታመናለን። መለኮት በሥጋ እንደሞተ ሥጋም በመለኮት እንደተነሣ እናምናለን። መለኮት በሥጋ እንደተያዘ ሥጋ በመለኮት በተዘጋ ደጅ እንደገባ እናምናለን።

መተኛትም መቀስቀስም የሰውነት ሥራ፥ ነፋሳትንና ማዕበላትን
ገሥጾ ጸጥ ማድረግ የአምላክነት ሥራዎች መኾናቸው፥ ሠሪያቸው
ግን አንድ ክርስቶስ መኾኑ የማይካድ ነገር ነው።

ኬልቄደናውያን እንደሚሉት የመለኮትን ሥራ መለኮት
የሰውነትን ሥራ ሰውነት ተከፋፍለው የሚሠሩት ኾኖ ቢኾን
ነፋሳትንና ማዕበላትን መገሠጽ በተለይ የመለኮት ሥራ ስለኾነ
ሰውነትን ባልቀሰቀሱትም ነበር። እንግዲህ የተኛውና የተቀሰቀሰው
ማዕበላትንም ጸጥ ያደረጋቸው ያው አንዱ ክርስቶስ ከኾነ አንድ
እርሱን ሁለት አድርጎ ገዢና ተገዢ ተማላጅና አማላጅ ማለት
እንደምን ይቻላል። አይቻልም።[10]

አንድ አካል አንድ ባሕርይ መኾኑንም ሲያስረዳ ቅዱስ ጴጥሮስ
ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ገዝፎ የሚያየውን አካል፥
«አንተ የሕያው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ክርስቶስ ነህ
ብሏል» በዚህም እምነቱ ብፅዕናን አግኝቶበታል፤ ተመስግኖበታል።
ማቴ.16፥17–20።

በዮሐንስ ወንጌል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምራቁ ጭቃ
አድርጎ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ዓይኑን ቀብቶ እንዳዳነው
ተጽፏል። ዮሐ.9፥6።

ምራቅ የሰውነት ገንዘብ ነው። ለመለኮት ምራቅ አለውን? ወደ
መሬት እንትፍ ብሎ በመራቅ ዓይንን ከፈጠረ ሰውነት መለኮትን
ተዋሕዶ የመለኮትን ባሕርይ ባሕርይ አድርጓል ማለት ነው። በዚህ
ተዋሕዶ መካከል ይኽ ምራቅ ተፉ ይኽ አዳነ ሊባል አይችልም።

ክርስቶስ በፈቃድ ከባሕርይ አባቱ ጋር አንድ ነው። «የላከኝን
ፈቃድ ላደርግ ነው እንጂ የራሴን ፈቃድ ላደርግ አይደለም።»
ለክርስቶስ የአብን ፈቃድ የሚቃወም ሌላ ፈቃድ እንደሌለው በግልጽ
አስረድቶናል። ዮሐ.3፥13።

---

10 መድሎተ አሚን።

## የጌታ ሰው መሆን በብሉይ ኪዳን ተጽፏል

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ በድንገት የሆነ አይደለም። አስቀድሞ ትንቢት አናግሮ ሱባዔ አስቆጥሮ ነው የመጣው። ነቢያት የጌታን ሰው መሆን በትንቢት መስታወትነት ተመልክተው በተለያየ ምሳሌያዊ አገላለጽ ተናግረዋል።

የተነገረው ትንቢት የተመሰለው ምሳሌ አያሌ በመሆኑ ከብዙው በጥቂቱ ከምሉ በከፊሉ ለመጥቀስ እንወዳለን።

ዘፍ.3፥5፣ «በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ። እርሱ (የሴቲቱ ዘር) ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።»

አዳምና ሔዋን በምክረ ከይሲ (እባብ) ተታለው ዕፀ በለስን በበሉ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ከላይ የተገለጸውን ተናገረ። ሴቲቱ የተባለችው ለጊዜው ሔዋን ስትሆን በፍጻሜው ግን ንግሥተ ሰማይ ወምድር የሆነችውን ቅድስት ድንግል ማርያምን ያመለክታል። የሴቲቱ ዘር የተባለው የድንግል ማርያም ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የሴቲቱ (የድንግል ማርያም) ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንዶ[11] (እባብ) የተባለውን የዲያብሎስ ራስ በመስቀሉ ላይ ተሰቅሎ ቀጥቅጦታል። የሰው ልጆችንም ከዲያብሎስ ባርነት አርነት አውጥቷል። ገላ.4፥4። ቆላ.2፥14።

ዘፍ.3፥22፣ «እግዚአብሔር አምላክም አለ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ!»

አዳም ዕፀ በለስን በበላ ጊዜ ትዕዛዘ እግዚአብሔርን በመጣሱ ዘላለማዊ ሞት ተፈረደበት። ከዚህ የዘላለም ሞት የሚያድነው ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም ባለመኖሩ አዳም ከሕገ

---

[11] ራእ.20፥2። ራእ.12፥3–16።

እግዚአብሔር በወጣ ጊዜ ከሦስቱ አካል አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ ፍጹም ሰው እንደሚሆን በሥላሴ ዘንድ የተወሰነ (የታወቀ) በመሆኑ «አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆኗ» ብሎ አካላዊ ቃል ሥጋን እንደሚዋሐድ ትንቢት ተነገረ። የዘመኑ ፍጻሜ ማለትም በእግዚአብሔር ዘንድ የተቀጠረው ቀነ ቀጠሮ ሲደርስ በተናገረው ቃል መሠረት በተፈጥሮዋ አዳማዊት ከሆነችው ከድንግል ማርያም እግዚአብሔር ቃል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ፍጹም ሰው ሆነ። «ዳግማዊ አዳም» ተባለ።

ዘፍ.22፥13፤ «አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጐ ሠዋው።»

እግዚአብሔር አብርሃምን ሊፈትነው ልጁ የስሐቅን በሞሪያም ምድር በአንድ ተራራ ላይ እንዲሠዋው አዘዘው። አብርሃምም ለፈጣሪው ያለውን ታማኝነት ይገልጽ ዘንድ በስተርጅና የወለደውን ልጁ ይስሐቅን የመሥዋዕቱን እንጨት አሸክሞ ወደ ተባለው ስፍራ ተጓዘ። በተራራውም ላይ እንጨት ረብርቦ ልጁን ይስሐቅን በመሠውያው በእንጨቱ ላይ አጋድሞ ሊሠዋው ሲል እግዚአብሔር የአብርሃምን ጽናት አይቶ በልጁ ምትክ የሚሠዋውን በግ በዱር ውስጥ አሳየው። ይህ በግ በይስሐቅ ምትክ በመሠውያው እንጨት ላይ ተሠዋ። ቀንዱ በዕፀ ሳቤቅ (በሐረግ) ተይዞ በዱር የተገኘው በግ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው።

በጉ በይስሐቅ ምትክ እንደተሠዋ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም (በአዳም ምትክ) ስለ አዳም ተገብቶ (ተወክሎ) መሥዋዕት ሆኖአል። በጉ የተሠዋው በሞሪያም ምድር በተራራ ላይ ነው። ጌታም የተሰቀለው በቀራንዮ ኮረብታ ላይ ነው። ዕፀ ሳቤቅ የድንግል ማርያም ምሳሌ ሲሆን በጉ ቀንዱ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ በዱር እንደ ተገኘ ሁሉ አማናዊው በግ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ለሰው ልጆች ሁሉ ቤዛ ይሆን ዘንድ በከብቶች ግርግም ተገኝቷል። ኋላም በቀራኒዮ ኮረብታ ላይ ተሰቅሏል። ልበ አምላክ ዳዊት፥ «እነሆ በኤፍራታ ሰማነው በዱር



ውስጥም አገኘነው» ብሎ ትንቢት እንደተናገረ። መዝ.131(132)፥6–11።

ኤፍራታ ቤተ ልሔም ነች። ጌታም በነቢያት አድሮ እወርዳለሁ እወለዳለሁ ሲል ሰማነው። የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ አገኘነው ማለቱ ነው። አንድም በኤፍራታ (በቤተ ልሔም) ቱወልዶ በግዕዘ ሕፃናት ሲያለቅስ ሰማነው፥ በኃል ተጥሎ በጨርቅ ተጠቅሎ አገኘነው ሲል ነው።

«ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን» ተዘግታ ወደነበረችው ገነት በጌታ መሥዋዕትነት እንገባለን፤ የመንግሥተ ሰማያት ወራሾችም እነሆናለን ብሏል።

ዘፍ.29፥1–12፤ «ያዕቆብም ተነሥቶ ወደ ምሥራቅ ሰዎች አገር ሄደ። በሜዳውም እነሆ ጉድጓድን አየ፥ በዚያም ሦስት የበጎች መንጎች በላዩ ተመስገው ነበር፤ ...ያዕቆብም የእናቱን ወንድም የላባን ልጅ ራሔልንና የአጎቱን የላባን በጎች ባየ ጊዜ፥ ቀረበ ከጉድጓዱም አፍ ድንጋዩን ገለበጠ፥ የአጐቱን የላባን በጎችንም አጠጣ።»

ብሉይ ኪዳን የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ መሆኑ የታወቀ ነው። በዘመነ ብሉይ ይፈጸም የነበረው ለወደፊት ሊፈጸም ላለው ምሳሌ ነው። በዚህ መሠረት ያዕቆብ የጌታ፥ እረኞች የነቢያትና የካህናት፥ በጐች የምእመናን፥ ድንጋዩ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ፥ውኃው የዘላለም ሕይወት (ጽድቅ) ምሳሌ ነው።

ያዕቆብ በጉድጓዱ አፍ ላይ ተመስገው ለነበሩት በጐች ራሔል እስክትመጣ ድረስ ድንጋዩን አንስቶ እንዳላጠጣ ራሔል በመጣች ጊዜ ግን ለስድሳ ሰው የማይቻለውን ትልቅ ድንጋይ ለብቻው አንስቶ በጐቹ እንዲጠጡ እንዳደረገ ሁሉ፥ ጌታም ለብዙ ዘመን የሕይወትን ውኃ ተጠምተው የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስን ድንጋይ የሚያነሣላቸውን ለሚሹት ሰዎች መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን ያጠፋው መጀመሪያ ድንግል ማርያምን አዘጋጅቶ ነው። በቅድሚያ እርስዋ ተወለደች። ከእርስዋ እርሱ ተወለደ። ራሔል ለነዚያ ውኃ ተጠምተው ለነበሩት በጐች ውኃ መጠጣት ምክንያት እንደሆነች ሁሉ ድንግል ማርያምም ለፍጥረተ ዓለሙ መዳን ምክንያት ሆናለች።

በጉድጓዱ ዙሪያ በጎቻቸውን ይዘው የመጡ ብዙ እረኞች ነበሩ። አቅማቸው ውስን በመሆኑ የሌሎችን እረኞች መምጣት ነበር የሚጠባበቁት። ምክንያቱም ድንጋዩ ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ ብዙ ሆነው ነውና የሚያነሡት።

እንዲሁም ሁሉ የቀደሙት የብሉይ ኪዳን ካህናትና ነቢያት ይጠብቁአቸው ከነበሩት ሰዎች መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን እርቀው የሕይወት ውኃን ሊያጠጡአቸውና ሊያረኩአቸው አልተቻላቸውም። እንኳን ለሌላው ሊያጠጡ ስለራሳቸውም ሲናገሩ፥ «ጽድቃችን እንደ መርገም ጨርቅ ሆነ ነው» ያሉት። ኢሳ. 64፥6።

ዳሩ ግን የተወሰነው ጊዜ ሲደርስ የድንግል ማርያም ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በፈጸመው የመሥዋዕትነት ተልእኮ የመርገመ ሥጋና የመርገመ ነፍስ ምሳሌ የሆነውን ድንጋይ ከሕይወታችን ፈንቅሎ ጣለው። ዘላለማዊ ማየ ሕይወትንም አጠጣን። ነፍሳችን በጽድቅ ውኃ ረካች! ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ምስጋና ይግባውና።

ዘጸ. 12፥1–51። እግዚአብሔር አምላክ ወገኖቹ እስራኤልን ከግብፅ የባርነት ሕይወት ነፃ ሊያወጣቸው በወደደ ጊዜ ሙሴንና አሮንን ወደ ፈርዖን ዘንድ ይልካቸው ነበር። ሙሴና አሮንም በፈርኦን ፊት ብዙ ተአምራትን በማድረግ እግዚአብሔር አምላካችን ሕዝቤን ልቀቅ ይልሃል ይሉት ነበር። የፈርዖን ልብ ግን እንደ አድማስ አለት ደንድኖ ነበርና፥ «እግዚአብሔር የሚባል አምላክ አላውቅም እስራኤልንም አልለቅም» ብሎ በትዕቢቱ ጸና። እግዚአብሔርም በግብፃውያን ላይ በኵረ ሞትን እንደሚያመጣ ለነሙሴ ተናገረ። ይኸውም የመጀመሪያ ልጆችን በሞት መቀሰፍ ነው። ሙሴም በኵረ ሞት እስራኤልን እንዳያገኛቸው ሊያደርጉት የሚገባቸውን ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጠየቀ።

እግዚአብሔር አምላክም ነውር የሌለበት ማለትም ጠጉሩ ያላረረ፥ ቀንዱ ያልከረከረ፥ ጥፍሩ ያልዘረዘረ ንጹሕ የአንድ ዓመት ጠቦት እንዲያዘጋጁ ለእስራኤል ሁሉ ተናገረ አለው። እያንዳንዱ ቤተሰብ አንድ ጠቦት እንዲያዘጋጅ ታዘዘ።

በአሥረኛው ቀን በጉን ይገዛሉ። እስከ አሥራ አራተኛው ቀን ያስሩትና ባሥራ አራተኛው ቀን እንዲሠውት ይታዘዛሉ። የበጉን ደም ደግሞ መቃንና ጉበኑ ላይ እንዲረጩ እንዲሁም የበጉን ሥጋ ጥሬውን ወይም ቅቅሉን ሳይሆን ጥብሱን ብቻ እንዲበሉ ታዘው ነበር። ይህ ሁሉ ሊመጣ ላለው ምሳሌ ነው።

ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ጠቦት ምክንያተ ኃጢአት ለሌለበት ለንጹሐ ባሕርይ አምላክ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። በጉን በአሥረኛው ቀን ገዝተው እስከ አሥራ አራተኛው ቀን አሥረው እንዲሠዉት እንደታዘዙ ሁሉ የጌታም ምክረ ሞቱ በአሥር ተጀምሮ በአሥራ አራተኛው ቀን ተፈጽሟል።

የበጉን ደም መቃኑና ጉበኑ ላይ እንዲረጩ የታዘዙት ከሚመጣው መቅሰፍት ይድኑ ዘንድ ነው። ምክንያቱም መልአከ ሞት የበጉ ደም በተረጨው ቤት ውስጥ እንዳይገባ ታዟልና። ዛሬም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ በሰጠው በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምኖ ሥጋውንና ደሙን የተቀበለ ሁሉ የዘላለም ሞት አይሞትም፤ ሞተ ነፍስ አያገኘውም። ዮሐ.3፥16። ሠራዊተ አጋንንትም አይቀርቡትም።

«የበጉን ሥጋ ጥሬውንና ቅቅሉን አትብሉ» የተባሉት በጉ የጌታችን ምሳሌ በመሆን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ያዳነን ጌታን ፍጡር የሚሉ አይሁድና ተረፈ አይሁድ እንደሚነሱ ይታወቃልና፥ ጌታን ፍጡር አትበሉ የምትበሉት ሥጋ የምትጠጡት ደም የፍጡር ነው አትበሉ ለማለት ሲሆን፥ «ጥብሱን ግን ብሉ» ሲል በእሳት የተመሰለ መለኮት የተዋሐደውን የመለኮትን ሥጋ ነው የምንበላው ብለን የመለኮትን ሥጋና ደም እንደምንበላ እንደምንጠጣ ሲያመለክተን ነው።

«አታሳድሩ ካንዱ ወደ አንዱ አትውሰዱት» መባሉ ምሳሌነቱ የጌታ ሥጋው በመስቀል ላይ ሳለማደሩ ዕለቱኑ ወደ መቃብር መውረዱን የሚያመለክት ሲሆን እንዲሁም የመቃብሩ ስፍራ ከተሰቀለበት አቅራቢያ እንደሚሆን የሚያመለክት ነው። መካነ መስቀሉና መካነ መቃብሩ ቅርብ ለቅርብ ናቸው። እንዲሁም ካሣ ሳይፈጸም ሳለማደሩ ምሳሌ ነው። ዛሬም በቤተክርስቲያናችን

1ኛ. ሙሴ ጐልማሳ በሆነ ጊዜ ግብፃዊውን ገድሎ በአሸዋ ውስጥ ቀብሮ ዕብራዊውን እንዳዳነ ጌታም የአዳም ባላጋራ የሆነውን የሰይጣን (ዲያብሎስን) ሥራ (ሥልጣን በመስቀል ላይ ሽሮ) ገድሎ (አዳምን ነፃ አውጥቶታል) ሕይወትን ሰጥቶታል።

2ኛ. ሙሴ 430 ዓመት ያህል በባርነት ቀንበር ተይዘው በግብፃውያን ሲገዙ የነበሩትን እስራኤላውያን በእርሱ መሪነት በእግዚአብሔር ተአምራት ከግብፃውያን የአገዛዝ ቀንበር ነጻ እንዳወጣቸው ሁሉ ጌታም 5500 ዘመን በሲኦል በዲያብሎስ የባርነት ቀንበር ሲገዙ የነበሩትን ነፍሳት ነፃ አውጥቷል። ዘጸ.14፥31። 1ጴጥ.3፥18።

3ኛ.ሙሴ ወገኖቹን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲመራ ከፊታቸው የገጠማቸውን የኤርትራ ባሕር ለሁለት ከፍሎ እንዳሻገራቸው (ዘጸ.14፥21) ጌታም የኃጢአት ባሕርን ለሁለት ከፍሎ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ተጋርዶ የነበረውን የበደል (የጠብ) ግድግዳ አፍርሶ ነፍሳትን ከሲኦል ወደ ገነት አግብቷል።

4ኛ. ሙሴ በሲና ተራራ ላይ የቃል ኪዳን ጽላት ለመቀበል አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾሟል። በጾሙም ጊዜ ምግብ አልበላም፤ ውሃም አልጠጣም። ዘዳግ.9፥9። ጌታም በገዳመ ቆሮንቶስ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾሟል። በነዚያ ቀናት እንጀራ አልበላም፤ ውኃም አልጠጣም። ሉቃ.4፥3።

5ኛ. ሙሴ ከእርሱ በፊት የነበሩት አበው ይመሩበት የነበረውን ሕገ ልቡና ከእግዚአብሔር በተቀበለው በሕገ ኦሪት ለውጦታል። ያንንም ሕግ እንዲጠብቁ ትዕዛዝ በማስተላለፍ የማይጠብቁ ቢኖሩ ዕዳ፥ ፍዳ እንደሚመጣባቸው አስተምሯል፤ አስጠንቅቋል። ጌታም በኦሪት ተሰውራ የነበረችውን ሕገ ወንጌልን አስተማረ፤ እንዲፈጽሟትም አዘዘ። በሕገ ወንጌልም የማይመሩ ዕዳ፥ ፍዳ እንደሚጠብቃቸው አስጠንቅቋል። ዘጸ.20፥1–26። ማቴ.5፥7።

6ኛ. ሙሴን ወገኖቹ ሊታዘዙት ፈቃደኞች እንዳልነበሩ ሁሉ (የሐዋ.7፥39።) እንዲሁም ለጌታ የገዛ ወገኖቹ ሊታዘዙለት ሊቀበሉት ፈቃደኞች አልነበሩም። ዮሐ.1፥12።



7ኛ.ሙሴ፥ «የጸጋ አምላክ» እንደሆነ (ዘጸ.7፥11) ጌታ ደግሞ፥ «የባሕርይ አምላክ» ነው። 1ዮሐ.5፥20።

8ኛ. ሙሴ ስለወገኖቹ ራሱን አሳልፎ እስከመስጠት ፈቃደኛ እንደነበረ ሁሉ (ዘጸ.32፥32) ጌታም በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖራቸው ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ ሰጥቷል። ዮሐ.3፥15። ፊል.2፥8።

9ኛ. እስራኤላውያን ማራ ወደ ተባለችው ስፍራ በደረሱ ጊዜ ውኃ ጥም አቃጠላቸው። ጠጥተው ከጥማቸው እንዳይረኩ የማራ ውኃ መራራ ነበርና ሊጠጡት አልቻሉም። ምን እንጠጣለን ብለው ወደ ሙሴ አቤት አሉ። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር አመልክቶ እግዚአብሔር በነገረው መሠረት በውኃው ላይ እንጨት ጣለበት። መራራ የነበረው ውኃ እንጨቱ ባረፈበት ጊዜ ጣፋጭ ሆነ። እስራ ኤልም ውኃውን ጠጥተው ረኩ፤ ተደሰቱም። ዘጸ.15፥22–26።

ጌታም 5,500 ዘመን በመርገመ ሥጋ በመርገመ ነፍስ (በኃጢአት) ተይዘው (ኃጢአት በምረት ይመሰላል) የጽድቅን ውኃ ተጠምተው የዘላለምን ሕይወት ውኃ የሚያጠጣቸውን ሲሹ በእን ጨት መስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን አፍሶ የዘላለም የሕይወትን ውኃ ለተጠሙ ወገኖቹ አጠጥቷል። (ዮሐ.4፥14። ዮሐ.6፥53–59።)

10ኛ. ሙሴ መናን ከደመና አዘነመ (አወረደ)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምስት እንጀራ አበርክቶ ሴቶችና ሕፃናት ሳይቆጠሩ አምስት ሺህ ርኁባን ወንዶችን አጥግቦ አሥራ ሁለት ቅርጫት ሙሉ እንዲተርፍ አደረገ። ዘጸ.16፥4። ማቴ.14፥17–21።

11ኛ. ሙሴ እስራኤላዊ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከነገደ ይሁዳ የተወለደ እስራኤላዊ ነው።

ዘኁል.24፥17፤ «አየዋለሁ፥ አሁን ግን አይደለም፤ እመለከተዋለሁ፥ በቅርብ ግን አይደለም፤ ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል፥ ከእስራኤል ኃጢአትን ያርቃል።»

ይህን ትንቢት የተናገረው የቢዖር ልጅ በለዓም ነው። በለዓም በእርሱ ዘመን ሳይሆን ለወደፊት የ ሚሆነውን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን

ልደት አስቀድሞ ተናገረ። ከያዕቆብ ዘር የወጣው ኮከብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም እውነተኛው ኮከብ (ብርሃን) ነው። ዮሐ.8፥12።

2ነገሥ.2፥20፤ «እርሱም፥ አዲስ ማሰሮ አምጡልኝ፥ ጨውም ጨምሩበት አለ ያንንም አመጡለት። ውኃው ወዳለበቱም ምንጭ ወጥቶ ጨው ጣለበትና፥ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ ይህን ውኃ ፈውሼዋለሁ ከዚህም በኋላ ሞትና ጭንጋፍ አይሆንበትም አለ። ኤልሳዕም እንደተናገረው ነገር ውኃው እስከ ዛሬ ድረስ ተፈውሶአል።»

አዲሱ ማሰሮ ንጽሐ ነፍስ፥ ንጽሐ ሥጋ፥ ንጽሐ ልቡና አንድ አድርጋ የያዘችው የንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ሲሆን በውስጡ የተጨመረው ጨው ደግሞ በድንግል ማኅፀን የተወሰነው የጌታ ምሳሌ ነው። ከማሰሮው ውስጥ ያወጡትን ጨው በውኃው ላይ በጣሉት ጊዜ ውኃው ተፈወሰ፤ ሞትና ጭንጋፍ ቀረ፤ ከዚያ በፊት ግን ውኃውን የሚጠጣ ሁሉ ይሞት ነበር። ሴቶችንም ያስወርዳቸው ነበረ። ፈውሱም ፍጹም እንደሆነ ተገልጾአል።

በጨው የተመሰለው ጌታችንም ኃጢአትን (መርገምን) ከእኛ ሕይወት አስወግዶ በምትኩ ሕይወትን አድሎናል። በእርሱ አምነው በቃሉ መሠረት ለሚኖሩ ሞተ ነፍስ አያገኛቸውም።

2 ነገሥ. 6፥6፤ «ኤልሳዕም እንጨትም ቆርጦ በዚያ ጣለው፥ ብረቱም ተንሳፈፈ።» የነቢያት ልጆች ኤልሳዕን ቤት ጠብቦናል በማለት መምህራቸው ኤልሳዕን በማስከተል ለቤቱ ምሰሶ የሚሆን እንጨት ቆርጠው ለመምጣት ምሳራቸውን ይዘው ወደ ዮርዳኖስ አመሩ። እየቆረጡ ሳለ የአንዱ ምሳር (መጥረቢያ) ከዛቢያው ላይ ወልቆ ብረቱ ውኃ ውስጥ ገባ። በዚህ ጊዜ፥ «ጌታዬ ሆይ ወየው ወየው የተዋስሁት ነበረ» ብሎ ጮኸ። ኤልሳዕም የወደቀበትን ቦታ ጠይቆት (ቅርፊት) ቆርጦ ወደ ውኃው ውስጥ ጣለ። ቅርፊቱም ውኃው ውስጥ ሰጥሞ ብረቱን ይዞ ወጣ።

መስጠም የማይችለው ቅርፊት/እንጨት ሰጥሞ መንሳፈፍ የማይችለውን ብረት እንዲንሳፈፍ ማድረጉን ማስተዋሉ ይገባል።



ይኸንንም በምሳሌነቱ ስናጤነው መሞት የማይገባው መለኮት በሥጋ ሞቶ ሞት የሚገባውን አዳምን የማዳኑ ምሳሌ ነው።

መዝ.2፥6፤ «እኔስ በመመስገኛው ተራራ በጽዮን ንጉሥ ሆኜ ተሾምኩባቸው...እግዚአብሔርም አለኝ፥ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ»

ይህ አነጋገር ሥጋ የባሕርይ አምላክ የሆነው በማኅፀነ ማርያም መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። አባቶችም፥ «የሥጋ እርገት በማኅፀን የቃል እርገት በአርባ ቀን» የሚሉት ይህን ይዘው ነው። አማናዊት ጽዮን ድንግል ማርያም ናት። የመመስገኛው ተራራ የተባለችም እርሷው ናት። ጌታ ማኅፀንዋን ዓለም አድርጎ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ተመስግኖበታል።

«አንተ ልጄ ነህ» የሚለው አባባል ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ከአብ ያለእናት መወለዱን የሚያስገነዝብ ሲሆን፥ «ዛሬ ወለድኩህ» ሲል ደግሞ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ 5,500 ዘመን ሲፈጸም ከድንግል ማርያም ያለአባት መወለዱን ያረጋግጣል። ስለዚህ የአብ ልጅ የድንግል ማርያም ልጅ ነው። «ወልደ አብ ወልደማርያም በተዋሕዶ ልደት ከበረ» እንዳለ መጽሐፍ።

መዝ.21(22)፥11–18። በዚህ አነጋገር ዳዊት ለወደፊት በጌታ ላይ የሚፈጸመውን ድርጊት ቁልጭ አድርጎ በራሱ አስመስሎ ተናግሮታል። ቃሉን አንድ በአንድ እንመርምረው።

«ብዙ በሬዎች ከበቡኝ» በበሬዎቹ የተመሰሉት አይሁድ ናቸው። ምክንያቱም ላም (በሬ) ሳሩን አጭዶ ውኃውን ገድቦ የሚመግበውን ጌታውን ወግቶ እንዲገድለው አይሁድም ኅብስት አበርክቶ የሚመግባቸው፥ ድውይ የሚፈውስላቸው፥ ሙት የሚያስነሳላቸው ፈጣሪያቸውን ጠልተው ተመቅኝተው ሰቅለው ገድለውታልና። «የሰቡትም ፍሪዳዎች ያዙኝ» የሰቡት ፍሪዳዎች የተባሉት በምቀኝነት መንፈስ የሰቀሉት አይሁድ ናቸው። «ደናቁርት የሚሆኑ አይሁድ ያዙኝ» ሲል ነው። ሰው የሚደነቁር ልቡ ሲሰባ ነውና ስብህን (መስባትን) የድንቁርና ምልክት አድርጎት ነው። ሐዋርያው ያዕቆብ፥ «በምድር ላይ ተቀማጥላችኋል በሴሰኝነትም ኖራችኋል

ወጣ። ...ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀ፤ በበቀለም ጊዜ መቶ እጥፍ አፈራ። ሉቃ.8፥8።

እያንዳንዱ ሕግ እንደ መቶ ተቆጠረ። መቶን በአሥር ስናበዛው አንድ ሺ ይሆናል። የውኃው ጥልቀት ቁርጭምጭሚት ደረሰ ሲል የትምህርታቸውን ድክመት መናገር ነው። ገና ጥንተ ስብከት ነውና።

2. በዘመን ነገሥት፥ በነገሥታት አድሮ አሥርቱ ቃላትን አስተማረ። የውኃው ጥልቀት ጉልበት መድረሱ የትምህርታቸውን ብርታት መናገር ነው። በዘመን ነገሥት ቤተ መቅደስ ተሠርቷል። ነቢያት፥ ካህናት በዝተዋል።

3. በካህናት አድሮ አሥርቱ ቃላትን አስተማረ። የውኃው ጥልቀት ወገብ መድረሱ የትምህርታቸውን ብዛት፥ ጥንካሬ፥ የጉባኤያቸውን ስፋት መናገር ነው። ሰባ ሊቃውንት ወደ ግብፅ ወርደው አሪት ነቢያትን ከዕብራይስጥ ወደ ፅርዕ ቋንቋ መልሰዋልና (ተርጉመዋል) እስከ ወገብ መድረሱ ምሳሌነቱ በትምህርት ልጅ መውለዳቸውን ያሳያል።

4. ራሱ ጌታ በነቢያት፥ በካህናት አድሮ ሳይሆን በሥጋ ተገልጦ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ነቢያት ያስተማሩትን ያንኑ ሕግ (አሥርቱ ቃላትን) አስተማረ። ይህንን የሚጠቁመን የወንዙ የጉን ርዝመት በአራተኛው ያው አንድ ሺ ነው የተለካው። ምክንያቱም ጌታ አዲስና ልዩ የሆነ ትምህርት አላመጣም። ራሱ እንደተናገረው፥ «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም» ማቴ.5፥17።

ዳሩ ግን በሦስቱ ዘመናት ፍጹምነትን ያላገኘው ሕግ በጌታ ፍጹምነትን አገኘ። በሥጋ ተገልጦ ባስተማረ ጊዜ ትምህርቱ ጉድለት የሌለበት ምሉዕ፥ ፍጹም ሆነ። ጸጋ እግዚአብሔር በምልዓት ተሰጠ።

ከመቅደሱ የወጣው ውኃ ወደ ሙት ባሕር ተጉዞ ሙት ባሕር ገብቶ የሙት ባሕርን እንደፈወሰው የረከሰውን እንደቀደሰው ሕዝቅኤል ጽፏል።

ያ ሙት ባሕር (የጨው ባሕር) በውስጡ ብዙ ሙታንን ይዟል። ይህም የዓለም ምሳሌ ነው። ዓለም በፍዳ የተያዙ ዘላለማዊ ሞት



የተፈረደባቸውን የአዳም ልጆችን በውስጥዋ አቅፋ ደግፋ ይዛለችና። ዳሩ ግን ከአማናዊት ቤተ መቅደስ ከድንግል ማርያም የተወለደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ወደ ረከሰው ዓለም መጣ። በደሙም ቀደሰው፤ በውስጡ ያሉትን ሙታንንም ሕያዋን አደረጋቸው። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» ዮሐ.3፥16።

ሕዝቅኤል፥ «ወንዙም በሚመጣበት ያለው ሁሉ በሕይወት ይኖራል» እንዳለው ሁሉ ያን የሕይወት ውኃ የሚልስ የሚቀምስ ሁሉ ከሞት ይድናል። እርሱም ማየ ሕይወት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። «እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።» ዮሐ.6፥48። የሕይወት ውኃ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ የባሕርይ አምላክነቱን የሚያምኑትን ሁሉ ከሞተ ነፍስ ያድናቸዋል።

በመዋዕለ ትምህርቱም, በየመንገዱ ዳር ተቀምጠው፥ «የዳዊት ልጅ ሆይ ማረን» እያሉ የለመኑትን ሁሉ፥ «ልትድን ትወዳለህን? ልትድኚ ትወጃለሽን?» እያለ ፈቃዳቸውን በመጠየቅ ከደዌ ሥጋ ፈውሷቸዋል። ዛሬም እርሱ በሚመላለስበት መንገድ ላይ (ሃይማኖት) ቆመው፥ «የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ማረን» የሚሉትን ሁሉ ከሞተ ነፍስ ያድናቸዋል። ወንዙ (ውኃው) በሚመጣበት ያለው ሁሉ በሕይወት ይኖራል ተብሏልና።

አጥማጆችም ይበዛሉ እንደተባለው ምእመናንን በወንጌል መረብነት ከዓለም ኃጢአት አጥምደው ወደ አማናዊትዋ ሐመር ቤተ ክርስቲያን የሚያስገቡ ሐዋርያት በዝተዋልና። «መረብ ይዘረጋል» እንደተባለው የወንጌል ትምህርት በመላው ዓለም ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ተዘርግቷል። ማቴ.13፥47።

ረግረጉና ዕቋሪው ውኃ ግን ከምረት አይፈውስም፤ መራራ እንደሆነ ይኖራል እንጂ። እንደተባለው ሁሉ ዛሬም ወንጌልን ዲቃላ ሕግ በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም ፍጡር፥ ወልደ ዮሴፍ የሚሉ አይሁድና ተረፈ አይሁድ (የአይሁድ ግብር አበሮች) ከደዌ ነፍስ አይፈወሱም፤ ከብለየት አይታደሱም። ርጉማን ተብለው ለገሃነም ይሰጣሉ እንጂ። ማቴ.8፥12። 1ዮሐ.2፥23።

መልካቸውን እየለዋወጡ አሉ፤ ከቤተ ክርስቲያን ጨርሰው አልጠፉም።[13]

ጳውሎስ ሳምሳጢ:- ይህ ሰው የተወለደው በታናሽ እስያ በሶርያ አካባቢ ነው። የነበረበትም ዘመን ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን ሳምሳጢ የተባለውም በሀገረ ስብከቱ ነው። (ሳምሳታ ኤጺስ ቆጶስነት የተሾመበት አገር ናት) ጳውሎስ ሳምሳጢ በምሥጢረ ሥጋዌ ብዙ የተሳሳተ ሰው ነበር። «ከማርያም የተወለደው ዕሩቅ ብዕሲ ነው፤ ስሙም ኢየሱስ ይባላል። ዕሩቅ ብእሲ ኢየሱስ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ በአብ ሕልውና ውስጥ የነበረው ዝርው ቃል (አካል የሌለው ቃል) መጥቶ አደረበት። ከዚያ በኋላ ራሱ ባደረገው ተጋድሎና በሠራው ትሩፋት በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ ለመባል በቃ» ይላል።

በመስቀል ላይ ስለታየው አምላካዊ መግቦት ሲናገር፥ «ዝርው ቃል የሚለው ወልደ እግዚአብሔር እስከ መከራ መስቀል ድረስ ዕሩቅ ብዕሲ (አምላክነት የሌለው ሰው) ከሚለው ከማርያም ልጅ ከኢየሱስ ጋር አብሮት (አድሮበት) ኖረ። ዳሩ ግን የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ዝርው ቃል የእግዚአብሔር ልጅ ተለይቶት ሄደ» ይላል።[14]

አርጌንስ:- የተወለደው በ185 ዓ.ም በእስክንድርያ ነው። የመጀመሪያ ትምህርቱን የተማረው በእስክንድርያ ትምህርት ቤት ነው። በትምህርት ኰትኩቶ ያሳደገው ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ነው።

በምሥጢረ ሥጋዌ በአንቀጸ ተዋሕዶ ቃል ሥጋን በመዋሐዱ ምንም ዓይነት ውላጤ እንደሌለበት ያስተምራል። ክርስቶስ የተናገራቸው ሁሉ የራሱ «የሥግው ቃል» እንደ ሆኑም ይመሰክራል። ነገር ግን ክርስቶስ ስለ ራሱ በተናገራቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ሁለት ባሕርያትን የሚመለከቱ ሁለት ስሜቶች አሉ ብሎ ያምን ነበር። ይህ አስተሳሰቡ በአንቀጸ ተዋሕዶ ምንታዌን (ሁለትነትን) ለሚያስተምሩ ምንጭ ሆኖአል።

[13] St Athanasius and Incarnation, የቤተክርስቲያን ታሪክ።

[14] የቤተክርስቲያን ታሪክ።



ክርስቶስ የሰውን ዘር ለማዳን ለመዋጀት መምጣቱን ያምናል። ይሁን እንጂ «ማዳን» የሚለው ቃል በአርጌንስ አተረጓጐም በታወቀ፥ በተወሰነ ዘመን በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ በጎልጎታ የተደረገው ብቻ ሳይሆን ከዘመነ ሥጋዌም በፊት እግዚአብሔርን ማወቅ ለሰው ዘሮች መገለጥ የክርስቶስ ሥራዎች ነበሩ ይል ነበር።

በአርጌንስ ግምት የክርስቶስ ሥጋዌ ወይም የማዳን ተልእኮው ኃጥአንን ለማዳን፥ ለጻድቃን ግን አምላካዊ ምሥጢርን ለማስተማር ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ የወደቀውን የሰው ዘር ለማዳን ከነበረው ተፈላጊነት ይልቅ ራሱን ለማዳን ለሚጣጣረው ሰው መሪና አስተማሪ እንዲሆን የነበረው ተፈላጊነት ያመዝን እንደነበር ያምን ነበር።

ስለ ክርስቶስ የመጨረሻ ሁኔታም ከትንሣኤና ከዕርገት በኋላ የሥግው ቃል አካል ወደ መለኮትነት ተለወጠ ብሎ ያምን ነበር።[15]

አርዮስ:- በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በ257 ዓ.ም ገደማ በአፍሪቃ ሰሜን ክፍል በምትገኝ በሊብያ ተወለደ።

አርዮስ:- እግዚአብሔር ወልድን በባሕርይው ፍጡር ነው ብሎ ያስተማረ መናፍቅ ነው። ፍጡር እንደ መሆኑ መለወጥ የባሕርዩ ነው። ማዘን፥ መተከዝ፥ መደሰት፥ መበሳጨት፥ ሰው መሆንም ራሱ በአርዮስ ግምት የባሕርዩን ተወራጅነት ያመለክታል። ቃል ሰው ለመሆን የመጣው የመታዘዝ ግብር ቢኖርበት ነው ይላል። ባጭሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍጡር ነው ብሎ በገሃድ ያስተማረ ከሀዲ ነው።[16]

ይህ ሰው በ325 ዓ.ም በኒቂያ ጉባኤ ተወግዟል።

አቡሊናርዮስ:- በታናሽ እስያ በሎዶቅያ ተወልዶ ያደገ ሰው ነው። አቡሊናርዮስ ፻ፕላቶንን ፍልስፍና መሠረት በማድረግ ሰውን ለማወቅ ለማሰብ የምታስችለው ነባቢት ልባዊት ሕያዊት ነፍስ ከመለኮት ተከፍላ የመጣች ናት ብሎ ያምን ስለነበረ በምሥጢረ

[15] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ።

[16] The Nature of Christ

አመለካከታቸው ድጋፍ አድርገው ከሚያቀርቡአቸው ምክንያቶች፥ «ምሉዕና ዘላለማዊ አምላክ መንፈስ ሆኖ ሳለ ከሚሞት ውሱን ከሆነ አካል ጋር ተዋሕዶ አንድ ሆነ ማለት እንዴት ይቻላል? ይኼ እግዚአብሔርን እንደ መስደብ ነው» ይላሉ።

እነርሱ ይህን ቢሉ እኛ ግን ምሉዕና ዘላለማዊው አምላክ የፈጠረውን ሥጋ ተዋሕዶ ለመገለጥ የሚሳነው ነገር ባለመኖሩ (ዘፍ.18፥19፤ ሉቃ.1፥37፤) ለሰው አእምሮ የማይቻል የሚመስለውን እርሱ በፈቃዱ አደረገ። የሚታየውንና የማይታየውን ግዙፉንና ረቂቁን የፈጠረ እርሱ አይደለምን? እንግዲህ በፍጥረቱ ላይ የፈለገውን ለማድረግ ምን ያግደዋል? የፈጠረውን ሥጋ ተዋሕዶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ መገለጥ ለእግዚአብሔር ይሳነዋል?

በእርግጥ እግዚአብሔር በሰማይና በምድር የመላ፥ የሌለበት ቦታ የሌለ፥ ምሉዕ ስፉሕ አምላክ ነው። ሰው ደግሞ ውሱን ነው። ግን ምሉዕ አምላክ ከውስኑ ሥጋ ጋር ተዋሕዶ መገለጡ (መታየቱ) ምሉዕነቱን፥ ስፉህነቱን አላስቀረውም። ተለውጦም ሰው የሆነ አይደለም። ዳሩ ግን ምሉዕነቱን ሳይለቅ ሰው ሆነ እንጂ። ይህን ለማድረግ ደግሞ የሚሳነው ነገር የለም።

በሰማይና በምድር የመላው ጌታ እግዚአብሔር ከእግዚአብሔርነቱ ሳይዛነፍና ሳይለወጥ በተዋሕዶተ ሥጋ ሰው ሆነ። ቀደም ብለን ለዚህ አስረጂ የሚሆኑ ምሳሌዎችን የመሰልን ቢሆንም ለእጽንኦተ ነገር ሌላም እናክል።

ዙሪያችንን ከቦ የሚገኘው ከባቢ አየር (Atmosphere) ዜናን በሚያሰራጩ ሞገዶች (Transmission Waves) የተሞላ ነው። እነዚህን ሞገዶች (Waves) በአየር ላይ እያሉ በሥጋዊ አይናችን አናያቸውም፤ በጆሮአችንም አንሰማቸውም። ነገር ግን በቴሌቪዥንና በሬዲዮን እናየዋለን፤ እንሰማዋለን። ይህ ማለት ግን ማለትም በከባቢው አየር የሞላውን የሬዲዮና የቴሌቪዥን ሞገድ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ አየነው ሰማነው ማለት በእኛ ብቻ ተወስነ ከከባቢው አየር ጠፋ (ለቀቀ) ማለት አይደለም።



## ምሳሌው ከምሥጢረ ሥጋዊ ጋር ያለው ግንኙነት

ሞገድ በዓይናችን አናየውም፥ በጆሮአችን አንሰማውም። እንግዲህ ከእኛ የተፈጥሮአችን ድክመትና (ውሱንነት) የተነሣ ባለማየታችንና ባለመስማታችን የተነሣ የለም ልንል አንችልም። መኖሩን በተለያየ ሁኔታ አረጋግጠናል።

- የማይጨበጠው የማይታየው ሞገድ ተጨባጭ ሆኖ በተንቀሳቃሽ ምስል በቴሌቪዥን እንዲሁም በመቅረጸ ድምፅ በሬዲዮ ይደርሰናል። በተመሳሳይ ሁኔታ (ልዩነት መኖሩን ግንዛቤ ውስጥ በመክተት) ገናናው አምላካችን የማይታይ የማይጨበጥ መንፈሳዊ አካል ሆኖ ሳለ ዳሩ ግን እኛን ለማዳን ፍቅሩን ለመግለጽ የሚጨበጥና የሚዳሰሰውን የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ ታየ፤ በሥጋ ተገለጠ።

- ሞገዱ በቴሌቪዥን መታየቱ በሬዲዮ መደመጡ በከባቢው አየር ያለውን ሕልውና አጣ ወይም ተወገደ ማለት እንዳልሆነ በቴሌቪዥን ሲታይ በሬዲዮ ሲደመጥ በከባቢው አየር ሞልቶ እንዳለ እንደሆነ ሁሉ፥ እንደዚሁም እግዚአብሔር ወልድም የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ በተገለጠ ጊዜ በሰማይ የለም ማለት አይደለም። በመንበረ ክብሩ ከአብ ከባሕርይ አባቱ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ በሕልውና ነበር። ዮሐ.3፥13።

## ሰው የሆነው ምሉ መለኮት ነውን?

በመለኮት ተከፍሎ አለመኖሩን በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን ላይ ገልጸናል። እንግዲያው በመለኮት ተከፍሎ ከሌለ፤ ምሉዕ መለኮት ሰው ሆነ ከተባለ አብና መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆነዋል ማለት ነው?

ሰው ሆኖ የተገለጸው አካላዊ ቃል በተለየ ሁኔታው ነው እንጂ አብና መንፈስ ቅዱስ ሥጋን አልተዋሐዱም። እንዲህ ከሆነ መለኮት በተከፍሎ ነዋ ሰው የሆነው? ወይም አብና መንፈስ ቅዱስ ከመለኮት ውጭ ናቸው ማለት ነው?

መለኮት በተከፍሎ ሳይሆን ምሉዕ መለኮት ነው ሥጋን የተዋሐደው። አብና መንፈስ ቅዱስም ከመለኮትነት ውጭ አይደሉም። ዳሩ

## ቅዱሱ ሰው በመሆኑ አልረከሰም

እግዚአብሔር በቅድስናው ወደር የማይገኝለት ቅዱስ መሆኑ የታመነ ነው። ዳሩ ግን ቅዱሱን ጌታ ከረከሰውና ከጎሰቆለው ከአዳም ሥጋ አዋሕዶ ሰው ሆነ ብሎ ማመንና ለሌላውም ማስተማር የአምላክን ሉዐላዊነትና ቅዱስነት የሚጻረር ነው የሚለውን አመለካከት አጥብቀን እንቃወማለን።

ተቃውሟችንም መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ እንጂ በጭፍን አመለካከት ተጋርደን የምናቀርብ አይደለንም።

ሐዋርያትን የመሰለው ታላቁ የቤተክርስቲያናችን አባት ቅዱስ አትናቴዎስ የቅዱስ እግዚአብሔር ሥጋን መዋሐድ፤ እንኳን የእግዚአብሔርን ቅድስና ሊያረክሰው የረከሰውን የአዳምን ሕይወት እንደቀደሰው ሲያመለክት፥ «እንደ ፀሐይ ብሩሕ ጽሩይ የሆነ በስነ ፍጥረት መካከል አይገኝም። የፀሐይ ብርሃን በሁሉም ሥፍራ ይኖራል። በቆሻሻ ነገር ላይም ያርፋል። ዳሩ ግን ንጹሕነቱን (ብሩህነቱን) ያረፈበት ቆሻሻ አያጎድፈውም። እንደውም ቆሻሻውን በማድረቅ መጥፎ ሽታውን በትነት ያጠፋዋል። ቦታውንም ያጠራዋል። እንደዚሁም በብርሃን የተመሰለ ጌታ ወደ እኛ በኃጢአት ወደረከስነው መጣ። ቅዱሱ ጌታ በርኩሳኑ መካከል ተገኘ። ንጹሑ ጌታ በቆሻሻዎቹ መካከል ተገኘ። ገናናው ጌታ የደካሞቹን ባሕርይ ባሕርይው አደረገ። በእሱ ቅድስና የእኛ ርክስትና ጉስቁልና ተወገደ። ሥጋችንን ተዋሕዶ በመካከላችን በመገኘቱ ከኃጢአት እድፋችን ነፃን እንደገና ተፈጠርን እንጂ የእኛ ኃጢአተኝነት የእኛ መርከስ እርሱን አላረከሰውም።»

## ኃያሉ ስለ እኛ ደካማ ሥጋን መዋሐዱ ኃያልነቱን አልሻረውም

እግዚአብሔር አምላካችን ኃያል አምላክ ሲሆን ሰው ሆነ፡ የደካማው የሰው ልጅን ባሕርይ ባሕርይው አደረገ። እንደ ሰው ተራበ፥ ተጠማ፥ ደከመ። ይህ ሁሉ ግን በፈቃዱ የሆነ እንጂ በባሕርይው ድክመት ኖሮበት አይደለም። ሰው ሆኖ የተገለጠው ጌታ ሁሉን የሚችል ከሃሌ ኩሉ '(ominipotent) ነው። ስለዚህ ሁሉን ቢያደርግ የባሕርይ ችሎታው ነው። የደካማውን የሰውን ሥጋ



ተዋህዶ በድካሙ ሰውን ነፃ ቢያወጣው በኃይሉ ሰውን ቢያድነው ሁሉም የእርሱ ነው።

ለእግዚአብሔር አምላካችን ባሕርይ የማይስማማው ብቸኛ ነገር ኃጢአት ነው። ከኃጢአት በስተቀር ሁሉን ለማድረግ ይቻለዋል።

## እግዚአብሔር ወልድ ሰው የሆነበት ዓላማ

1. እርሱንቱን በተጨባጭ ሁኔታ እንድናውቀውና እንድናምነው በመፈለጉ ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ሰው ደግሞ ሥጋ ነው። እግዚአብሔር የሚኖረው በሰማይ ነው፤ ሰው ደግሞ የሚኖረው በምድር ነው። እንግዲህ የሰው ልጅ የአምላኩን ፊት ለማየት ቢሻም ይኸ ምኞቱ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ሊሳካና እውን ሊሆን አልቻለም። ስለዚህ የአምላኩን ፊት ማየትን ያልቻለው የሰው ልጅ አምላኩ ሰው ሆኖ በመካከሉ በተገኘ ጊዜ አየው በሚገባም አወቀው።
2. በአዳም ላይ የተፈረደበትን ሞት ለማስቀረት ነው። «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው።» ሮሜ.6፥23።

በኃጢአት ወድቃ ዘላለማዊ ሞት የተፈረደባትን የአዳም ሕይወት ከዚህ ፍርድ ነፃ ሊያደርግ የሚችል ከመለኮት በስተቀር ማን ይኖራል? የሞተውን የፈረሰውን የበሰበሰውን የሰውን ሰውነት ከተቀበረበት የሚያነሳ ከመለኮት በቀር ማን ይኖራል? ስለዚህ አካላዊ ቃል ሰው ሆነ።

3. ስለ አዳም ፍጹም ካሣ ለመክስና አዳምና ልጆቹን ከእዳ ነጻ ለማድረግ ነው።
4. «እሾህን በሾህ» እንደሚባለው ሰይጣንን በሥጋ ተሰውሮ ድል ሊያደርገው ነው።
5. አምላክነቱ አባትነቱ ለሁሉም መሆኑን ያስረዳ ዘንድ ነው።

ከላይ የተጠቀሱትን ዘርዝር አድርገን እንመልከታቸው።

የሰው ዘር ሁሉ የዚህ አመጽ ተካፋይ በመሆን በእዳ ተይዟል። ስለዚህ ካሹ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው መሆን ይኖርበታል።

መ. ኃጢአት የሌለበት ንጹሐ ባሕርይ መሆን አለበት። ያለበለዚያ እርሱም ኃጢአተኛ ከሆነ ስለ ኃጢአተኞች እዳ ከፍሎ ሊያድን አይችልም። እንዲያውም ለራሱም የሚክስለት ያስፈልገዋል።

ሠ. ፈጣሪ መሆን አለበት። ወደ ወህኒ የተጋዙትን ነፍሳት ነጻ ማውጣት ብቻ ሳይሆን የረከሰው የሰውን ተፈጥሮ ይቀድስ ዘንድ ይገባዋልና።

ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሊያሟላ የሚችል ከፍጡር ወገን ሊገኝ ስለማይችል ራሱ ፈጣሪ የእጁን ፍጥረት አዳምን ለማዳን ራሱ ስለአዳም ካሣ ከፍሎ በሐዲስ ተፈጥሮ ከእንደገና ሊፈጥረው አምላካዊ ጉዞ ወደ ሰዎች ልጆች አደረገ።

ቀዳማዊ ቃልም ከድንግል የምትናገር የምታውቅ ነፍስ ያላቸው ሥጋን ነሣ።[21] በዚህ መንገድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ስቃይና መከራ ያስወግድ ዘንድ ወደ ወገኖቹ መጣ። ቅዱስ አትናቴዎስ እንደተናገረው፥ «የእኛ የሆነውን ወስዶ (ከኃጢአት በስተቀር) የእርሱ የሆነውን ሰጠን።» ከዚህ ውጭ ሌላ መፍትሔ ሊኖር አይችልም። ብቸኛውና ፍጹም የደኅንነት መንገድ ይኸው ብቻ ነው።

## በምሥጢረ ሥጋዌ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሆነናል።

በጥፋታችን ከፈጣሪያችንና ከአምላካችን አንድነት ተለየን። ዳሩ ግን ርኅሩኅ አምላካችን ስለ እኛ ተገብቶ (ተወክሎ) በበደልነው በደል ሁሉ እርሱ ክሶ ታረቀን። ከአብና ከመንፈስ ቅዱስም ጋር አስታረቀን። በእርሱ መሥዋዕትነት (የማስታረቅ አገልግሎት) በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ተጋርዶ የነበረው የጠብ ግድግዳ ፈረሰ። ሰውን ከአምላክ ለይቶት የነበረው የኃጢአት መጋረጃ ለሁለት

[21] ሃይማኖተ አበው ገጽ 240።



ተከፈለ። ማቴ.27፥51። እግዚአብሔርና ሰው አንድ ሆኑ። የጠፋው ልጅ ተገኘ፤ ወደ አባቱ እቅፍ ገባ።



ነብየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ አስቀድሞ እንደተናገረው፥ «ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» ኢሳ.7፥14። የተባለው ይፈጸም ዘንድ ድንግል አማኑኤል ብላ ስሙን ሰየመችው። ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው ማቴ.1፥23።

እግዚአብሔር ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነሥቶ ሰው ሆነ፤ ተዋሐደን፤ ተዋሐድነው። ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ አደረገን። «አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ። እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤» ዮሐ.17፥22።

## በምሥጢረ ሥጋዌ ሰይጣን ድል ሆኖአል።

አዳምና ሔዋንን በእባብ ሥጋ ተሰውሮ ወደ ገነት በመግባት ያሳሳታቸው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ድል ሆኖአል። ሰይጣን በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ አዳምን እንዳሳሳተ ሁሉ ጌታም የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ ደካማ መስሎ ሰይጣንን ወደ መስቀሉ በማቅረብ ከመስቀሉ እግር ሥር ጥሎ ቀጥቅጦታል።

እግዚአብሔር ሥጋዌውን ከሰይጣን ሰውሮ ነው ያደረገው። ሰው ሆኖ በምድር የተገለጠው አምላክ ወልደ አምላክ ለመሆኑ ሰይጣን እርግጠኛ አልነበረም። ብዙ ጊዜ ግራ ይጋባ ነበር። ጌታም ሰይጣንን ያዘናጋ ዘንድ አንድ ጊዜ ታላላቅ ተአምራትን ሲያደርግ በሌላ ጊዜ ደግሞ ደካማ ሆኖ ሲራብ፣ ሲጠማ፣ ሲያንቀላፋ፣ አላዋቂ መስሎ ሲታይ ሰይጣን የጌታን ማንነት ለማወቅ ግራ ተጋብቶ ነበር።

በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ ሰይጣንን ፍጹም አዘናግቶ ወደ መስቀሉ ሊያቀርብና ድል ሊያደርገው ስለፈለገ፣ «አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ» የሚለውን ጩኸት አሰማው። ማቴ.27፥46። በዚህ ጊዜ በጥርጥር ማዕበል ይዋዥቅ የነበረው ዲያብሎስ ይህን በሰማ ጊዜ፣ «ፍጡር ነው» ብሎ አረጋግጦ እንደሌላው ሰው ነፍሱን በሲኦል ሥጋውን በመቃብር ሊቆራኝ ወደ ጌታ ቀረበ። ጌታም ከመስቀሉ አጠገብ ሲደርስ ሰውሮበት የነበረውን መለኮታዊ ክብሩን ገለጸለት። እልፍ አእላፋት መላእክት ከመስቀሉ እግር ሥር ተነጥፈው ጌታን ሲያመሰግኑ አይቶ ፈራ፤ ደነገጠ። ወደ ኋላው ሊመለስ ሲል በነፋስ አውታር (ገመድ) በእሳት ዛንጅር አሠረው።

በዚህ ጊዜ መለፍለፍ ጀመረ። ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ድል የነሣኝ ምእመናንን ይነጥቀኝ ዘንድ ሥልጣን የተሰጠው ይህ ማነው? ከእኔ ሕግ ልዩ የሆነ ነፍሳትን ከእኔ እጅ እየማረከ የሚወስድ ይህ ማነው? እንደ ኃጢአተኛ በመስቀል ተሰቅሎ ያለኃጢአት ሞቶ የወደድኩትን እንዳላደርግ የከለከለኝ ልቀርበው የማይቻለኝ ይህ ማነው? የተሰጡኝን ነፍሳት ሁሉ ወደ ክብር ወደ ልዕልና ይወስዳል እንጂ በእግሬ እርግጥ በእጄ ጭብጥ አድርጌ ይዣቸው በነበረ በነፍሳት ላይ እንዳልሠለጥን ያደረገኝ ይህ ማነው?



ለካስ እኔ ሳላውቀው ነው እንጂ እሱስ ሰማያዊ ኖሯልና እያለ ቀባጠረ፤ ወይኔ ከእንግዲህ ወዲህ በርሱ ካመኑ ሰዎች በማንም ላይ ክፉ ማድረግ አይቻለኝም። ማንንም ለመጉዳት ሥልጣን የለኝም ብሎ ፈጽሞ ድል መሆኑን መሰከረ።[22]

ቅዱስ ጳውሎስም «ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ?» ብሏል 1ቆሮ.15፥55።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የሰይጣንን በመስቀል ላይ ድል መሆን ሲናገር፣ «ከባላጋራችን ተንኰል የተነሳ ሰው በመሆኑ የዕዳችንን ደብዳቤ አጠፋልን፤ ከመካከላችንም አራቀው፤ በመስቀሉም ቸነከረው።» ብሏል። ቆላ.2፥14።

ጌታም ለሐዋርያቱ ከመሰቀሉ በፊት አስቀድሞ እንዲህ ብሎአቸው ነበር፣ «ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም፣ የዚህ ዓለም ገዥ (ሰይጣን) ይመጣልና፤ በእኔ ላይም ምንም አያገኝም፤» ዮሐ.14፥30።

## በምሥጢረ ሥጋዌ ክፋትና ሥቃይ ተወግደዋል

ፈጣሪያችን ሥጋችንን ተዋሕዶ ሰው በመሆኑ በኃጢአት ከመውደቃችን የተነሣ በሁለት ነገሮች እንሠቃይ ነበር። አንደኛው፣ በኃጢአት የጐሰቆለው ተፈጥሮአችን ነው፤ ሁለተኛው፣ በእኛ ላይ የታወጀው የሞት ፍርድ ነው።

እነዚህ ሁለቱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተወግደውልናል። እርሱ በእኛ ፈንታ ስለ እኛ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ–በእኛ ላይ የተፈረደውን ጽኑ ፍርድ ያስቀር ዘንድ። አካሉንም ከአካላችን አዋሕዶ በአዲስ ተፈጥሮ ፈጠረን፤ ከቀደመው በደላችን አነፃን። ስለዚህ በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አብረን እንቀበራለን፤ ደግሞ ትንሣኤውን በኩር አድርገን በተሐድሶ እንነሣለን።

እርሱ አምላካችን ወደ እኛ መጣ። በአርአያው የፈጠረንን እኛን ከረከሰንበት ከጉስቁልና ሕይወት ነፃ ሊያወጣን የቀደመውን

[22] ትምህርተ ኅቡአት።

ተፈጥሮአችንን ሳያጠፉ ያንኑ አድሶ እንደገና ፈጠረን (ወለደን)። «አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ተውት በአእምሮም ፍጹም የሆነውን አዲሱን ሰው ልበሱት ፈጣሪውን የሚመስለውን» ቆላ.3፥9–10።

ሰው ዳግመኛ ከእግዚአብሔር እንደተወለደና በአዲስ ተፈጥሮ እንደተፈጠረ የሚያምን ብቸኛ ሃይማኖት ክርስትና ነው። በተዋሕዶ ተገልጦ ይህን ያደረገ ደግሞ ብቸኛውና ሁሉን ቻይ አምላክ ነው፤ ስሙም እግዚአብሔር ነው።

ከጌታችን መወለድ በፊት የነበሩ ወገኖች በስቃይና በመከራ ውስጥ ማለፋቸው የታወቀ ነው። ይህ መከራና ስቃይ የኃጢአት ውጤትና ቅጣት ነበር። ስቃዩ በአዳም መውደቅ ወደ ሰዎች ሁሉ የተዛመተ ነው። ዛሬ ግን በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው መከራ የኃጢአት ቅጣት ሳይሆን ክርስቶስን የመምሰላችን ምልክት ነው። «ሊከተለኝ የሚወድ ማንም ቢኖር መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ።» ማር. 8፥34። «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁና»

የክርስቶስ በመሆናችን የመከራው ተካፋይ ልንሆን ይገባል። «በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ ይህም ለእነርሱ የጥፋት፥ ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው፤ ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤ በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፥ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና።» ፊልጵ.1፥28–30።

«የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱም ኃጢአት አላደረገም፥ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ በኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት (መስቀል) ላይ ተሸከመ፣ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል።» 1ጴጥ.2፥22–25።



«እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፤» የሐዋ.5፥41።

በኃጢአት ሳይሆን በሃይማኖታችን ምክንያት የሚገጥመን መከራ ሁሉ በውስጥ ደስታን፥ ንጽሕናን፥ ብቁነትን፥ ዓለምን ማሸነፋችንን፥ ሰይጣንን ድል ማድረጋችንን የሚያሳይ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር፥ «አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፥ ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ» ብሏል። ቆላ.1፥24።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አባል ነች፤ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ ተከታዮቹ ደግሞ የአካሉ ክፍሎች ናቸው። ራስ የሚቀበለውን መከራ ሌላውም አካል ይቀበላል። ስለዚህ በክርስትና ሕይወት የሚገጥመን መከራ የኃጢአት ውጤት አለመሆኑን መረዳት ይኖርብናል። የክርስቶስ የአካሉ ክፍሎች መሆናችንን የሚያስረዳና የሚያረጋግጥልን በመሆኑ መከራውን በደስታ መቀበል ይገባናል።

## ሰው ሆኖ በመገለጡ የሁሉም አባት መሆኑን ገለጠ

የሚታየውና የማይታየው ፍጡራን ሁሉ የተፈጠሩት በእርሱ ነው። እርሱ ጌታችን የሁሉ አስገኚ፥ የሁሉ ፈጣሪ ነው። አምላክነቱ ለአይሁዶች ብቻ አለመሆኑን ያስረዳ ዘንድ ወደዚህ ዓለም መጣ። የእስክንድርያው ቄሌምንጦስ እንደገለጸው፥ «እግዚአብሔር አባትነቱና አዳኝነቱ ለአይሁድ ብቻ አይደለም፥ ለሰው ዘር ሁሉ እንጂ። ስለዚህ የሰው ዘርን ሁሉ ወደ እርሱ ሊመልስና ሊያድን መጣ። መሥዋዕትነቱም ለአንድ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ ሳይሆን ለሁሉምና ለሁልጊዜ ነው።»[23]

በማዕከለ ምድር ላይ የተሰቀለው ጌታ የዓለም መድኃኒት መድኃኒዓለም ነው። የተሰቀለው ለአንድ ግለሰብ አይደለም። ወይም ለተወሰኑ ሕዝቦች አይደለም። ለመላው የሰው ዘር ነው። ለዚህም ነው

---

[23] Man and Redemption

መድኃኒዓለም የሚባለው። እንዲህ ሲባል ግን የሚያምነው የማያምነው ሁሉ ይድናል ማለት አይደለም። እርሱ ምርጫ ሳያደርግ ለሁሉ ተሰቅሏል። ነገር ግን አዳኝነቱን የሚክዱ ድኅነትን አይኖራቸውም። ለሚያምኑት ግን ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ዮሐ.3፥16–18።

## ሥጋው በመቃብር አልቀረም

የክርስቶስ ሥጋ በሦስተኛው ቀን በመቃብር አለመገኘቱ ለአይሁድና ለተረፈ አይሁድ እስከዛሬ ድረስ የማይፈታ እንቆቅልሽ ቢሆንባቸውም ለእኛ ትንሣኤውን ለምናምን ክርስቶሳውያን ግን የሕይወታችን ብርሃን ነው ጳውሎስ እንደተናገረው «የተኛህ ንቃ ከሙታንም ተለይተህ ተነሥ ክርስቶስ ያበራልሃል» ኤፌ.5፥14። ጌታችን ሞትን ድል አድርጐ በመነሣቱ እኛም በደሙ የተዋጀን ልጆቹ ሞተን እንደማንቀር ትንሣኤ እንዳለን አበሠረን። «ሞት! እንግዲህ ሥልጣንህ ወዴት አለ መቃብርስ አሸናፊነትህ ወዴት አለ?» 1ቆሮ.15፥56።

የክርስቶስን ማንነት ባግባቡ ያልተረዱ ቢጽ ሐሳውያን የስህተት መምህራን አንድ የሆነውን ክርስቶስን ሁለት በማድረግ ሥጋው በመቃብር ሲቀር፤ መለኮት ግን ተነሣ በማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ከንቱ የፍልስፍና ነገር ይናገራሉ። ዳሩ ግን መለኮት ከሥጋ፥ ሥጋ ከመለኮት ከተዋሐዱ በኋላ ሥጋው ሞቶ በመቃብር ቀረ። መለኮቱ ግን ከሥጋው ተለይቶ ተነሣ የሚሉ ሁሉ ቁጥራቸው ክርስቶስን ከካዱት ከነአርዮስ ከነንስጥሮስ ነው። ክርስቲያን ተብለውም ሊጠሩ አይችሉም።

እኛስ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አጋዥነት በቅዱሳን አበው ጸሐፊነት የተጻፉትን ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት በማድረግ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን እንናገራለን እንዲህ ስንልም የአምላክነትንም የሰውነትንም ሥራ ባንድ ፈቃድ ባንድ ሥልጣን ስለሠራ ነው እንጂ በየራሳቸው የቆሙ ያልተዋሐዱ በኹለትነት የሚቆጠሩ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው ብለን አይደለም።



እንግዲህ ጌታ በዕለተ ዓርብ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ በለየ ጊዜ። መለኮት ከሥጋም ከነፍስም አልተለየም። በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ በሲኦል ተግዘው ለነበሩ ነፍሳት ነፃነትን ሰብኮላቸዋል። በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር ወርዷል። በዚህም ሙስና መቃብርን (በመቃብር ፈርሶ በስብሶ መቅረትን) አጥፍቶልናል።

ስለዚህ በሦስተኛው ቀን መለኮትን የተዋሐደ ሥጋ ሌላ አስነሺ ሳይፈልግ ሞትን ድል አድርጐ ተነስቷል። ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን ሲገልጽ፥ «በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ነው» ብሏል 1ጴጥ.3፥19። በመለኮቱ ሕያው የሆነ ጌታ ሞትን ድል አድርጐ ተነሣ።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጐ መነሣቱ በመጽሐፍ ቅዱስ በስፋት ተገልጹአል። ለማስረጃነት የሚከተሉት ተጠቅሰዋል።

ማቴ.28፥5፤ «እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደምትሹ አውቃለሁና ከዚህ ግን የለም እሱ እንደተናገረው ተነሥቶአል ነገር ግን ኑና ተቀብሮበት የነበረውን ቦታውን እዩ።»

በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ከተቀበረበት ሞትን ድል አድርጐ መነሣቱን መልአኩ የክርስቶስ ሥጋው ያረፈበትን መቃብሩን ሊያዩ ለመጡት ሴቶች አረጋግጦላቸዋል። ስለዚህ ሥጋው በመቃብር ቀርቷል የሚሉ ሁሉ ተሳስተዋል።

ማር.16፥6፤ «...አትደንግጡ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ ተነሥቶአል በዚህ የለም እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ»

ስለ እኛ ብሎ የተሰቀለው የአብ ልጅ የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ሞታችንን አጥፍቶ በትንሣኤው ትንሣኤ እንዲኖረን ማድረጉን ወንጌላውያኑ አስትምረዋል። «የተሰቀለው፥ የሞተው እርሱ ተነሥቶአል» ከሚል ምስክርነት ሌላ ምን ይምጣ።

ሉቃ.24፥3፤ «የጌታ ኢየሱስን ሥጋ አላገኙም...ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም»

ሥጋው በመቃብር ቀርቷል አልተነሣም የሚሉ መናፍቃን ይህን ትምህርታቸውን ከወዴት አገኙት? ወንጌላዊው ሉቃስ የጌታ ኢየሱስን ሥጋ ሽቱ ሊቀቡ የሄዱት ሰዎች ሥጋውን እንዳላገኙትና መላእክተም «ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ» በማለት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ሕያው እንጂ ምውት አለመሆኑን አረጋግጠውላቸዋል። ሽቱ ሊቀቡት የፈለጉት የጌታ ሥጋም እንደተነሣ መላእክቱ መስክረዋል።

ሉቃስና ቀለዮጳ ወደ ኤማሁስ መንደር በሚጓዙበት ጊዜ እንግዳ ሰው መስሎ አብሩአቸው ለሚሄደው ጌታ በአዲስ መቃብር ተቀብሮ ስለነበረው ስለ እርሱ ሲነግሩት፥ «ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን ሥጋውንም ባጡ ጊዜ ሕያው ነው የሚሉ የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን ሲሉ መጥተው ነበር» ሉቃ.24፥23። በማለት ሥጋው በመቃብር እንዳልቀረ ሞትን ድል አድርጐ እንደተነሣ ገልጸዋል።

ሐዋርያቱ በዝግ ቤት ውስጥ ተሰብስበው ሳሉ ጌታ በመካከላቸው ተገኝቶ፥ «አትፍሩ እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው ይህንንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው» ሉቃ.24፥36–43። በሥጋው አልተነሣም ሥጋ የሌለው መንፈስ ግን ተነስቷል የሚሉ ክፍሎች ይህን የጌታን አነጋገር እንዴት ያስተውሉታል? ራሱ ባለቤቱ እኔ ራሴ አብሬአችሁ የነበርኩ በዕለተ ዓርብ እጆቼና እግሮቼ የተቸነከሩት ራሴ መሆኔን የተቸነከሩት እጆቼን እዩ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውም ብሏቸዋል። መንፈስ ሆኖ ሳለ ሥጋ ያለው መስሎ ታያቸው እንጂ ሥጋና አጥንት የለውም እንደይሉ፥ «እኔን ዳስሳችሁ እዩ አረጋግጡ» በማለት አስዳብሷቸዋል። ደግሞ ጌታ መንፈስ አይደለሁም ለመንፈስ እንደ እኔ ሥጋና አጥንት የለውም ብሎ ባልተናገረም ነበር። ስለዚህ የጌታ ሥጋ እንዳልተነሣ በመንፈስ ግን እንደታያቸው አድርገው



የሚያስተምሩ መናፍቃን የመጽሐፍ ቅዱስን ማስረጃነት ያልተቀበሉ መሆናቸው ተረጋግጡአል።

በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ የሚበላ እንዳላቸው ጠይቆ በፊታቸው ካጠመዱት አሣ መብላቱ በዕለተ ሐሙስ በአልአዛር ቤት «በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሮ አልጠጣም» ማቴ.26፥29 ብሎ የተናገረው እርሱ ራሱ መሆኑን ያረጋግጥላቸው ዘንድ ነው። በተናገረው መሠረት ሞቶ ከተነሣ በኋላ በፊታቸው በላ፤ ሉቃ.24፥42።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በተረዳ ነገር የተረዱት ሐዋርያት ስለ እርሱ ሞትና ትንሣኤ እስከ ሞት ደርሰው መስክረዋል። «ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን ሕይወትም ተገልጦ አይተንግል እንመሰክርማለን» 1ዮሐ.1፥1–2።

## ያረገው ማን ነው?

«ወደ ሰማይ የወጣ የለም፤ ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር እርሱ በሰማይ የሚኖር ነው» ዮሐ.3፥13።

የወጣውም፤ የወረደውም አንድ አካል አንድ ባሕርይ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ጌታ፥ «ሳያዩ የሚያምኑ ብጹዓን ናቸው» ብሎ ሳያዩት ለሚያምኑት ተስፋ ከሰጠ በኋላ ከትንሣኤው በኋላ በአርባ ቀን ውስጥ በተለያየ ቦታ ለሐዋርያት ታያቸው እጁንም በመጫን ባረካቸው ሥልጣነ ክህነትን ሰጣቸው ጳጳስነትም ሾማቸው መምህራን አደረጋቸው በምስጋናም ፈጽሞ ወደ አልተለየው ወደ ባሕርይ አባቱ ዓረገ። በሥጋና በነፍስ፤ በአጥንትና በደም፤ በሥርና በጅማት፤ በፀጉርና በጽሕም እንዳለ በጥንት አነዋወሩ ተቀመጠ ሥልጣናትም ኃይላትም መናብርትም ሊቃናትም መኳንንትም አጋእዝትም መላእክትም ሠራዊትም ሁሉ አንድ ሆነው ሕይወት ያላቸው ሕያዋን ሁሉ በሰውርም በግልጥም ያሉት የሆነውም የሚሆነውም የልብ

ሰው ቸር ሊባል አይገባውም ብሎ መለሰለት። በዚህም በልቡ አስቦ የመጣውን እንዳወቀበት ገልጾለታል ሰውየው ቸር ብለው ቸር ይለኛል በማለት ነበርና አመጣጡ። ጌታ ደግሞ የሰው ልቡና ያሰበውን ጠልቆ የሚያውቅ አምላክ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ የሠፈረ ነው። ለዚህም ማስረጃ፣ «ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሆነህ አየሁህ» ዮሐ.1፥49። እንዲሁም የሰማርያይቱ ሴት ባል የለኝም ባለች ጊዜ አምስት ባሎች የነበሩአት መሆኑን ገልጾላታል ዮሐ.4፥18።

በሉቃስ ወንጌል 11፥27፤ «አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው» ባለችው ጊዜ እርሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመልስላት፣ «ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁ ናቸው» የሚል መልስ ነበር የመለሰላት። እንግዲህ በዚህ መልሱ እናቱን ብፅዕት አይደለችም ሊል ፈልጐ ነው ሊባል ይችላል? ይህንን እንዳንል፣ «ያመነች ብፅዕት ናት» ተብሎ በሉቃስ 1፥45 ላይ ተጠቅሷል። ዳሩ ግን የጌታ መልሱ ያቺ ሴት በተንኮል መጥታለችና በተንኮል መምጣትዋን ዐውቆባት ማለትም ብፁዕ ብለው ብፅዕት ይለኛል የሚል አስተሳሰብ አድሮባት ነበርና ጌታም አንቺ ብፅዕት አይደለሽም ብፁዓን ሊባሉ የሚችሉ ወንጌልን ሰምተው የሚጠብቁ ናቸው። እመቤታችን ደግሞ የፀሐየ ጽድቅ የእውነተኛው ወንጌል የኢየሱስ ክርስቶስ እናት እንደመሆንዋ መጠን በጸጋው የተመላች መሆንዋ የታወቀ ነው።

ስለዚህ አመላለሱ እመቤታችንን የነቀፈ የሚመስላቸው ቢኖሩም እርሱ ግን ሊናገር የፈለገው ያቺን ሴት ነው። በማርቆስ 10፥28 ላይ ያለው አባባልም ከዚሁ ጋር አንድ ነው።

ማቴ.26፥39፤ «አባት ሆይ የሚቻል ከሆነ ይህ የመከራ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ነገር ግን እንደፈቃድህ እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን»

ጌታችን ወዶ ፈቅዶ ሥጋ መልበሱን (መዋሐዱን) እንዲሁም መከራ መቀበሉን መሞቱን ከደው ለማስካድ የጌታ ጠላቶች ይህን በመጥቀስ ጌታ በግዴታ እንደሞተ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ። ነገር ግን ጌታችን በስቅለቱ ዋዜማ በጌቴሴማኒ ያትክልት ቦታ ያደረጋቸው ድርጊቶች በጭንቀት ጊዜ ክርስቶሳውያን (ክርስቲያኖች) ምን ማድረግ እንዳለብን ትምህርት ሊሰጠን ፈልጐ



ነው እንጂ ጌታ ላለመሞት ቢፈልግ ኖሮ ማንም ባላገደው ወይም ባላስገደደውም ነበር። ዳሩ ግን ጌታችን በእውነት ፍጹም ሰው ሆኖአልና፣ «ከኃጢአት በቀር በነገሩ ሁሉ የተፈተነ መሆኑን» ቅዱስ መጽሐፍ እንዳስረዳው ሰው ሆኖ በመካከላችን በመገኘት እኛ ልንፈተንባቸው የምንችልባቸውን ሁሉ እርሱ ራሱ በገቢር በማሳየት በምን ዓይነት ሁኔታ ፈተናውን እንደምንወጣም በተግባር በመፈተን አሳይቶናል። ማቴ.4፥1–11።

ጌታ ግን መከራ ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል ሥልጣኑ የእርሱ ለመሆኑ፣ «ያለኔ ፈቃድ ነፍሴን ከሥጋዬ የሚለያት የለም እኔ ወድጄ እለያታለሁ እንጂ ደግሞም እስነሣት ዘንድ ስልጣን አለኝ» ዮሐ.10፥17–18 ብሏል።

አይሁድ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ለመሆኑ ማስረጃ ምልክት እንዲያሳያቸው በጠየቁት ጊዜ ጌታ በሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጐ በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ገልጾላቸዋል። ዮሐ.3፥18–21።

እንግዲህ ክርስቲያኖች መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስን አብነት በማድረግ መከራ በሚደርስብን ጊዜ ወይም ለሞተ ሥጋ ቀርበን ሳለ፣ «አባታችን ሆይ የሚቻል ከሆነ ይህ የመከራ ጽዋ ከእኛ ይለፍ ነገር ግን እንደፈቃድህ እንጂ እንደ እኛ ፈቃድ አይሁን» በማለት ሁሉ ነገር የጌታ ፈቃድ እንደሆነ እንድንገነዘብ ለትምህርት ያደረገው ነው እንጂ ደካማ ሆኖ ፈርቶ ላለመሞት ሽቶ የጸለየው ጸሎት አይደለም። በእውነት ፍርሀት የሚስማማውን የሰው ልጆችን ሥጋ እንደተዋሐደ ለማስገንዘብ ነው እንጂ።

ማቴ.24፥36፤ «ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም»

ልጅም ቢሆን የሚለው ክርስቶስን የሚያመለክት ነውና ክርስቶስ ሁሉን የሚያውቅ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም ብለው በድፍረት የሚናገሩ አጽራረ ክርስቶስ (የክርስቶስ ተቃዋሚዎች) አሉ።

ዳሩ ግን የዚህ አባባል ትንታኔ በመጽሐፍ ቅዱስ አስረጂነት እንዲህ ይገለጻል።

እንግዲህ የጌታ መምጫ ቀን በሥላሴ ዘንድ ብቻ መታወቅዋን መግለጹንና ከዚህ ውጭ ግን ከሰማይ መላእክትም ሆነ ከምድራውያን ወገኖች የተሰወረች መሆንዋን ገልጸልናል።

ዮሐንስ 14፥28፤ «ከእኔ አብ ይበልጣል»

በዚህ ምዕራፍ ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ እንዳነሰ መናገሩን ይገልጻል። ይህን አባባል ጠለቅ ብለን ስናጤነው እንደ አርዮሳውያን አባባል ወልድ በመለኮቱ ከአብ ያንሳል የሚለውን አርዮሳዊ ትምህርት የሚደግፍ ሆኖ አናገኘውም።

ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋን በመዋሐዱ መከራ የሚቀበልና ስለሰዎች ልጆች ድኅነት ሲልም በፈቃዱ እንደሚሞት ሲገልጽ ነው። ሰውን ከወደቀበት የጉስቁልና ሕይወት ለማንሣትና ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ ልዑለ ባሕርይ አምላክ ራሱን አዋርዶ ሥጋን ተዋሕዶ መከራን ተቀበለ። ይህንንም ሲያደርግ በጳውሎስ መልእክት እንደተገለጸው «ይኸውም የእግዚአብሔር መልኩ ነው፥ ቀምቶ እግዚአብሔር የሆነ አይደለም፥ ራሱን ዝቅ አድርጐ የአዳምን ባሕርይ ባሕርይ አደረገ እንጂ ሰውንም መሰለ» ፊልጵ.2፥6–7።

እንግዲህ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ የሰው ፍቅር ስቦትና አስገድዶት ራሱን ዝቅ አድርጐ በሠራው የትህትና ሥራ እንኳን በባሕርይ አንድ ከሆነው ከአብ ቀርቶ ከፈጠራቸው ከመላእክትም አንሶ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል። «ከመላእክት ይልቅ በጥቂት ያሳነሰው ስለሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን...» ዕብ.2፥7–9።

እንግዲህ ከታች የተጠቀሰውን ጥቅስ ይዘው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከመላእክትም ያንሳል ብለው ሊናገሩ ይችላሉ?

ጳውሎስ ጌታችን ስለ እኛ ሲል ራሱን ዝቅ አድርጐና አዋርዶ መላእክትን እንኳን እንዳይሞቱ አድርጐ የፈጠረ እርሱ ስለሰው ልጅ ፍቅር ሲል ግን ሞተ ብሎ እግዚአብሔር ወልድ በለበሰው ሥጋ በሰዎች ዘንድ እንደተዋረደና እንደ ሞተ ግልጽ አድርጐታል።



ጌታም ከእኔ አብ ይበልጣል ማለቱ ራሱን ዝቅ አድርጐ ሥጋን ተዋሕዶ በምድር ላይ መንገላታትን፥ ሞትን በገዛ ፈቃዱ ሊቀበል መምጣቱን ሊገልጽ ሲሆን በትህትና የሚታይበት ጊዜም አጭር መሆኑን፥ ሞትን ድል አድርጐ ከተነሣ በኋላ በልዕልና በክብሩ እንደሚኖር ሲገልጽ «ወደ አብ በመሄዴ ደስ ይበላችሁ» ብሏቸዋል። በትህትና ከአብና ከመንፈስ ቅድስ አንሶ የታየው ጌታ ተልእኮውን ከፈጸመ በኋላ ወደ ቀደመ ክብሩ ይመለሳልና (በልዕልና) ይታያልና የሐዋ.ሥራ 7፥55። «ኢየሱስን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ አየዋለሁ» ማለት በቀደመ ክብሩ በልዕልናው ሆኖ አየዋለሁ ማለቱ ነው።

ዮሐንስ ወንጌል 17፥3፤ «የዘለዓለም ሕይወትም ይህቺ ናት። ብቻህን በእውነት የባሕርይ አምላክ አንዱን አንተን የላከውንም ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲያውቁ መሆን ናት።»

ይህን በመጥቀስ ክርስቶስ እውነተኛ (የባሕርይ) አምላክ አይደለም የሚሉ አሉ። ጌታችን ግን የባሕርይ አምላክ አብ ብቻ ነው እኔ የባሕርይ አምላክ አይደለሁም የሚል ቃል አልተናገረም። ተቃዋሚዎች ግን ያለ አስመስለው ለማቅረብ ብዙ ይጥራሉ። የጌታን አባባል በጽሞና ስናጤነው ግን የራሱንም የባሕርይ አምላክነት መግለጹን እንገነዘባለን። «የላክኸው ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ» የሚለውን በአንክሮ እናጢነው። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምንነት ያውቁ ዘንድ? ነቢይ መሆኑን? ወይስ ፍጡር መሆኑን? ይህ ሊያስደንቅ አይችልም። አይሁድ ሊገነዘቡና ሊረዱ ያልቻሉት የክርስቶስን እግዚአብሔርነት–ከአብ ጋር የተካከለ መሆኑን ነበር። «ኢየሱስ ግን አባቴ እስከዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው እንግዲህ ሰንበትን ስለሻረ ብቻ አይደለም ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከሉ! እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር»። ዮሐ.5፥17–18።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር የተካከለ መሆኑን ብዙ ጊዜ ቢገልጥላቸውም አይሁድ ልባቸውን እንደ አድማስ አለት አደንድነው ሊቀበሉት ስላልቻሉ ደንዳናው ልቡናቸው ተሰብሮ የባሕርይ አምላክነቱን እንዲረዱ ሲል ጸለየላቸው። እንግዲህ የአብን

ለማውጣት የፈጠረውን ሥጋ ተዋሕዶ የወደቀውን የአዳምን ባሕርይ ባሕርይው አድርጎ መምጣቱን ሲገልጽ መሆኑን በመገንዘብ ጌታን የአብ ፍጡር ከማለት ትልቅ ስህተት መጠበቅ ይገባል። ብርሃነ ዓለም ቅ/ጳውሎስ የአካላዊ ቃልን (የኢየሱስ ክርስቶስን) በትህትና መገለጽ ሲገልጽ «ሁላችሁ ይህን አስቡ ለእኛም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አደረገልን። ይኸውም የእግዚአብሔር መልኩ ነው ቀምቶ እግዚአብሔር የሆነ አይደለም ራሱን ዝቅ አድርጐ የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ እንጂ ሰውንም መሰለ» ፊል.2፥5–7።

1ቆሮ.15፥24–28፤ «እግዚአብሔር አብ መንግሥቱን እጅ ባደረገ ጊዜ ያን ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል ገዥም ሁሉ ንጉሥም ሁሉ ኃይልም ሁሉ በተሻረ ጊዜ ጠላቶቹ ከእግሩ በታች እስቲወድቁ ድረስ ይነግሥ ዘንድ አለውና ከዚህ በኋላ የመጨረሻው ጠላት ይሻራል። ይኸውም ሞት ነው ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶለታልና። ሁሉ ይገዛለት ባለ ጊዜ ግን ሁሉን ከሚያስገዛላት በቀር እንደሆነ የታወቀ ነው። ሁሉም በተገዛለት ጊዜ ያን ዕለት ወልድም ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል። እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ በሁሉ ይሆን ዘንድ።»

«ወልድም ሁሉን ላስገዛላት ይገዛል» የሚለውን ነቅሰው በማውጣት ወልድ የአብ ተገዢ ይሆናል የሚሉ መናፍቃን አሉ። ዳሩ ግን አባባሉ እነርሱ እንደሚሉት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የአብ ተገዥ አድርጐ የሚያቀርብ ሳይሆን ከላይ ጀምሮ ጳውሎስ እየገለጸ የመጣው ሁሉ ስለማለፉ ሲሆን በተለይ በሰዎች ላይ ነግሦ የነበረው ሞት የመጨረሻው (የኋላ) ጠላት ተብሎ ተገልጾአል። ምክንያቱም ከአዳምና ሔዋን መሳሳት በኋላ የመጣ ነውና። እንዲሁም ከወደኋላ የመጣ ጠላት ጽኑዕ እንደኾነ ሁሉ ሞትንም ጽኑዕ ጠላት ሲል ነው። ይህ ሞት እንግዲህ በሰዎች ልጆች ላይ ሠልጥኖባቸው ሁሉም የእርሱ ተገዢ ሆነው ኖረዋል። እርሱም ሁሉንም ገዝቷልና። ነገር ግን ሁሉን ካስገዛለት (ሥልጣን ከሰጠው) ከወልድ ሞት እንዲያንስ ይታወቃል። ሞት በሁሉ ላይ እንዲሠለጥን ያደረገው ወልድ ነውና። ይህስ ቁም ነገር አይደለም ብሎ ካስገዛለት ከሰው ሁሉ ሞት እንዲያንስ ይታወቃል። እንዴት ቢባል በዕለተ ምፅአት የሞት ኃይል ይሻራልና ሁሉም ሞትን ድል አድርገው ይነሣሉ።



ሁሉ በተገዛለት ጊዜ ያን ጊዜ ወልድም ሁሉን እንዲገዛ ሥልጣን ሰጥቶት ለነበረው ለሞት ተገዝቷል። በዕለተ ዓርብ ጌታ ስለ ሰዎች ልጆች ብሎ እንደሞተ ሲገልጽ ነው። ነገር ግን ክርስቶስ በገዛ ፈቃዱ ሞተ እንጂ እንደሌሎች ሰዎች በግድ የሞተ አይደለም። ራሱ ወዶ ፈቅዶ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አደረ እንጂ። ይህም ወዶ ፈቅዶ ያደረገው መሆኑን ጳውሎስ ሲገልጽ «ሁሉን ላስገዛለት ተገዥ ይሆናል» አለ። ሁሉን እንዲገዛ ሥልጣን ለሰጠው ለሞት ወዶ ፈቅዶ ራሱን ሰጠ ማለት ነው።

የሐዋ.2፥32፤ «እርሱን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው» ይህን በመጥቀስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ኃይሉና ሥልጣኑ ሞቶ እንዳልተነሣ የሚናገሩና እርሱ የመነሣት ኃይል እንደ ሌለው ሌላ እንጂ ኃይል እንዳስነሣው አድርገው የሚናገሩ አሉ። ዳሩ ግን ቅዱስ ሉቃስም ሆነ ሌሎች ሐዋርያት ሲጽፉ ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ብለው መናገራቸው መለኮት የተዋሐደውን ሥጋ ከሙታን ለይቶ እንዳስነሳው ለመግለጽ ነው። ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ መሆኑን እናምናለን። ስለሆነም እግዚአብሔር የሚለው ስም የአብ ብቻ መጠሪያ ሳይሆን የወልድም የመንፈስ ቅዱስም መጠሪያ ነው ዮሐ.1፥1። የሐዋ.20፥28። ሰው የሆነው እግዚአብሔር መሆኑንና ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የዋጃት እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ ይመሰክራሉ።

እንግዲህ እግዚአብሔር ብሎ መለኮትን ለመግለጽ ተጠቀመበት እንጂ አብ በቻውን ያለ ወልድና ያለ መንፈስ ቅዱስ አስነሺ ወልድ በባሕርይ ሥልጣን ከአብ የተለየ ወይም አብ ብቻ ብርቱ ወልድ ግን ለመነሣት ሥልጣን የሌለው ደካማ ነው ለማለት አይደለም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ፈቃዱ ለመሞቱ በገዛ ሥልጣኑ ለመነሣቱ በዮሐ.10፥17–18 ላይ ተገልጾአል። «ስለዚህም አብ ይወደኛል እኔ ሰውነቴን ለበጎቼ ቤዛ አድርጌ አሳልፌ እሰጣለሁና እንደገና እስነሣት ዘንድ እኔ ራሴ በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣታለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት የለም ነፍሴን ከሥጋዬ ልለያት አዋሕጄም ላስነሣት ሥልጣን አለኝና ይህን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልኩ።»

እንዲሁም ጌታ በሥልጣኑ ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሣ ሲገልጽ «ጌታ ኢየሱስም ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስተኛውም ቀን አነሣዋለሁ ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም ይህ ቤተ መቅደስ በአርባ ስድስት ዓመት ተሠራ አንተስ በሦስት ቀናት ውስጥ ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ቤት ስለተባለ ስለ ሥጋው ነገራቸው ከሙታን በተነሣ ጊዜም ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ እንደነገራቸው አሰቡ» ዮሐ.2፥19–22።

እንግዲህ በሦስት ቀናት ውስጥ የሚያስነሣኝ አለ ሳይሆን ያለው ራሱ በሥልጣኑ እንደሚነሣ መግለጹን አስተውሉ።

1ጢሞ.2፥5፤ «አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።»

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅ ነው ብለው የሚያምኑ ክፍሎች ብዙውን ጊዜ ይህን ጥቅስ እንደመረጃ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ ወይስ ተማላጅ? ለማኝ ወይስ ተለማኝ፤ አስደራጊ ወይስ አድራጊ? አስማሪ ወይስ መሐሪ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ስለ ምሥጢረ ሥላሴ ማወቅና መረዳት ያስፈልጋል በሥላሴ ትምህርት ላይ አብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ እንደማይበልጥ በሥላሴ ዘንድ የሥልጣን ተዋረድ እንደሌለና በሥልጣን፤ በአንዛዝ፤ በመለኮት፤ በባሕርይ አንድ መሆናቸው በምዕራፍ ሁለት ላይ በስፋት ተዘርዝሯል።

እንግዲህ በሥላሴ አምናለሁ የሚል ከላይ የተገለጸውን መቀበሉ ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመለኮታዊ ሥልጣን የማይበላለጡ መሆናቸው በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጸ ነው። «እኔና አብ አንድ ነን» ዮሐ.10፥30።

ይህ እንዲህ ከሆነ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ብሎ ጳውሎስ ያስተማረው ምንን ሲያመለክት ነው? የክርስቶስን አማላጅነት አይደለምን፤ ለሚሉ የሚቀጥለውን መልስ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርገን እንመልሳለን።



በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርታችን ላይ ክርስቶስ ሰው የሆነበት ምክንያት በዝርዝር የተገለጸ በመሆኑ እዚህ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም። ዳሩ ግን ባጭሩ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌው ያደረጋቸው የትሕትና ሥራዎች ምልጃን ጨምሮ ለካሣ፤ ለቤዛ ዓለም ያደረገው መሆኑን ነው። እነዚህም የቤዛነት ሥራዎች በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የፈጸማቸው ናቸው። አሁን ግን በትሕትና በምድር ላይ የተመላለሰበት ጊዜ አልፎ በልዕልና በቀደመ ክብሩ ስላለ በምድር ላይ በሥጋ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ ያደረገውን ይዞ አሁንም ያማልዳል ማለት ስሕተት ነው። ስለ አዳምና ስለ ልጆቹ ጸሎትና ምልጃ አቅርቦ ነበር ይባላል እንጂ አሁን በልዕልና እያለ ያማልዳል አይባልም።

ዳሩ ግን ሕያው አምላክ የፈጸመው የቤዛነት ሥራ (የማስታረቅ አገልግሎት) መቼም መች ቢሆን ዘመን አይሽረውም፤ አይለውጠውም። የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ የፈጸመው የማስታረቅ አገልግሎት ዛሬም ለእኛ ይሠራል። ለወደፊትም እንደዚያው። ይህ የቤዛነት ሥራ ዛሬም ሕያው መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ «ዘወትር በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር (አብ) የሚቀርቡትን ሊያድናቸው ይቻለዋል። ለዘለዓለም ሕያው ነውና ያስታርቃቸዋል» ብሏል ዕብ.7፥25።

ያስታርቃቸዋል ሲል በዕለተ ዓርብ በፈጸመው መሥዋዕትነት የማስታረቅ አገልግሎት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚነሱትን ምእመናን እንደሚያድንበት ሲገልጽ ነው እንጂ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሎ እንደጸለየው ዛሬም ከአብ መንበር ሥር ተንበርክኮ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ይላል ለማለት አይደለም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለየ አካሉ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ መሥዋዕት በመሆኑ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን የጠብ ግድግዳ አፍርሶታል። በዚህ መስዋዕትነቱም ከፅንስ ጀምሮ እስከ ስቅለቱ ድረስ በፈጸመው ካሣ አዳምን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ እና ከራሱ ጋር አስታርቋል።

ይህን በዕለተ ዓርብ የፈጸመውን የማስታረቅ አገልግሎት ለመግለጽ ፈልጎ እንጂ ክርስቶስ ለማኝ አብ ተለማኝ ነው ለማለት አይደለም።

ምናልባት አንድ ሰው «በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አንድ አለ» አለ እንጂ መች «ነበር » አለ? «ያስታርቃቸዋል» አለ እንጂ «መች አስታርቋል» ብሎ በኃላፊ ግሥ ዓረፍተ ነገሩን አሠረውና ነው እናንተ የዕለተ ዓርብን ለመናገር እንጂ የአሁኑን ለመናገር አይደለም የምትሉት። ስለዚህ ዛሬም ቢሆን እንደቀድሞው ያማልዳል ሊል ይደፍር ይሆናል።

የመጽሐፍ ቅዱስን የአጻጻፍ ዘይቤ ጠንቅቆ ካለማወቅ ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ አጻጻፍ ስልት ተሰናክለው ሲወድቁ ይታያሉ። የወደፊት ጊዜን በኃላፊ ግሥ መግለጽ የመጽሐፍ ቅዱስ አጻጻፍ ጠባይ ነው።

ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን አነጋገሮች እንመልከት ዘፍ.3፥22፤ «እግዚአብሔር አምላክም አለ፥ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» ይህ አነጋገር ለወደፊት ከ5500 ዘመን በኋላ)' ከሦስቱ ግሩማን አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ የአዳምን ሥጋ (የእመቤታችንን) እንደሚዋሐድ የሚገልጽ ሲሆን ዳሩ ግን «ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ በማለት አዳም በሳተበት ወቅት እንደሆነ አድርጐ ነው የገለጸው። ከሰዋሰው ሕግ አንጻር ግን «ከእኛ እንደ አንዱ ሊሆን ነው (ይሆናል) ብሎ ለወደፊት የሚሆን ድርጊት መሆኑን መግለጽ ነበረበት።

መዝ.21(22)፥12–30፤ በዚህ ምዕራፍ ያለው ቃል ሁሉ ለወደፊት በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚፈጸመውን ድርጊት የሚገልጽ ሲሆን ዳሩ ግን አጻጻፉ በዚያን ወቅት እንደ ተፈጸመ ሆኖ የቀረበ ነው። «እጆቼንና እግሮቼን ይቸነክሩኛል» ማለት ሲገባው «ቸነከሩኝ» ብሏል። «በቀሚሴም ላይ ዕጣ ይጣጣላሉ።» ማለት ሲገባው «ተጣጣሉ» በማለት ከሺህ ዘመን በኋላ የሚፈጸምን ድርጊት እንደተፈጸመ አድርጎ አቅርብዋል።

ኢሳ.53፥1፤2፤ ያለውን ብናይ «በእውነት ደዌያችንን ይቀበላል።» ማለት ሲገባው ምክንያቱም ኢሳይያስ ጌታ ከመወለዱ በፊት የነበረ ነብይ ነውና። ትንቢቱን በኃላፊ ግሥ ደዌያችንን



ተቀበለ» በሚለው ተናግሮታል «እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ይቆስላል» ማለት ሲገባው ቆሰለ (ኃላፊ ግሥ) ...ስለ ዓመፀኞችም ይማልዳል ማለት ሲገባው «ማለደ» በሚለው ኃላፊ ግሥ ተናግሯል።

ስለዚህ ከላይ በማስረጃነት እንዳየነው መጽሐፍ ቅዱስ የሰዋሰውን ሕግ አይጠብቅም (አይጠነቀቅም) በመሆኑም «በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አንድ አለ» «ያስታርቃቸዋል» ወይም «የሚማልደው» የሚሉት አባባሎች በዕለተ ዓርብ የተፈጸመውን የቤዛነት ሥራ የሚያመለክቱ መሆናቸውን ልንገነዘብ ይገባል። ስለሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ባሕርይ አባቱ ተማላጅ እንጂ አማላጅ፤ ተለማኝ እንጂ ለማኝ፤ አድራጊ እንጂ አስደራጊ አይደለም።

በምድር ላይ በሥጋ ተገልጦ በትሕትና በተመላለሰበት ጊዜ መማለዱ ስለ አዳምና ስለ ልጆቹ ተወክሎ እንጂ በባሕርይው ደካማ ሆኖ ወይም አማላጅ ሆኖ አለመሆኑም ሊጤን ይገባዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው ነው። (የባሕርይ አምላክ ነው) ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ» ዕብ.13፥8።

ሮሜ.8፥34፤ «የሚፈርድ ማነው ክርስቶስ ኢየሱስ ሞተ ከሙታንም ተለይቶ ተነሣ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል ስለ እኛም ይፈርዳል»[24]

በቅርብ ጊዜ በታተሙት የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ላይ ግን «ስለ እኛ የሚማልደው» ተብሎ ተተርጉሟል። ተርጓሚዎች ከምን አንፃር እንደተረጎሙት ግልጽ ባይሆንም መሠረታዊ አባባሉ ግን የጌታን ፈራጅነት ለመግለጽ የተነገረ መሆኑን ከቀደሙት የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ማረጋገጥ ይቻላል።

1ቆሮ.11፥3፤ «የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ የሴትም ራስ ወንድ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር» ይህን በመጥቀስ ክርስቶስ የአብ ፍጡር ነው የሚሉ አሉ። አባባሉን በአንክሮ ስናጤነው ግን መናፍቃኑ እንደሚሉት ሆኖ አናገኘውም። እንደ መናፍቃኑ ትርጉም ከሔድን

---

[24] አዲስ ኪዳን (በአማርኛ) በዩናይትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካ በናሽናል ባይብል ፕሬስ ፊላደልፊያ 1938 ዓ.ም፤ ሐዲስ ኪዳን (በግዕዝና በአማርኛ) በሊቃውንት ጉባኤ ታርሞ የተዘጋጀ።

## ለጽሑፉ ረዳት የሆኑ መጻሕፍት (References)


1. ሐዲስ ኪዳን (በግዕዝና በአማርኛ) በሊቃውንት ጉባኤ ታርሞ የተዘጋጀ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1975 ዓ.ም
2. መጽሐፍ ቅዱስ (በአማርኛ በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች)
3. ሃይማኖት አበው ተስፋ ገብረ ሥላሴ፣ አዲስ አበባ 1982 ዓ.ም
4. ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ በ1966 ዓ.ም
5. አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ አዲስ አበባ በ1978 ዓ.ም
6. አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን) ሠርሐ ሃይማኖት ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1949 ዓ.ም
7. መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት) የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ
8. ምሥጢረ ሥላሴ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1960 ዓ.ም
9. ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀመዘምራን) መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ኮከበ ጽባሕ ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍ.ሃ ማተሚያ ቤት አሥመራ 1969 ዓ.ም
10. መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት) መጻሕፍተ ሐዲሳት ሦስቱ ንባቡ ከነትርጓሜው በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1951 ዓ.ም
11. መዝሙረ ዳዊት ንባቡ ከነትርጓሜው አዲስ አበባ 1973 ዓ.ም
12. አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን) መድሎተ አሚን ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1954 ዓ.ም
13. መዝገበ ሃይማኖት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል የተዘጋጀ አዲስ አበባ 1959
14. ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው አዲስ አበባ 1983
15. ትምህርተ ኅቡአት (በአማርኛ) ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማ/ቤት አዲስ አበባ 1983 ዓ.ም
16. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ) መጽሐፈ ሕዝቅኤል ከትርጓሜው ጋራ 1916 ዓ.ም





17. ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ዜና ሐዋርያት በጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1923 ዓ.ም
18. H.G. BISHOP MOUSSA, St. Athanasius and Incarnation Coptic Orthodox Patriarchate.
19. H.H. POPE SHENOUDAIII, Comparative Theology.
20. H.H. POPE SHENOUDAIII, Nature of Christ.
21. Fr. TADROS Y. MAIATY, Man and Redemption Ottawa, Ontario, Canada.